አግዐዚ።

ወደ ውጭ አገር ሔጄ ነበር።

ልብ ወልደና ታሪክ ወለድ።

የአግአዚ እናት አባት ወንድምና እህት ቄሱ መነኩሴ ሳይቀር አትሒድ ብለው ሲለምኑት።

ተጻፈ።

ከወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ።

ትኅትመ ዝንቱ መጽሐፍ በ፴ በ፳ መንግሥቱ

ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢዮጵያ።

አዲስ አበባ ፲፱፻፳፭ ዓመተ ምሕረት።

በቅዱስ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት ታተመ።

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።

Join us on Telegram @amharicbookss

ማውጫ

መግቢያ። 1

አግዐዚ የአሳብ መነሻ ያደረገው መቅድም። 2

አንደኛ ክፍል። 4

የማየት ፍሬ። 4

ሁለተኛ ክፍል። 12

ልሒድ አትሔድም። 12

ሦስተኛ ክፍል። 23

የእናቴ የወይዘሮ ያዳንቁሽና የአባቴ አቶ አደገኛ ንግግር። 23

አራተኛ ክፍል። 30

ደህና ሁን ደህና ይመልስህ። 30

ደህና ሰንብቱ ደህና ቆዩኝ። 30

አምስተኛ ክፍል። 32

የባሕር ላይ ጉዞ። 32

ስድስተኛ ክፍል። 36

የሀገሬ ትዝታ። 36

ሰባተኛ ክፍል። 44

በኢትዮጵያ ተራራ የሥልጣኔ ጮራ። 44

ስምንተኛ ክፍል። 49

በእንደዚህ ያለ አለኝታ ስኖር። 49

ዘጠነኛ ክፍል። 53

ግርማዊነታቸው በኤውሮፓ። 53

ዓሥረኛ ክፍል። 55

አፍሮ አይገቤ። 55

አሥራ አንደኛ ክፍል። 62

እኔው ሙቼ እኔው አልቃሽ አለ መሆኔ። 62

አሥራ ሁለተኛ ክፍል። 66

ስለ አበርኞች ብርታት። 66

አሥራ ሦስተኛ ክፍል 69

Join us on Telegram @amharicbookss

ጸሎተ ንዋም 69
አሥራ አራተኛ ክፍል 80
በትግሉ መጨረሻ የተገኘው ድል። 80
አሥራ አምስተኛ ክፍል። 84
አዲሱ ዘመን ኑሮአችን። 84

Join us on Telegram @amharicbookss

መግቢያ።

ዓለም እንድትስቅልህ ሳቅላት አለዚያ ግን በኃዘን እንደ ተኩራመትህ ወደ መቃብር ትወርዳለህ ይባላል።

ይሁን እንጂ እየሳቀ ኃጢአት የሚሠራ፤ እያለቀሰ ወደ ሲኦል ይወርዳል የተባለውን አለማስታወስ ከጉዳት መጣሉ የታወቀ ነው። ስለዚህ ለመምከርም ለመመከርም ለማወቅም ለማሳወቅም ፤ብዙ ጽሑፎችን መመልከት ተጠቃሚ ማድረጉን የሚጠራጠር እጅግ የተሳሳተ ነው።

ዛሬ በዓለም ላይ በልብ ወለድነትና በታሪክ ወለድነት የተከናወነውንና የሚከናወነውን ጥበባዊ ተግባርና ረቂቃዊ ፍልስፍና ሁሉ በረቂቅ አስተያየት ለመመልከትና ለትውልድ ልብ ወለዳዊ አሳብ ለመስጠት እንደሚገባው አድርጎ የመረቅ ፍትፍት በሆነ አማርኛ መግለጽ ያስፈልጋል። ምግብ ካልጣፈጠ እንደማይዋጥ ጽሑፍም ካልጣፈጠ አይደመጥም።

ጌታ የጌታ ልጅ ነፃ የነፃ ሀገር ተወላጅ የኔ ዘመድና ወዳጅ አግዐዚ» የሚባል «ኢትዮጵያዊ ወጣት» የሥልጣኔው ጊዜ አስረግዞ የዕውቀት ዘመን የወለዳቸው የትምህርት ቤት ኰትኵቶ ያሳደጋቸው የኤሮፓ ሕዝቦች ተምረው ከተቋቋሙበት ደረጃ፤ ሠልጥነው ከደረሱበት እርምጃ ደርሶ ውዲቱን አገሩንና ተወዳጅ ንጉሠ ነገሥቱን ስመ ጥሩ የሆነውን ወገኑን ለማገልገል በዚህ ፲፱፻፳፩ ዓ.ም ለትምህርት ወደ ውጭ አገር ለመሔድ ከተነሣበት ቀን ጀምሮ፤ እስከ ተመለሰበት ጊዜ፤ በጉዞውና ያየውን አገር በኖረበት መንደርና በረገጠው ምድር ሁሉ ያየውን ልዩ ልዩ ታሪክና የደረሰበትን ዘመናዊ ትግል አንድ፤ በአንድ በቃል ነግሮኝ ነበር።

እኔም እሱው እንዳየው እሱው ጽፎ እሱው ያሳትመዋል በማለት፤ ተስፋ አድርጌ ሳለ በልዩ ምክንያት ሊጽፈው ሳይቻለው ቀረ ማለትን ስለሰማሁ ያሰበው እንዳይቀርበት፥ እሱን ሁኜ በሱ ተገብቼ ከብዙ በጥቂቱ ተገልጾ ሐሳቡ በጽሑፍ ጐልቶ በማኅተም ተራብቶ ለሁሉ ይደርስ ዘንድ በማለት ይህን ትንሽ መጽሐፍ አሰናድቼ ሳቀርብ፤ ተመልካቾች በውስጡ ባለው ፍሬ ነገር እንዲጠቀሙበት እየተማመንሁ ነው።

Join us on Telegram @amharicbookss

መግቢያ

ይህ መጽሐፍ ከዚህ ቀደም በ፲፱፻፹፰ ዓ.ም ከሙሉ በክፍሉ ባዲስ ዘመን ጋዜጣ እየተከፋፈለ ይቀጥላል እየተባለ ታትሞ ስለ ነበረ፤ ሑረተ ቃሉንና ሐሣበ ፍኖቱን የተከታተሉ ከቶውንም ስለ ባሕረ በር አከፋፈት ብዙ የትንቢት ቃል ስለ ነበረበትና ይህም ዛሬ ስለ ተፈጸመ ለምን በመጽሐፍነት መልክ አሳትመውም፥ እያሉ ስለጠየቁኝ ከዚህ ቀደም በጋዜጣም የወጣውንና ከጋዜጣ ተቆርጦ የቀረውን አንድነት ሰብስቤ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለ፷፩ኛው ዓመት የልደት በዓል መታሰቢያ እንዲሆን ታተመ።

አግዐዚ የአሳብ መነሻ ያደረገው መቅድም።

በዚች በምታስገርም ዓለም በአስገራሚነቷ ላይ አስገራሚ ነገር ሲደረግ ከመኖሩ የተነሣ ከመንገድ ላይ ቁሞ ፍጥረትን በሚያስተላልፈው በዓለም ፖሊስነት የሚዘዋወረውን የደቂቀ አዳምን መንገድ ሲመረምሩት፥ ደንና ጥሻ፤ ገደልና ዋሻ ወጣ ገባና ስርጉጥጉጥም ሆኖ ይገኛል።

እንደ መንገዱም የመንገደኝኖቹ ታሪክ የዚያን ያህል ነው። ቢሆንም የቀድሞው ትውልድ ብዙውን ሺህ ዓመት ያህል ዘዴ ካለፈው በኋላ መሻሻል ምን እንደ ሆነ ለመሞከር ጀመረ። ከል ማድረግ ነፃ ለመውጣት ታገለ። ልማድም አልወድቅም ብሎ በብርቱ ተከላከለ።

ይሁን እንጂ ልማድ በግድም በውድም መሸነፉ ስላልቀረ ሥልጣኔ በአዲስ አእምሮ እንጂ በዘር በሩካቤ የሚገኝ አለመሆኑ ታወቀ።

ዓለምም የቀድሞውን ዕድፋምነት ትታ መኳኳልና መዋዋብ ራሷን መሠራራትና መታሸም ጠጉሯንም ማሰማመርና በሚያንፀባርቅ መልክ መታየት ፈቀደች። ከዚህ የተነሣ ልማድን ዘወር በል ብላ አፍንጫውን ለማለት በትር ብትመዝበት ካንቺ ጋራ ምን አታገለኝ በማለት እልም ብሎ ጠፋ። ከዚህ ወዲያ ዓይኑ አልታየም። ድምፁም አልተሰማም።

በዚህ ምክንያት ከላይ እንዳልሁት ሥልጣኔ እግሩን ለመግባት ሥር ለመስደድ የሕዝቡን ልብ ለማግኘት ተመቸው። አገር ዕልል ብሎ ተቀበለው። ልጅ ተወልዶ ወደ ተማሪ ቤት ተማሪ ተምሮ ወደ ሠራተኛነት ሠራተኛ ሠርቶ ወደ ከበርቴነት ለመድረስ የሥልጣኔ መንገድ በሰፊው ተጠረገ።

Join us on Telegram @amharicbookss

እኛም አንማር ልጆቻችንንም እናስተምር ሲሉ የነበሩ ሰዎች ያ የጠሉት የሥልጣኔ ትምህርት ዛሬ ጠቃሚ መሆኑን በወጣቶቻቸው ተረዱት። ጣዕሙን ቀመሱት። ጥቅሙን ዐወቁት።

የታሪኩ ዚቅ ከዚህ ላይ ነው። ክረምት ሲጠሉት እንዲያከብር ያ የጠሉት አዲስ ልማድ ሽማግሌዎችን በልጆቻቸው እስከበራቸው። ለማናቸውም ነገር ምክንያት አለው። ያለምክንያት ሊጀመርም፤ ሊጨረስም የሚቻል ነገር የለም። በምክንያትም ለሚፈሙት ዋና ዋና ነገሮች ዋና ሰው ያስፈልጋቸዋል። ለዋናውም ሰውየ መብትና ጊዜ ይኖረው ዘንድ አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ጊዜውም ሳይደርስ፤ ውናውም ሰው ሳይገኝ ይፈጸሙ ዘንድ ሊያስፈልጉት ጉዳዮች ምክንያት አይገኝላቸውም። ስለዚህ ኢትዮጵያ ከፍ ከፍ እንድትል ወጣቶቿም የዕውቀት ተካፋይዮች እንዲሆኑ፤ በገሪቱም በሥልጣኔ እንድታብብ በጥበብ ጌጥ እንድትዋብ እግዚአብሔር ምክንያት ሲፈጥር ለዚህ ችሎታ ያለው ሰው ፈለገ። ፈልጎም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን አገኘ። ጊዜና መብት ሰጣቸው። ዕድልና ድልንም አደላቸው።

ኢትዮጵያም እንድትለማ የሚቻልበትን መንገድ እንዲዘረጉ ረዳቸው። ቀኛቸውን በቀኙ ይዞ ደገፋቸው።

ይህን መብትና አምላካዊ አደራ የተቀበሉ ንጉሠ ነገሥታችንም የሀገር መብራት ትምህርት፤ የትምህትም መቅረዝ የወጣቶች አእምሮ መሆኑን ተገነዘበው፤ ትምህርትን ከነአስተማሪው ከኤሮፓ ቀጥረው አስመጥተው ባቋቋሙት ትምህርት ቤቶች የዕውቀት ሥልጣኔ እንዲጐርፍ አደረጉ።

ይሁን እንጂ ያ ዘመን ገና ሙሉ ብርሃን አልነበረውም። ለግል ጉዳያቸው ሲሉ ልማድ እንዳይሻሻልና ሥልጣኔ በር እንዳይከፈት ወደ ኋላ የሚጐትቱ አንዳንድ የዱሮ ሰዎች ስለአልታጡ ልማድ ለምን ይለውጣል። ኑሮስ ለምን ይሻሻላል። ኑሮ ሲባል ያው ኑሮ ነው። መሻሻልስ መሰልጠንስ ምንድን ነው። ካባት ያልቆየንን ለልጅ አናቆይም ለማለት መገበዛቸውን ስላልቀረ ሕይወትነት ያለው ነገር ሁሉ ሞት መስሎ ይታያቸው ነበር።

ግርማዊነታቸውም ቀን ሊሠራ ሲደለድል ሲያመቻችና መሠረቱን ሲጥል የዋለውን ሥራ ሌሊት የልማድ ድጅኖአቸውን እየያዙ እናፍርስ በማለት ሲታገሉ ለማፍረስ ሳይችሉ ያ የተተገኑበት

Join us on Telegram @amharicbookss

ጨለማ እየነጋና ጎሕ እየቀደደ ስለ ሔደ አሳባቸው ሁሉ ይገባ ዘንድ ከበር የደረሰውን ሥልጣኔ ሊያግደው አልቻለም።

ስኳን ጠርተውትና ሳይጠሩትም የመጣ ከበር ከደረሰ በኋላ ተመለስ ሲሉት ማስቸገሩ አይቀርም። በግርማዊነታቸው ንጉሣዊ ቃል ለወጣቶች መልካም ዕድል ለኢትዮጵያ የደስታ በዓል ተጠርቶ የመጣው ሥልጣኔ የዱሮ ሰዎች ምንም ቢከላከሉት። ወደ ኋላ አላለም። እየገፋ መጣ። ከደጃፍ ደረሰ። መድረኩን ተራምዶ ከውስጥ ገባ። ሕፃናትም እንደሆሣዕና ዕልል ብለው ተቀበሉት። የትምህርት ጡት አስጣይ ለመሆን የታሰበው ልማድም እንደ መሸነፍ አለ።

ነገር ግን የዱሮ ልማድ ምንም ቢሸነፍ ውሥጥ ውሥጡን ገና ነበር። ምነው እናንተ በቀራችሁና በቃሪያችን በበላን የማለት መንፈስ ባንዳንድ ሽማግሌ አሳብ ነበር። ከልጅነት፤ እስከ ሽበት ያጠራቀምሁትን የልማድ ኲተት ለምን እለቀና፤ ልጄስ ለምን ይማርና በማለት አንዳንድ ሰው ለመከላከል ባይችል እንኳ ያፍ ልማዱን መናገር አልቀረም ነበር።

እኔም በዚያ ጊዜ ከትምህርት ውጭ ሆኖ ከዕውቀት ፈንጠር ብሎ የቆየው ወጣትነቴ ከትምህርት ዳር ሆኖ እንዳይቀር፤ የጥበብ ተወላጅ የሥልጣኔ ተዛማጅ እንድሆንና የዕውቀት ባላባት እንድባል ተምሮ ለማወቅ ወደውጭ አገር ጕርፍ ወሰደኝ።

እንዲህ ነው ውሀ አወሳሰድ።

አንደኛ ክፍል።

የማየት ፍሬ።

ከአገር ወደ አገር መዞር ብዙዎች ነገሮች ለመመርመርና መርምሮም በተገኘው የማየት ፍሬ ታላቅ ዕውቀት ለማግኘት ይችላል። ይልቁንም በትምህርት ምክንያት የሚደረገው ነሰሳው ብዙ ጥቅም አለው።

ገና ከትምህርት ቤቱ ሳትደርስ በመንገድ ሳለህ ጠቃሚ የሆነ ብዙ ትምህርት ታገኛለህ። አፍህ ሀሁ ሳይል አስተማሪዎች በጥቁር ሰሌዳ ላይ የፊደሎችን ቅርጽና መልክ ሳያስገነዝቡህ

Join us on Telegram @amharicbookss

ዓይኖችህ ባዩት ጆሮዎችህ ብቻ ባዳመጡት፤ አእምሮህ መርምሮ በተገነዘበው፤ ብዙ የትምህርት ፍሬዎችን ልትለቅም ትችላለህ።

ሰማዩን በአኤሮፕላን ሲንሸረሸሩበትና ነፋስን እየሰነጠቁ በስንጣቂው ውስጥ ሲተላለፉ ታላቅ ዕውቀት ይገኛል። የብሱ በባቡር ሲሽከረከሩት መሬቶችን ሁሉ እያቋረጡ ሲሔዱ ከፍ ያለ ጥበብ ይወረሳል። ባሕሩን በመርከብ ሲንሳፈፉና የማዕበላትን ወሬሳ አነሣሥ እየተካከሉ ሲታለፍ፤ የሚታየው ትንግርትና የሚገጥምህ አድናቆት ምን ተብሎ ይነገራል።

ያላየኸውን ባወራልህ የማትበላው የጾም ምግብ ይሆንብህ ይሆን። ማየቴ ማየት እንዲሆልህ እንዴት ብየ ልንገርህ። እንዴትስ አድርጌ ላስረዳህ። የነፋሱ አነፋፈስና የባሕሩ አንቀሳቀስ ደስታዎች በሰውነትህ እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋቸዋል። የማዕበሉ አዘላለል ረድፍ ረድፍ እያበጀ ሲገነፍልና ፈረሰኛውን ፈረሰኛ እየተከታተለው ባሕሩን እየለቀቀ በተፈጥሮ ሳይሆን እብገዛ ኃይሉ ባበቀለው ክንፍ አግድም ሲንቻረር «እግዚአብሔር መንፈስ በወሀዎች ላይ ይሰፍ ነበር» የተባለው ቃለ ኦሪት ሲተረጐም ታየዋለህ። ማዕበሉ እንደ ሰገኖ አንገቱን አስግጎ በኋላ እግሩ ቀጥ ብሎ ቁሞ እንደገና በፊት እግሩ ደፋ ሲል በስግደት ላይ የሚገኝ ባሕታዊን ይመስላል። ይህንም ይተወውና ሲያገፍትና በዳልጋው ልዩ ልዩ ጅምናስቲክ ሲሠራ በተፈጥሮ ፈጣሪውን የሚያስመሰግን ተግባር ይፈጸምበታል።

በዚህ ሁሉ ምክንያት አሳብህ በጥሞና የሚያዳምጠው የባሕሩን ምሥጢረ ምግባርና የማዕበሉን እስፖርታዊ ሥራ ነው እንጂ፤ ሌላ ፊትን ዘወር የማያሰኝና አሳብን የሚማርክ ነገር አይገኝም። ከታች የዓይን ማረፊያ ዛፍ ከላይ የሕዋ መሸፈኛ አዕዋፍ ለበስማም ወልዴው አይታይም። ውቅያኖሱ ለጥ ሰማዩ ቅል ጥጥ ብሎ ሲታይ ዓይንን ምዕራፍ ያሳጣዋል። ከቶውንም ሰማዩን ወደ ምድር ምን አወረደው። ምድሩንስ ወደ ሰማይ ምን አውጣው ያሰኝሃል። ፀሓዩና የባሕሩ ጽርየት ሲፈካከር ዓይነ ወርቅ የሆኑ ብልጭልጭታዎችና የዕንቍ ጠቃጠቆ የመሳሰሉ ወራውርቶች እንደ ቢራቢሮ ሲፈናጠዙና እንደ ጅራታም ኮከብ ሲወረወሩ የዓይኖችህ ነጸብራቆች አብረው ይወነጨፋሉ።

Join us on Telegram @amharicbookss

ይህን የመሰለው ተጨዋችነታቸው የሰውን አዝማሪና ዘፋኝ ያስንቃል። የሰው ዘፋኝ ተጫውቶ በመጨረሻው ገንዘብ አምጡ በማለቱ ደስታን ይቀንሳል። ቢከለክሉትም ይሳደባል። ማዕበሎቹ ግን የሚያቀርቡት የጨዋታ ዓይነት ዋጋ ስለ ማይጠየቅበት ደስታው ዕጥፍ ነው።

አንደኛው ማዕበል በሁለተኛው ማዕበል ፊት ሲቆምና ቃለ ግርማውን ሲያንጐደጉደው የቅኔና የአንገርጋሪ መሪና ተመሪ ይመስላል።

ነፋሱ ባሕሩን ከተኛበት ቀስቅሶ እንደ ሕፃን በደረቱ ላይ አድርጎ ሲያስጨፍረውና ሲያስቦርቀው እንቡር፤ እንቡር፤ እያሰኘና እሽሩሩ እያለ ሲያስፈነጥዘው ሲያቃብጠው ለተፈጥሮው ምን ያህል የቀበጠ ጠባይ እንዳለው የተመልካችን አሳብ በምርመራ ላይ ያውለዋል። ለነፋስ ያለው ጠባይ ዕብደት ስለሆነ ባሕሩ እንደ እሱው ያበደና የተሟረ እስኪሆን ድረስ አያሳርፈውም። ይህም አደራረግ በአንድ በኩል የሚያቀርበው ግምት በጥልቅ አስተያየት የተመሠረተ ነው።

ባሕሮች አስጨፋሪያቸውና አስቦራቂያቸው ከሆነው ከነፋሱ የሚያገኙት ውዝዋዜና ንቅናቄ ለተፈጥሮዋቸው የሚመች የጤና አጠባበቅ ዘዴ ሳያገኙላቸው አለመቅረቱን ለመረዳት ለማዕበሉ ከነፋሱ ጋር ያለው ትግል ልፊያ ሊያስረዳን ይችላል።

ነፍሱ ጸጥ (ዲብ) ሲል ባሕሩ እንደ ጸሎተ ሐሊና አድራሽ ድምጹን ጥፍት ያደርጋል። ኰሽ አይልበትም። ከቶውንም ሁሉንም ይተወውና፤ ይዝላል። ሥርዓተ ሞት እንደደረሰለት ምውት አሳቡን ጥሎ ዟ ብሎ ይዘረጋል።

ምክንያቱም ወሀዎች ለዓለም የሥር ደም ሲሆኑ፤ ነፋሶች ለወሀዎች የደም ሥርና የሕይወት ደም ስለሆኑ ነው። በዚህም ጊዜ ወሀውን እንዳሻኰራ (እንደ ጥና) የሚወዛወዘውና ማዕበል እንደ ቆራቢ አፉን ይዞ ዝም በማለቱ መርከቦቹ አካሔዳቸውን ይቀንሳሉ። በመርከቡም ውስጥ ያሉትን የባሕር ጉዞኞች ባሕሩ ሲያኰርፍና ማዕበሉ አርምሞ ሲያድርግ እንቅልፍ እንቅልፍ ይላቸዋል። ድካምም ይሰማቸዋል። ሕይወታቸው ደስታው የሸሸበትና በሙቀት ውስጥ የታፈነ ይሆንና ጉዞአቸውን ዋጋ የሌለው ያደርገዋል።

Join us on Telegram @amharicbookss

ይህም የሚሆንበት ምክንያት ማዕበሉን የሚፈጥረው ነፋሱ በመሆኑ፤ የማዕበሉ መንቀሳቀስ በባሕሩ የሕይወት መንፈስ ስለሚያሳርፍበትና ባሕሩ የተቀበለው የመንቀሳቀሻ ሕይወት ለባሕሩም ጉዞኞች ደስታን ሰለሚያስገኝላቸው ነው።

ለዚህ ሁሉ መሠረት የሆነው የሕዝቦች ጉዞኛነት መጀመሪያ በመሬት ተጀምሮ ቀጥሎ በባሕር በኋላም፤ በዓየር ይሆን ዘንድ የሰው ልጅ መንቀሳቀሻዎች ሊያስረዱ ስለቻሉ፤ ሰፊ መሬት ላለው መንግሥት ሰፊ ባሕር ከማስፈለጉም በላይ በዚሁ ቁና ዙር ልክ ዓየር ከነ ዓየር ኃይሉ አስፈልጎታል። ይህንም ለማለት ምክንያት የሆነኝ ወደ ውጭ አገር ያደረግሁት ጉዞኛነቴ ነው።

ከላይ እንደ ተባለው የባሕሩ ተፈጥሮ በመመልከትና ባሕር ያላቸው አገሮች ያሚያገኙትን ታላቅ ጥቅም በማመዛዘን ልቤ በኀዘን ተነካ። የሃሳብ ማዕብል አናወጸኝ። ብስጭት ያዘኝ። ቆጨኝ። ነደደኝ። አንገበገበኝ። ቢቸግረኝ እንዲህ አልሁ።

ዋ ኢትዮጵያ የኔ ሞንዳላ፤ የኔ ዠርጋዳ፤ የኔ ሽቅርቅር፤ የኔ ድሙንሙን *(ሽሙንሙን)* አንቺን የመሰለ ቅድስት ቅዱሳን የሆነች አገር እንዴት፤ ያለ ባሕር ትኑር፦ ዱሮ እኮ ባሕር ነበረሽ ምን ይታወቃል። ወይም ወደፊት ይኖርሽ ይሆናል። ተፈጥሮሽን ሙሉ ያደረገ ፈጣሪ መጪውን ዕድልሽን ሳያቃናውና የቀድሞ አቀማመጥሽን ሳያስተካክለው እንዴት ይቀራል? ተስፋ አለን። ለተስፋችንም ጊዜ አለው። በጊዜያችንም የዕድል ጽዋችንን እጀታ ሳንጨብጠው አንቀርም። ይኸውም በአሁኑ መሪያችን የሚፈጸም መሆኑን አንጠራጠረውም። ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለም።

ያልተማረ ሕዝብ ባሕሩ በሰፊ መሬት ላይ ተዘርግቶና ሰማይ መስሎ ሲያየው እንዲያው ለከንቱ ተፈጥሮ አገር ያጠበበ ይመስለዋል እንጂ፤ የኤኰኖሚ መተንፈሻ ሳንባ መሆኑን አያውቅም።

እውነት ነው። በምን ይወቀው? ማወቅ እኮ ያስፈልገዋል። ከእናቱ ማኅፀን ከወጣ ጀምሮ፤ ወደ መሬት ማኅፀን እስኪገባ ድረስ፤ ያየው ጥበብ ሳይኖርና ሳይማር አላወቀ ተብሎ አይፈረድበትም።

እኔም እንኳን ብሆን ገና ልማር ልማር በማለት ላይ ነው እንጂ ያለሁት፤ ገና ከዚህ ቀደም ያልረገጥሁት ባሕርና አሁንም ይህቺ የቆምሁባት መሬት ብትሆን፤ የምን ዓይነት ጥበብ መዝገብ የስንት ዓይነት ማዕድን ሣጥን የስንት ዓይነት ፍልስፍና መቃብር እንደሆነች ለማወቅ አልችልም።

ስለዚህ አሁን እኔ የማውቀው፤ ማናቸውንም ነገር አለማወቄን ብቻ ነው። ይህም ከዕውቀት ሳይቆጠርልኝ አይቀርም። አለማወቁን የሚያውቅ፤ ያላወቀውን ለማወቅ ጾጸት የሚያድርበት ነው።

የባሕር ባለሥልጣን የሆነ መንግሥት የደረጀና ችግሮቹን ድል ነሥቶ የተራመደ መሆኑን ገና በመርከብ ስሳፈር ለመረዳት በመቻሌ ከተማርሁት አብጬ ትምህርት ያገኘሁ መሰለኝ።

ከቶውንም መርከቡ እንደምን ባለ ጥበብ እንደ ተሠራና ያን ያህል ግሥንግሥና ክብደቱ ስንት ኪሎ ወይም ስንት ቶን እንደሆነ ሊገመት የማይቻል ጭነት ተሸክሞ አስጣሚ የሆነውን የባሕሩን ተጫኝነትና አስፈሪነት፤ ወደታች ረግጦ ሲንሳፈፍ በማየቴና እኔም ለሸክሙ ተጨማሪ ሁኜ መገኘቴን በመመልከቴ ዋ ያገሬ ሰው፤ እንደዚህ ያለ ሥራ ሳይማር የኖረ እግዚአብሔር ራሱ እንደ ኖኅ ቃል በቃል እየነገረ መርከብ ያሠራኛል ብሎ በመጠባበቅ ይሆን? የማለት ፀፀት ያብተከትከኝ ጀመር።

ጭንቅላቴም ሆነ ፀፀቴ ደግነቱ ዙሮ ዙሮ ተስፋ አይቆርጥም። ጐኔን ሲዳብሰው ተስፋን በጐኔ አጥንቶች መካከል ተሸጦ ያገኘዋል። የአንድ ሰው ብርታትና ትግል ትዝ ሳይለውና የተባለው ሁሉ እንደሚፈጸም እርግጠኛ ስሜት ሳይገጥመው አያልፍም።

ከቶውንም አንዳንድ ጊዜ፤ ከአንጐል የፈለቀ አንዳንድ ትኩስ አሳብ ሲመጣብኝ እንደተፈጸመ እንጂ ገና እንደሚፈጸም አይታየኝም ነበር። አንጐል ነቢይ ነው። መጪ ነገር ይታየዋል በማለት እጽናናለሁ።

ባሕራችን በዙሪያችን እንደ ተዘረጋ ይገኛል። ከተፈጥሮው አልተናወጠም። ኢትዮጵያነቱንም አልለወጠም። በግፍ የያዙትን ገዥዎች እግዚአብሔር በቃችሁ ሲላቸው አንድ ቀን ጠፊዎች ስለሆኑ፤ ባሕራችን፥ በእጃችን ይገባል። ይህም እርግጥ ነው። በእርግጥም እውነት ነው። ነገር ግን መማርያው አሁን ነው። ኋላ ባሕሩ ሲገኝ፤ የሠለጠኑ ሠራተኞችና መርከበኞች መሰናጃው አሁን መሆኑን የሰኔ

Join us on Telegram @amharicbookss

በጋ አናድርገው፤ እያልሁ ከአሳቤ ጋር ስወቃቀስ አሳቤ ንግግሬን ካፌ ቀበል ወይም ቀለብ አድርጎ እውነትህን ነው ካለኝ በኋላ

«አንዲት ጣት ዝንብ አትይዝም» የሚባል የሊቅ ንግግር አለ። አንተ ላንተው ብታወራ ምን ይሆናል? ይልቅስ መንገዳችንን እንቀጥል ብሎ ትንሽ አደብ ሰጠኝ።

እኔም ሰው ከተጸጸተና ባመለጠው ነገር ከተቆጨ ካልደረሰበት ለመድረስ መሮጡ አይቀርም በማለት አሳቤን አሳርፌ ወደ ጉዞዬ ውዝዋዜና ወደ ባሕሩ ምግባረ ተፈጥሮ አስተያየቴ ተመልሼ በባሕር ላይ ባለው ሁናቴ እገረም ጀመር።

መርከቦቹ የውሀ እናት አበባዎች መስለው ከባሕሩ ማዕበል ጋር እየተፈካከሩና እየተገራመሙ፤ እየተጣለቁና እየተዳፈቁ በትግል ላይ ሁነው ሲታዩ ያስገርማሉ። አንዳንድም ጊዜ ማዕበሉ ወደላይ ደንገላሳ እየተነሣ፤ በመርከቦቹ ላይ ሲቾለስና መርከቦቹ በማዕበሉ ዳልጋ ተሸፍነው ወደ ጥልቁ ሲወርዱ ወይም ሰጥመው ቀሩ ሲባል፤ ተመልሰው በባሕሩ ጀርባ ላይ እንደገና ሲታዘሉ ግሩም ኃይለ እግዚአብሔር ያሰኛል። ይህንም ሁሉ አድራጊ ሰው ስለሆነ ከሰው ሰው ሰንፎ ሲገኝ ሰው መባሉን የተገፈፈ መሆኑን ያስረዳል።

ዓለም ዓላረፈም። የምድሩ ወይም የባሕሩ መንገድ አልበቃውም። ሰምዩንም የውሀ መንገድ ስላደረገው ወደ ሰማይም ቀና ብሎ በማየት ከአስገራሚዎቹ ፩ዱ ሊገኝበት ይችላል።

አኤሮፕላኖቹ የአይር ዋንተኞች ሆነው የነፋሱን ማዕበል ዕይቀዘፉና እንደ ሰንጋ ፈረስ ካፍንጫቸው በሚወጣው የአየር ቡልቅታ፤ ኃይለ ነፋሳትን እያራገቡ ሲበሩ በየመስኮቶቹ ብቅ ብሎ መመልከት ካንድ ዩኒቬርስቲ ገብቶ በሊቅነት ትምህርት ላይ እንደተገኙ ያህል ይታሰባል።

ከላይ እንደተጠቀሰው በባሕርም ሆነ በአየር መሔድ የሚያስገኘው ጥቅም የሩቁን በማቅረብ ብቻ ሳይሆን። በማየት በኩል የሚሰጠው ጥቅም ከፍ ያለ ስለሆነ፤ ከሰውና ከእንስሳት፤ እንዲሁም ከልዩ ልዩ አራዊት በተለየ ተፈጥሮ አክናፈ አግኝተው ከነዚህ ከተቆጠሩት በምድር ላይ ብቻ ተራማጆች ከሆኑት ፍጥረታት፤ በላይ በሰማይ ለመብረር ችሎታ ያላቸው አዕዋፍና አንሥርት የሰው ልጅ የሠራቸው አክናፈ አገራቸውን ሲወርሱት እንዴት ይገርማቸው?

Join us on Telegram @amharicbookss

ነፉሱስ ቢሆን በተፈጥሮ ሕጉ ውስጥ የሌለ ሸክም በጀርባው ላይ ተጭኖ የጥበብ አጋሰስ ሆኖ ለኰቴው መርገጫ በሌለው በአየር ሜዳ ላይ፤ እየታገለ ሰማይ ለሰማይ ሲንጋፈፍ እንዴት ይደንቀው? ለሰው ልጅ ጥበብ፤ ባሕርም ነፋስም ታዛዥ በሆኑበት ጊዜ ማነው ተኝቶ የሚያንኮራፉ። ?

ከመርከብም ከአእሮፕላንም ወርደህ መሬት ስትረግጥ በየወደቦች የሚቆዩህ ቤቶችና ሆስፒታሎች፤ ሆቴሎችና የመናፈሻ ገነቶች፤ አብያተ ክርሲያናት ቤተ መስጊዶች መሥሪያ ቤቶችና ልዩ ልዩ ሥራዎች፤ የሲኒማ ቤቶችና የመጻሕፍት መደብሮች ድንቅና ብርቅ ስለሚሆኑብህ ከማናቸው ማናቸውን ለማማረጥ ችግር ይገጥምሃል።

ከዚህ ተነሥተህ ካሰብኸው አገር እስክትደርስ፤ ምድር ያፈራቻቸው የሥልጣኔ ሥራዎች ለእንግድነትህ የደስታ መስተንግዶና መተያያ ሲቀርቡልህና የሚታዩት ነገሮች ሁሉ እየን እየን እያሉ በዚያም በዚያም በውበታቸው ሲጠቅሱህ፤ ደስታ ተወልዶ ያደገው ከዚያው መሆኑን ልታውቅ ትችላለህ። ከቶ ስንቱንስ አይተህ በየትኛው ለመደነቅ ዓይነ አዋጅ ይሆንብሃል።

በባሕሮችና በተራራዎች ለጥ ባሉት ከተማዎችና ሜዳዎች የሚታየው ነገር ሁሉ ያስጐመጃል። ሲያዩት ከቶ አይሰለችም። ተክሎችና አበባዎች ዛፎች ፍሬዎች፤ ሥዕሎችና ቅርጾች፤ በብዙ ዓይነት ቋንቋ የታተሙ ጋዜጣዎችና ልዩ ልዩ የሆኑ መጻሕፍት፤ ፋብሪካዎችና ማዕድኖች መንገዶችና፤ በላያቸው ላይ የሚሽከረከሩ መኪናዎች፤ በየሱቁ የሚታዩት ዕቃዎችና የውበት መደብሮች ሁሉ ሲያዩዋቸው የሰው እጅ ያልዳሰሳቸው ይመስላሉ።

ከንበል ፈሰስ ያድርገኝ። ሰው እኮ ነው ይህን ሁሉ የሠራው። ከሠሩና ከተሠሩ አይቀር እንግሀ ይሠሯል። ከተማሩና ካስተማሩ አይቀር እንዲህ ይማሯል፤ ያስተምሯል። ምን አልባት ገና ከሥልጣኔ ያልደረሰህ የዕውቀት እንግዳ ብትሆን እንኳ ቅሉ፤ ቶሎ ለመድረስ ስሜት ሕሊናህን ያገሠግሠዋል። ያራውጠዋል። ያስተፈትፈዋል። ትምህርት ሁል ጊዜ የሚያፈራ የወይን ሐረግ ነው። ሁል ጊዜ የማይጠወልግ የወንዝ አረንጓዴ ነው። ከሱ በቀር የከበረና የሚያከብር የለም። ከሱ በቀር ሰው የሚያደርግና የሚያሰለጥን አይገኝም። ይህንም ከመረዳት የተነሣ ዓለም በሱ ላይ ዓይኑን ጥሏል። በዓይኑም ላይ ድንቁርና የጣለበት ሁሉ ዓይን አብሪነቱን ይፈልጋል።

Join us on Telegram @amharicbookss

እንደዚህ ያለውን የብልሆችንና የትጉሆችን ኑሮ ሲያዩት መፈጠርን ያስመሰግናል። ባንድ ወገን ደግሞ የሰነፎችንና የንዝህላሎችን ሁናቴ ሲመለከቱት ተፈጥሮን ያስጠላል።

በውነቱ ሞት ላይቀር በትጋት ሠርቶ በሠሩት ደስ ተሰኝቶ ቢሞቱ ጽድቅ እንጂ ሞት አይባልም። ሳይሠሩና ከሥራ በተገኘው ሙሉ ሀብት ሳይደሰቱ፤ በሥንፍና ተጀጉሎና ተቆራምዶ በድንቁርና ታጅሎና የውርደት አናኵዕ ሁኖ ቢሞቱ ግን፤ ጉዞው ከሞት ወደ ሞት የታወቀ ነው ያሰኛል። ከዕድል ሁሉ ክፉውን ደኅባና ሥልጣኔ እርሙ ሆኖ መቅረት ነው።

ታሪክን ሲተርኩ፤ ምሳሌን ሲመስሉ መኖር ብቻ ጥቅም የለውም። መተረቻ ሁኖ ከመቅረትና ተራች ሁኖ ከመኖር ይልቅ አድራጊና ፈጣሪ መሆን ይበልጣል።

እንጅ ያለው ቀርቶ አፍ ያለው ያግባሽ የሚባልበት ጊዜ አልፏል። ብረት ሠርቶ ጠቢብ መባል አስፈልጓል። ከጐረቤት ከቶውንም ከባላንጣ ጋር ጐን ለጐን እንጂ ላይና ታች ሆኖ መገኘት አስጠቂ ሆኖ ተገኝቷል። ባላንጣ በሰማይ ሲመጣ በሰማይ ላይ ጠብቆ ካልተከላከሉት ምድር ከሰማይ ጋር ተዋግተው ድልን አያገኝም።

የባሕሩም ትግል እንደዚሁ ነው። ጠላትን ሲያሸንፉ ከባሕርም ላይ ነው እንጂ ከምድር ብቻ አይደለም። ምድሩን ለቅቆ በባሕር ላይ ሁኖ ልዋጋ ሲል በባሕር ፈረስ ካልተከላከሉት፤ ተመልሶ ምድራችሁን ልቀቁ መብታችሁን ተነጠቁ ማለት አይቀርም።

የዚህም መድኃኒቱ ያው የምድሩን በምድር የሰማዩን በሰማይ የባሕሩን በባሕር ለመከላከል የሚያስፈልገው ድርጅት ነው። ይህም ለሰማዩ አኤሮፕላኖች፤ ለባሕሩም መርከቦች ያስፈልጉታል ማለት ነው።

እህሳ ይህን ማነው የሚሰራው። ጠቢብ ጠቢብንስ ማነው የሚፈጥረው።? የትምህርት ቤት።?

የትምህርት ቤትንስ ማነው የሚመሠርተው።? ለሀገሩ አሳቢና ተቆርቋሪ የሆነ ታላቅ መሪ ነዋ። እንዲህ ያለውንስ መሪ ማነው የሚረዳው። ፈጣሪ።

Join us on Telegram @amharicbookss

በዚህ መሠረት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሕዝባቸው ዓይን እንዲከፈትና የአእምሮው ዓይነ ሞራ እንዲገፈፍ፤ ዓይን አብራ የሆነውን ትምህርት ከሕፃናት ጋር ስለ አስተዋወቁት ወጣቶቻችን ተምረው በዕውቀት አብበው፤ ሥልጣኔን አፍርተው፤ ከፍ ያለውን አገልግሎት የሚያበረክትበት ጊዜ ደርሷል።

ዋ ቀደም ብሎ ተጀምሮማ ቢሆን ይህን ጊዜ ከምን በተደረሰ ነበር።? ሽማግሌ ሆኖ የልጅ ጠባይ፤ ልጅ ሆኖ የሽማግሌ ባሕርይ ያለው ስለማይታጣ፤ ወጣት የምንለው የአእምሮ ነው እንጂ የዕድሜ አይደለም።

በኤውሮፓ የመንግሥቱን ፖለቲካ በትክክል የሚያስኬዱት አብዛኛዎቹ የአእምሮ ጉልምስናና የዕውቀት ልግስና ያላቸው ሽማግሌዎች ናቸው።

ኢትዮጵያ ለዘር ዘራችን ሁና ለመርኖር የምትችለው ከዚህ ቀደም ተምረው ዓዋቂዎች በሆኑትና፤ ወደፊትም በትምህርት በሚገኘው ዕውቀት ጐልምሰው፤ በአገልግሎት ላይ ይገኙ ዘንድ አዲስ ዕድል በሚጠብቃቸው ወጣቶች ነው። ከዚያ በኋላ ታስባለች እንጂ አትታሰብም። ታሠጋለች እንጂ አትሰጋም። ማን ደፍሯት

ሁለተኛ ክፍል።

ልሒድ አትሔድም።

በላይኛው ምዕራፍ እንደ ተመለከተው ከኢትዮጵያ ወጣቶች አንዱ እኔ «አግዓዚ በበኩሌ የዚህ ዕድል ተካፋይ ለመሆን እመኝ ጀመር። ምኞቴም የሚፈጸም መሆኑን ተረዳሁና ለሀገሬ ብፅዓት ገባሁላት። ተምሬ ከዕውቀቴ ፍሬ፤ ለውዲቱ አገሬ ለማካፈልና ንጉሠ ነገሥቴን በቅን ለማገልገል፤ አሳቤን ወጣት አደረግሁት። ለዚሁም አደፋፋሪ መንፈስ የሚገኝበት ብልህት ከትምህርት ለማግኘት ከመንግሥቴ ፈቃድ ጠይቄና እርዳታ ተደርጎልኝ ፲፱፻፳፩ ዓ.ም ገና ሰላም ሳይታመም በመካከለኛ ሕይወት ሳለ፤ ራሴንና ወገቤን እያለ ሲንቆላበስና ብርድ ብርድ ሲለው፤ ወይም ሲያተኩሰውና እንደ ማሰል ሲለው፤ ወደ ሌላ አገር እሔድ ዘንድ መንገደኛነቴ መረጋገጡን ለዘመዶቼ ባስታውቃቸው ከቶ ምንም ቢሆን አትሄድም ብለው ከጫማዬ ላይ ወደቁ። አለቀሱ። ተንሰቀሰቁ። እኔም ያ ልማድ አሁንም አልቀረም። እስከመቼ ድረስ እንዳስቸገረ ይኖራል።ስ አይማሩ

Join us on Telegram @amharicbookss

ማወቅ አይገኝም። አዋቂም ካልሆኑ እንደ ተናቁና እንደ ተጠቁ መኖር የሚቀር አይደለም «ተራራ ወደ ሰው ይመጣ ዘንድ ባይችል ሰው ወደ ተራራ ሔደ» እንደሚባል ትምህርት ወደው ወጣት በገዛ እግሩ ይመጣ ዘንድ ስለማይችል ወጣት ወደ፤ ትምህርት ሔዶ መማር አለበት። ይህንን የናንተን አሳብ የመሰለ ጥንታዊ ልማድ በወጣቶች አሳብ ፊት እየተደነቀ ፀሐይ ከልካይ ሲሆን ዓለም በጨለማ ተዋጠ ማለት ነዋ።

የነገው ትግል፤ በነገው ትውልድ እጅግ አስቸጋሪ ሳይሆንበት አለመቅረቱ አውቆ የነገውን ትግል ችግር ለማስወገድ የዛሬ ትውልድ የአእምሮ ኃይል ማግኘት አለበት። አእምሮው ደካማ የሆነ ሕዝብ የትኛውም ጉልበቱ ቢሆን ብርታት ሊያገኝ አይችልም።

ትምህርት ቢሏችሁ የአዳምን ሚስት ሔዋንን ከጥፋት ያደረሰ የበለስ ቅጠል አይምሰላችሁ። ወይም ደግሞ የሎጥን ሚስት ደንጊያ አድርጎ ያስቀረ፤ ፋይዳ የሌለው ስሜት አይደለም። ምናልባት ፊተኞች፤ ኋለኞች ይሆናሉ የተባለውን አልተማርኸውምና ምን ታደርግ እንዳትሉኝ እንጂ፤ ከኢትዮጵያ በኋላ የተነሣው ዓለም ትላንትና ተወልዶ ኢትዮጵያን ቀድሟት ሲራመድ፤ እንዴት አይቆጨንም። በሀገራችን የማይንቀሳቀስ ሸክም የምንሆንበት ስለ ምን ነው። እንኳንስ ፊደሉ እንኳንስ ፊደሉ፤ እንኳንስ በምድር ያለው ጥበብ ሁሉ የሰማይ ዘሎ ባይኔ የሆነው ኮከብ ተማሩኝ፤ መርምሩኝ ዕወቁኝ ብሏል። ዕውቀትም ቢሏችሁ እንደዚያች እንደ ስንዴ ቅንጣት ምድር ጫር ጫር፤ አፈር ለበስ ለበስ አድርጎ መተው ብቻ አይምስላችሁ። ሲያንስ የሚባል ነገር መጥቶ ጉድ አፍልቷልና ባይሆን ሳይበዛ በጥቂቱ ተመራማሪ መሆን የግድ ያስፈልጋል። «ቢከማች ዕዳው ካንቺ እንደሚባለው እናንተ ሳትማሩ እንደቀራችሁ እኔም ሳልማር ብቀር፤ ይህ ስንፍና ተጠራቅሞና ተከማችቶ የሚጐዳው አገርን ነው።

አሁንስ ባያችሁና ብመለከታችሁ «የላሊበላ ልጅ ብላ በለኝ እንዳባቴ በቆረጠኝ» አለ እንደሚባለው፤ ኑሩ ባለንስ በዚያው በዱሮው አኳኋን ባቄየን በተሻለን ነበር የሚል አሳብ ያለባችሁ መሰለኝ። ይህን የመሰለው ልማድ ተረድ መስሎ ታይቷል።

አዲስ ሕይወት ለመጀመር የተሰናዳሁ ሆኜ ሳለሁ ይህን ወጣት አሳቤን በከንቱ አታስቀሩት። በዚህ ነገር ኀዘን አይግባችሁ። ማልቀስ ሳይማር ለቀረ ሰው ብቻ ነው።

Join us on Telegram @amharicbookss

ዓይናችሁ ሲያለቅስ ዝም አትልም ዓይኔ

ለራሳችሁ እንጂ አታልቅሱ ለኔ።

አሁን ከናንተ ጋር አልቅሼ ብቀር

ኋላ ያገኘኛል የባሰ ነገር።

ምን ቢሆን አይገኝም ሳይማሩ ማወቅ

የሕልም ሩጫ ነው በከንቱ ልብ ውልቅ።

እያልሁ ይህን የመሰለውን ማስረጃ ባቀርብላቸው እነሱም ይህን ካደመጡ በኋላ።

ዋ የልጅ ነገር፤ ቋንቋ ቢያበዙት ፍሬ የለውም። አፈኛ ያሰኛል። ብረት ቢቀጠቅጡ ጠይብ፤ ሸማ ቢሠሩ ቍጢት በጣሽ ሌላው ይቅርና ግብርና እንኳ አፈር፤ ገፊ ብሎ ያሰድባል። ሌላውንም የእጅ ብልሃት ቢያውቁት ስድብ አይቀርም። ከአባታችን ልማድ የተረፈ አዲስ ባሕል ማምጣት፤ ዘርን ለማሰደብ ነው። ልጄ እንደ ዱሮአችን እንኑር። እንደ ቀድሞአችን እንደር። ሰው እንደ ቤቱ እንጂ እንደ ጐረቤቱ አይኖርም።

ይልቁንም የአንተ አሳብ የፈረንጅ ጽሕፈትና ትምህርት ለመማር ስለሆነ ይህ ይቅርብህ። ዛሬ ቀረ እንጂ ዱሮ ስንኳን የፈረንጅና የአበሻም ጽሕፈት የሚጽፍ ቢሆን ጠንቋይ ይባል ነበር የሰው አገር ትምህርት ሃይማኖት ያስለውጣል። ምግባር ያናውጣል። ከቶውንም ልብሳችሁን ጥላችሁ ሂዱ ያሰኛል።

የፈረንጅ ትምህርት አወቅን ብለው ራቁታቸውን የሚሔዱትን ጢማቸውን የሚላጩትንና ትምባሆ የሚያጤሱትን እነገሌን እነገሌን አታያቸውምን። አሁን ራቁት ሔዱና የነሱ ዕውቀት ዕውቀት መሆኑ ነው?።

በደጅ ከተበተነ አዝመራ

በእጅ የተጨበጠ ሽንብራ

Join us on Telegram @amharicbookss

ይበልጣል መባሉን አልሰማህ ይሆን? ዝንጀሮ እንኳ ባቅሟ ተጂ፤ በጉንጮ፤ ያለችውን እንደምን ትዘነጋዋለህ? ዳሩ ግን የትላንት ማሙዬ ምን ጊዜ ታውቀዋለህ።

ስለዚህ በውጭ አገር ከተገኘው ትምህርት እዚሁ ያለው የዱሮው ልማድ ይሻላል። ይህን ያህል ዕሩቅ የሚያሳስብህ ለየትኛው ነገር ነው። ይህ ዓለም እንደሆነ ቢማሩም ባይማሩም ቢያቁም ባያውቁም ያው ነው። ሞት ላይቀር ምን ያደክማል።

እኛ የምንፈራው ራሷን ሹርባ ልትሠራ ሄዳ፤ ጠጉሯን ተነጭታ መጣች የተባለው ብጤ እንዳይደርስብህ ነው እንጂ ለሌላው አይደለም፡

ባይሆን እንኳ ልማር ካልህ እዚሁ ፊደልን፤ አቡጊዳን ፊደለ ሐዋርያን ገበተሐዋርያን፤ ዳዊትን፤ ተንሥኡን፤ ጸልዩን፤ ሰዓታቱን፤ ግፋም ቢል ዜማንና ቅኔን፤ ዝማሜንና መረግድን፤ የመጻሕፍትን ትርጓሜ፤ ይህን የመሰለውን መማርና በዚያ ላይ እርሻን መጨመር ነው እንጂ፤ ወደ ውጭ አገር ሒደህ፤ የውጭ አገር ትምህርት መማር ሌላ አመል ጨምሮ ከመምጣት በተቀር ምን ይረባሃል?።

የኋላ ልጅጆች የማታመጡት የለምና ነው እንጂ ከዚህ ቀደም ዳዊት ደግመህ የምሥራችህን ደግሰን በተደሰትህና ስለ ደስ ደሱ የምሥራችህን በሰጠንህ ጊዜ ትምህርትህን የጨረሰህ መስሎን ነበር። በእውነትም ከዳዊት ድጋም ወዲያ ያለው ትምህርት እንዲያው ጉንጭ አልፋ ነው።

ይሁን እንጂ ግፋም ቢል፤ ከዳዊትም በላይ ትምህርት ቢኖር ለቅኔ ወደ ጐጃም ለዜማ ወደ ቤተ ልሔም ላቋቋምና ለመጽሐፍ ወደ ጎንደር ለዝማሬና ለመዋሥዕት ወደ ዙር አምባ ለቅዳሴ ወደ ሰለልኩላና ወደ ደብረ ዓባይ ሒደህ ለእድልህ አጋጣሚ የሆነውን ትምህርት ተምረህ፤ ዲያቆን ከዚያም በኋላ ቄስ የደብር አለቃ፤ የገጠር መሪ ጌታ ወይም ደብተራ ከዚህም ጋር እርሻና ንግድ ደብለቅ አድርገህ ሁለቱን መስቀል ተሰላጢን አጣምረህ በዳዊት አደጋገምና በጋሻ አመካከት በጦር አወጋግና በፈረስ አኰራኮር የተመሰገንህ ሁነህ መኖር ነው። ይህን ዓለም እንዲህ ባጭሩ ካልተገላሉት በሩቅ መመኘት በቅርቡ (ባጭሩ) ያስቀራል።

Join us on Telegram @amharicbookss

ይህም ቢቀር ለጌታ አድረህ፤ ከቶውንም የንጉሥ አሽከር ሁነህ፤ አቃ ሻቃ፤ ብላታ፤ ብላቴን፤ ጌታ፤ ሊቀ መኳስ፤ አፈ ንጉሥ፤ ቢትወደድ፤ ወይም ባላምባራስ፤ ግራዝማች፤ ቀኛዝማች፤ ፊታውራሪ፤ ደጃዝማች፤ ራስ፤ በወታደርነትም፤ በኩል በአዲስ ስመ ማዕርግ ያ፲ አለቃ፤ የ፷፭፤ የ፶፤ የ፻ አለቃ፤ ሻምበል፤ ሻለቃ፤ ኰሎኔል፤ ጄኔራል፤ እነዚህን የተቆጠሩትን የሹመት ስሞች በየተራ ለማግኘት ደጅ መጥናት በቅን ማገልገል ሞትን ሣይፈሩ በታዘዙበት ሥፍራ አስደናቂ ሥራ መሥራት ነው እንጂ፤ ይህን ትቶ ውጭ ለውጭ መሮጥ ትርፉ መታከት ብቻ እንጂ ሌላ ምንድን ነው።

አገሩ ደብረ ብርሃን ታቦቱ ሥላሴ፤

ዳዊት ጨርሶ ገብቷል እቅዳሴ።

ባያቱ ሽዬ ነው ባባቱ ጎንደሬ፤

መዝገብ ድጓ ዘልቆ ገብቷል እዝማሬ

ብሎ የሚዘፈንለት ደቀ መዝሙር እንዴት ያለ ክብር ያለው መሆኑን ማን በነገረህ? ዋ እንዲያው እንታክታለን እንጂ አንተ እንደ ሆንህ ያው አንድ ልብ ነህ።

ዳዊት ደጋሚ ከዕንጨት ዕንጨቱ

መወድስ ቋሚ ከነሳታቱ

ቅኔ ፈረሱ ድጓ በጉንጩ

መጽሐፍ ተርጓሚ ተነጐመጬ።

መጽሐፍ ተርጓሚ ተነጐመጬ።

እያለ ያገራችን ምሁር ሲፈክር፤ እንዴት ያስቀናል? ይኸውም ልህ የተማሪ ልብ የሚያስብ ወደ ጐንጅ፤ ትምህርት ግን ያለው በደጅ የተባለው ምሳሌ እንዳይደርስብህ ማስረጃውን ሰጠንህ። ምን አልባት አሳብህና ክጃሎትህ፤ ይህን አይቼ መጣሁ፤ እያልህ እኛን ለማስጐምጀትና፤አፈ ሰፊ

Join us on Telegram @amharicbookss

ሁነህ ወሬ ለመንዛት ብቻ እንደሆነ ለወሬ የለው ፍሬ፤ የተባለው ምሳሌ ከመሔድህ በፊት ደኅና አድርገህ ማወቅ አለብህ።

በእንደዚህ ያለው ነገር ከዚህ ቀደም ወደ ውጭ አገር ሒደን ነበር ያሉ ሁሉ አሰልችተውናል። በቃላቸው የሚናገሩትን በሥራ ላይ ማዋል እያቃታቸው፤ አፍና ሥራ አንገናኝ ብለው አስቸግረዋል። ይልቁንም እዚሁ በዚሁ የተማሩት ሳይሻሉ አልቀሩም። ይህንም የምንልህ ልብህ ልብ እንዲገዛ ብለን ነው።

ይኸውልህ ዐውቀህ ግባበት። የዛሬውን ትውልድ ወሬ አሰልችቶታል። ይህ ትውልድ፤ የሚጨበጥ ነገር ፈልጓል። እኛም እንደ ዱሮዎቻችን እንኑር የምንልህ፤ የረባ ነገር ይዘህ ላትመጣ ምን አታከተህ ሰላማለት ነው። አንድ ተአምራት ይዘህ መጥተህ ዓይን አብራ ብትሆን ግን የሚጠላ የለም። ምናልባት ማለት ታላቅ ዘዴ ነው። በቤታችን እንኳ ከዚህ ቀደም እንደዚህ ያለ አሳብ ያለው አልነበረም። የውጭ አገር ቢሉህ እንዲህ ቅርብ መሰለህ። እረ ቢጠሩት አይሰማም። እረ የት እየለሌ ነው እያሉ በዚህም በዚያም ሲያዋክቡኝ፤ ጣዲቄ የሚባሉት አክስቴ ከምጣድ ላይ ተነሥተው ከምጣድ ላይ ያፈሰሱትን ሊጥ ሳይከድኑት እጃቸውንም ሳይለቃለቁት፤ መሰቅሰቂያቸውን ይዘው እሳት ለብሰው፤ እሳት ጐርሰው እየሮጡ መጥተው ምን ታንቆሻብሉታላችሁ። በል አትመለስም። የባሕር አገር ቢሾፍቱ መስሎታልን። ብለው በያዙት ለመምታት እጃቸውን ዘርግተው ከንፈራቸውን ነክሰው ዘልለው ሊቆለሉብኝ ቃጡ።

እኔም ሁሉንም ተውሁትና አክስቴ እንዲህ የሚሉኝ እንዲህ ያው ሳልማር የመንደር አውደልዳይና ገልዋዳ ሴት አውል ሆኜ

አክስቴ ቤት

አለኝ ለከት

እያልሁ የሕፃንነት ዕድሜዬን ለኸት አሳጥቶ በማዘጥዘጥ ያሳልፈው ብለው ነው? ምነው ለቁጣ ቸኰሉ። ምነው ትዕግሥት አጡ። እንዲያው ዕውር ሁኜ እንድኖር ይፈልጋሉን።

Join us on Telegram @amharicbookss

መውለጃው ሳይኖር ልጅ ልውለድ ብሎ የሚያስብ እንዴት ያለ ጃንደረባ ነው። እህሳ ልብ ነው እንጂ ጃንደረባ የሆነው አባለ ዘሩ አይደለም።

ያለ ትምህርት በታሪክ ፊት የከበረ ሕዝብ እሆናለሁ ብሎ መመኘት ከዚህ ያላነሰ ሞኝነት ነው። በሆነማ በማን ዕድል ሳይገድሉ ጐፈሬ ሳይማሩ ቅኔ የተባለውን ምሳሌ ምነው የሚያው ታጣ። የእኔን አንጀት አሳርራለሁ ሲሉ እንጀራው በምጣዱ ላይ እንዳያር መሰቅሰቂያዎን ይዘው ይመለሱ። እኔ እንደሆንሁ ቆርጫለሁ አልኋቸውና ተመለሱ።

በዚህ ጊዜ እኔን ያዋልለኝና ወላላይቱ እናቴ ያዳንቂሽ አይ ወዲያ። ምነው። ልጅን እንዲያው ማባበልና መለማመጥ ነው። እምቢም ቢል አንገቱን አቅፎ፤ ጉንጩን ስሞ ጸሎተ እግዝእትነ ማርያምን ደግሞ፤ ስንቅ ሰጥቶ በደኅና አድርሶ፤ ደኅና ይመልስህ ይቅናህ፤ ትምህርቱን ይግለጥልህ፤ ለምለም ሣር አያንቅፍህ መንገድህን እንደ ሸማ ይጠቅልልህ፤ ብሎ መርቆ፤ ማሰናበት ነው እንጂ ቀልብ ማሳጣትና ማገጣበር አይገባም ብላ አንገቴን ተጠምጥማ ይዛ እያለቀሰች፤ ልጄ በአንጀቴ፤ በጡቴ ስሞት ስቀብር፤ አፈር ስሆን በአንቀልባህ አትሒድብኝ አትራቅብኝ፤ አብረን እንኑር አብረን እንቀበር፤ መቃብርህ ከመቃብሬ አስከሬንህ ከአከሬኔ አይለይ እያለች በርኅራኄዋና በእናትነቷ ፍቅር መንፈሴን ለመስበር ትለማመጠኝ ጀመር።

ከእነዚህ ላይ እኔንም ጨነቀኝ በእውነትም የእናቴ ፍቅር መንፈሴን እንክትክት አድርጎ ሰባበረው። እንቅሽቅሽ አደረገው አሣቤንም መሔጃ አሳጣው። አንገቷን በአንገቴ አስደግፋ ያነባችው ዕንባ በደረቴ ላይ ተንዠቀዥቆ ወርዶ መሬቱን አራሰው። የእኔም ዕንባ ተጨማሪ ሆኖ አብሮ እየጐረፈ ርኅራኄዋና ርኅራኄየ የሁለታችንንም መንፈስ እምሽክ ስላደረገው ለመላቀቅ አስቸጋሪና አስጨናቂ በሆነ ግዴታ ላይ ጣለን።

በእንደዚህ ያለ ጭንቅ ላይ ሳለን፤ አባቴ አቶ አደገኛና አጐቴ አቶ ነውጠኛ መጡ። አባቴ ልቡ በልዩ ኀዘን ስለተነካ ዝም ብሎ ቆመ። አጐቴ ግን እንደዚህ ሲል ምክሩን ቀጠለ። ዛሬ የዓለም ወሬ ደስ አያሰኝም። በዓለም አደጋ የሚደርስበት ይመስላል። የሁሉም ልብ ተነሥቷል አኰፍኵፉዋል። ያበጠው ሳይፈርጥና መንግሥታት ሳይናወጡ፤ ባሕሩ ሳይታወክና ሰላም ሳይደፈርስ የሕዝቦች ደም ሳይፋሰስና አጥንት ለአጥንት ሳይከሳከስ የሚቀር አይመስልም።

Join us on Telegram @amharicbookss

እንዲያውም በመላ ስንገምተው፤ ዛሬ ወደ ውስጥ የሚሰበሰቡበት እንጂ፤ ወደ ውጭ የሚወጡበት ጊዜ አይደለም።

ምንም ቢሆን ልጅ ያቦካው ከምጣድ አይወጣምና፤ የእኛ ምክር ይሻላል። ትምህርት ክፉ አልነበረም። ነገር ግን በእንደዚህ ያለ ጊዜ አይደለም። ልኩ ይታወቅ። ሰላም ሲረጋጋ ልትሄድ ትችላለህ። ይህን ዓለም አንተ የሥልጣኔ ዓለም ትለዋለህ እንጂ እሱስ አብዷል። ዕውቀት ሲበዛ በዕብደት ላይ ስካርን መጨመር ነው። የአሁኑ ዓለም እሾሃም በሆነ በብረት ቀፎ ውስጥ መከበቡ በምን ምክንያት መስሎሃል። ሥልጣኔው ባመጣበት በገዛ እጁ ሥራ ለመጥፋት ዳር ዳር ሲል አታየውምን። በማለት አጐቴ ላቀረበልኝ የምክር ቃል እንደሚከተለው መለስሁለት። አጐቴ ይህ ያጣ ወሬ ነው። በትምህርት በተገኘው ዕውቀት ለመተዳደር ሳልችል ቀርቼ በሰንካላ ዕድል ላይ ሆኜ ዓውደ ዓመት (ያመት በዓል) እየቆጠርሁ ሌሊት እንደ ጅብ እየሔድሁ ሰው አላስተኛ መዝጊያ እየደበደብሁ።

የኔ አጐት የሰጠኝ ሙክት

በጨለማ ነው ባለምልክት

መስከረም ጠባ ያንን ሳነክት።

ተው ስጠኝና ልሒድልህ

እንዳሮጌ ጅብ አልጩህብህ።

እይልኩ በማደሽደሽ ወርቅ ጊዜየን በከንቱ አሳልፈው ዘንድ ለምን ታስገድዱኛላችሁ። አሁን እናንተ ምኑ አምሮባችሁ ነው የእኔን ቀልብ የምትገፉት። እርግጥ ነው። ቃላችሁ የቄስ ቃል ነው። ሊጣስ አይገባም። ይሁን እንጂ በማይገባና ከሕግ በወጣ መንገድ ስትመጡብኝ ቃላችሁን መጣስ አለብኝ እያልሁ ስትከነከን።

አያቴ ወይዘሮ ሽዋዬ ባዘቶ በሰፌድ አቅርበው፤ ዝንዲ አንጥፈው ይነድፉ ነበርና ደጋናቸውን አሽቀንጥረው መታረሪያቸውን አሽትለው እየተቆናጠሩ፤ መጥተው አፈጠጡብኝ። እኔም አፈጠጥሁባቸ እንደ አክስቴ ግን ቍጣቸው የጋለ አልነበረም። ከማኅፀናቸው ከወጣው ማኅፀን

Join us on Telegram @amharicbookss

የወጣሁ ስለሆንሁ በርኅራኄ ቃል እባክህ ልጄ፤ ይህን ዕብድ ዓለም አምነህ፤ አገርህን ጥለህ ወደማታውቀው አገር ልሒድ ማለት ይቅር፤ እያሉ ስለ ለመኑኝ እኔም ረገብ ባለ ቃል አያቴ ይህን ፈርቼ ሳልማር ብቀር

የልጅ ልጅ እህል ፈጅ

በኋላም ጅብ አስፈጅ።

እያሉ ሲያላግጡብኝ ሊኖሩ አይደለምን። የርስዎ ምክር የርስዎ ቁጣ፤ ምንም አያዋጣኝም። ይልቅስ ንድፍዎን ይቀጥሉ ስል ቁርጥ ቃል ብመልስላቸው እየተገረሙ ገና ከተማሪ ቤቱ ሳትገባ መላስህ የተባ ሁኗል። ካንተ ጋራ ማ ይሚገታል? ያውልህ መንገዱ ብለውኝ ወደ ጥጣቸው ተመለሱ።

ነገር ግን አባቴ አደገኛ ለብቻው ወደኔ ጠጋ አለና ቅድም እናቱ ወይዘሮ ያዳንቁሽ እንደተናገረችው ልጃችን እንዲቀርልን በሰላም ቃል እንለምነው። እምቢም ቢል በሰላም ቃል እናሰናብተው።

ይህን ስናደርግለት የደስታው ስሜት የመንገድ ስንቅ ይሆንለታል።

ካሰበውም ከደረሰ በኋላ እኛንም አይዘነጋንም። ዓለሙ ቢያብድም፤ ቢጨምትም እንዳሻው ይሁን። አምላክ ሁን ያለው አይቀርም ቢሆንም ስለመጪው ሁናቴ ማሳሰብ አለብን። ያላሰበ፤ ተመነደበ ይባላል።

ሰማህ ልጄ በዓለም ላይ እንደሚሰማው የፈተና ሰዓት ዓለምን እጨኛ ለማድረግ፤ ሰይጣናትን አማጭ አድርጎ በያለበት መላላክ ጀምሯል ይባላል። ሁሉም ያለው በጦር ድግስ ላይ ነው። እብድ ውሻ የለከፋት የፋሽስታዊት የኢጣሊያ ዓይነ ተኩላ አላማረም። ዓለምን በቆበሯ ለውሳ አብራ ለመሞት ትፈልጋለች። ተቸናፊውን የሚያውቀው ምንም እግዚአብሔር ቢሆን፤ ጠብ ዓጫሪውን ሳናውቀው አንቀርም።

Join us on Telegram @amharicbookss

ከዚህም በላይ እንዳስረዳህ ስለ ድግሱም ያለወትሮው በጠጅ መርዘኛና ፈጥርቅ የሆነ አልኮል የበዛበት ራስ የሚያዞርና የሚፈጠፍጥ መጠጥ ሲበጠብጥ በሰፊው ይታያል። ስለዚህ ዳሱ እስኪፈርስና ዋንጫው እስኪመለስ ድረስ ከዚሁ ሁኖ ማዳመጥ ያስፈልጋል።

እንግዲህ ለዚህ ሌላ ምን ምስክር ያሻል። ጃፓን ግዴታ በመላበት ኃይልና ሕግን በማቃለል ማንቹሪያን ወረረ። ጀርመን በሕግ ላይ እየዛተ ሣር የሚባለውን አገርና ነምሳን ያዘ። ለእኛም እኮ ፋሽስት የሚተኛልን አይምሰልህ። የሚጠብቀው ጊዜ አለው። እውነት ከስታለች ከቶውንም ልትሞት ጥቂት ነው የቀራት ነፍሷም ወጥታ ልትሔድ በአፍንጫዋ ላይ ትርግ ትርግ ትላለች።

ሌላውም እኳኋን አላማረኝም። ሕግ እየላላ ሔዷል። ውል ከውሉ አፈትልኳል። ታንቲራና ዛቻ አንገት መነቅነቅና ከንፈር መንከርስ በዝቷል። ወደ ኤውሮፓ ልሒድ የምትለው ለመማር አይደለምን። አንተው እንደምትለው በምትናገረው ሁሉ እውነተኛነትህን ልንጠራጠር አንፈልግም። ሰላም ከሌለ ምን ትምህርት ተገኘ። የተማሩ እንዳልተማሩ ለመሆን አቆትመዋል። ስለዚህ እንድትሞት አንፈቅድም።

እኛም እኮ የምንነግርህ አንድ ትምህርት ነው። አጭሩን ነገር የምዘበዝብህ እንዳትሞትንና በከንቱ በሰው አገር ወድቀህ አንዳትቀርብን ነው እንጂ ብትማር ጠልተን አይደለም ብሎ የመጨረሻ ምክሩን ሰጠኝ።

በዚህ ጊዜ ከልካይ የሚባለው የዘመዶቼ ሎሌ መጥቶ በተራው ይህቺን አመንዝራ ናት ተብላ የፍቺዋን ወይም የመፈታቷን ደብዳቤ ትቀበለው ዘንድ በፍርድ ፊት የቀረበችና የደም አምቡላ መፋሰሻ የሆነች አመንዝራዊት ዓለም አምነህ አገርህን ጥለህ ወደሌላ አገር ልሒድ ማለትህ የበሽታ ነው እንጂ የደኅንነት አይደለም ሲል በትር ቀረሽ ቍጣውን ባወረደብኝ ጊዜ ነብር ሆንሁበት።

ይሁን እንጂ ነገሩ ምክሩም ልቤን ሳይነካውና ስሜቴን ሳይመታው አልቀረም። እውነትም ይቺን አመንዝራ ዓለም ተማምኖ ወዲያና ወዲህ ማለት የሚያስፈልግ ሁኖ አይታይም በማለት ሕሊናየ ይታመስ ይቆላ ጀመር። ቢሆንም በአሳቤ ቻልሁት እንጂ ባፌ አልተናገርሁትም።

Join us on Telegram @amharicbookss

ነገር ግን አንድ ጊዜ ቆርጬ ተነሥቻለሁና፤ ያላችሁትን ብትሉ እባብም ይዛችሁ ብታስፈራሩኝ ራሱንም ሞትን አምጥታችሁ ዋጠህ ሰለቀጠህ አኝክህ አላመጠህ፤ እያላችሁ ብታባንኑኝ መቅረት አይወራም በማለት የክርክሩን በር ዘጋሁበት።

እሱም ሆደ ባሻ ኖሮ እኔ ለአንተ ብዬ ነው እንጂ ለእኔ ብለህ እንደ ሆነ እንጭቆረር ድረስ ብሎኝ እየተጐናተለና እየተጉነፈ የት ሚናውን ሔደ።

ከዚህ በኋላ የእናቴ አባት ወንድም አያቴ አቶ ደባልቄ መጥቶ እንደሚቀጥለው ተናገረኝ።

ጃርት እሾሃም በመሆኗ ልጆች ስትወልድ በሾሁ እንዳይወጉ እሾህ በሌለበት በብብትና በብብቷ ትታቀፋቸዋለች። የእነሱ እሾህ መዋጋት ሲጀምር ግን ፉር ትለቃቸዋለች ይባላል።

ሰዎችም ልጆቻቸው በሕፃንነታቸው አመለኛ ቢሆኑም እስኪያድጉ ድረስ ይታገሷቸዋል። ካደጉ በኋላ ግን ፉር የለቋቸዋል። አንተም እንደዚያው መሆንህ ነውና ፉር ለቀንሃል ሲል ገሠፀኝ። እኔም አሁን እኮ የናቲቱን የጃርትን እሾሃምነት ስትናገሩ የእናንተ ነገር እሾህነት አልታወቃችሁም እንጂ ራሳችሁ በራሳችሁ ተዘልፉዋል። እኔ ግን ምንም ብትሉኝ ያው አንድ ልብ ነኝ። ሁል ጊዜ እጅግ አጣምሮ በስንፍና ታስሮ ማቱሳላን ሆኖ ፱፻ ዓመት ከመኖር አንድ ቀን ሙሴን ሆኖ መሞት ይሻላል።

የልማድ ጉም የሸፈነው የስንፍና ደመና የጋረደው ጊዜ መቼም ቢሆን ለፀሐይ አይመቻችም። ዘለዓለም ከስንፍና ምድጃ፤ ተወዝቶ ይኖር ዘንድ፤ በለባዊነት ነፍስ የተፈጠረ ፍጥረት እንዲህ ያለው ተግባር የሞት ሞቱ ነው። ስለዚህ የናንተና የመጣው የትውልድ ዘመን የሚያቀርበውን ጥያቄ በትክክል ሚዛን መመዘን አለባቸው። ግድ ሆኖብኝና ግድ ሆኖባችሁ ነው እንጂ እኔ ከእናንተ እናንተ ከኔ መለየት መች ያስፈልግ ነበር። እንዴት ያለች እናት ናት ልጅዋ ወደሩቅ ለመሔድ ሲነሣ አትሒድ የማትል አባትም ቢሆን የሚመለከተው ልጁ ካጠገቡ እንዳይርቅ መሆኑ የታወቀ ነው። እናንተም ይህን በማለታችሁ ፍርድ የለባችሁም። እኔ ግን ለሕይወትም ሆነ ለሞት እሔድ ዘንድ ቈርጫለሁና የእናንተም ሐሳብ ቈራጥ ይሁን።

ትርኪ ምርኪ አሳብ አታብዙብኝ። እግዚአብሔር ያለው ነገር የትም ቢሆን አይቀር። እባካችሁ በገዛ አረሟ አባብ ይዛ አስፈራራች የተባለው አይድረስባችሁ። ሁሉም ልጁ እንዳይማር

Join us on Telegram @amharicbookss

እንዲህ የሚያደርግ ከሆነማ ለሀገሩ ማን ያስብ። የጎን ውጋትያለበት እንደ ልቡ ተጐን እጐኑ ሊዘወርና እንደ ልቡ ሊተኛ አይችልም። ያልተማረ ሕዝቡም እንደ ልቡ ካገር አገር ሊዘዋወርና በዓየርና በባሕር ሊንሸረሸር አለመቻሉ የታወቀ ነው፤ ዙሪያ ገባው ጨለማ ይሆንበታል። ባልተማረ ሕዝብ ሞኝ ይስቅበታል። ብልህ ያለቅስለታል። እማራለሁ የሚለውንም ሕዝብ ሞኝ ያሰንፈዋል። ብልህ ያበረታታዋል።

ይልቅስ ሞኝ አትሁኑ። ይህን ያለ ተጐድቷል። ይህን ያላለ ግን ተጠቅሟል። ያለትምህርት የሚገኘው ድንቁርና ብቻ ነው። የሆነው ይሁን። እንዲያው ምናምንቶ ወይም እንቶፈንቶ ሁኜ የምቀር አይደለሁም ። አህያ ሞተች ተብሎ ጉዞ አይቀርም። እናንተ እንደምትሉት ችግር አለ ተብሎ ትምህርት ይቀራል ለማለት አይታሰብም።

እኛ ወጣቶቹ የሕይወታችን ፀሐይ ሳይጠልቅ። የሞት ጥላ በላያችን ሳይወድቅ፤ መማር አለብን። እናንተም ሽማግሌዎቹ ልጆቻችሁ እንዲማሩ ከማድረግ በቀር እንዲህ ያለ አሳብ ማሰብ ደግ አይደለም።

ገራገሩ ዘመን በገርነቱ አልፏል። መጪው ዘመን ብልጣብልጥ እንደሆነ ማወቅ አለብን። እንኳን ሳይማሩ እረ ተምሮም በሆነ እንኳን ሳያውቁና እረ አውቆም በሆነ እንኳን ሳይሠሩና እረ ሠርቶም በሆነ።

ዓለም ላቡ እስቲንቈረቈርና እግሩ እስኪነቃ ተራወጠ። በምድር ተሽከረከረ። በሰማይ በረረ። በባሕር ተንደረደረ። አራምዶ ተመለከተ። አሻቅቦ አየ። በብዙውና በአያሌው ርቋል። አሄሄ እረ የትና የት። እረ የት እየለሌ እሱን ማየት እሱ ወደ ወጣበት ወጥቶ ነው እንጂ እንዲያው ከታች ሁኖ አይደለም።

ሦስተኛ ክፍል።

የእናቴ የወይዘሮ ያዳንቁሽና የአባቴ አቶ አደገኛ ንግግር።

ይህን የምትለውን ሁሉ ባይናችን ባናየውና በእጃችን ባንዳስሰው በጆሮዋችን ስምተነዋል። እርግጥ ነው። ይህን የመሰለው ትምህርት በዚሁ በእኛው አገር ቢስፋፋ እሩቅ ሳትሔድ እዚሁ በዚሁ ትማረው ነበር። እኛም ጧት ጧት ጧት ስንቅህን በሰውንና ጭብጦውን፤ ሙልሙሉንና

Join us on Telegram @amharicbookss

ሽልጦውን፤ እየያዝን እየሔድን ለመጠየቅ እንችል ነበር። ይህ ያወራኸው ያለበት አገር ከሰማይም የራቀ ነው። ታዲያ ምን ይሁን ትላለህ። እያሉ ቢበዘብዙኝ እኔም ዋ የናንተ ነገር። ትርፍም ዕውቀትም የሚገኘው ከመሔድ ነው። ወጣ ብሎ ካላዩ፤ ዕልፍ ብሎ ካልተመለከቱ፤ ራቅ ብሎ፤ ካልተማሩ ዕውቀት እንደ ውሻ አነፍንፎ የሚመጣ መሰላቸው። እናቴ የቀረው ቀርቶ፤ እናንተ እንደ ዱሮዎቹ እናቶቻችሁ መፍተል አቅቷችሁ፤ ከውጭ አገር በመጣ ፈትል በገዛ ነጋዴዎቻችሁ አንደበት።

አርፈሽ ተኚ፤ ዙረሽ ዕቀፊኚ፤

ሰነፈ ሴቱ፤ ባሌን አሞኘሁት፤

አረፈ ጣቴ፤ ይሰበር ደጋኔ፤

ወልደየስ ተመጣ፤ ጥጡን ጠላው ዓይኔ፤

እየተበላችሁ መሰደባችሁና መቀለጃ መሆናችሁ በምን ምክንያት መሰላችሁ። ባትፈለቅቁ ባትዳምጡ፤ ባትባዝቱ ባትነድፉ ባትፈትሉ፤ ባታጠነጥኑ፤ አይደለምን። እያደር ዕውቀት እንደ መጨመር ያንኑ የቆየውን የናቶቻችሁን ባልትና እያጐደላችሁ መሔዳችሁ ሙያ መሆኑ ነው። በእናባቴም በኩል የእርሻ ዘዴያቸውን ማሻሻል አቅቷቸው፤ ያው የመጀመሪያ ድግር ጠራቢና ያው የቀድሞው ሞፈር አራቂ ባስገኘው ብልሃት ከመታገል በቀር ምንም የፈጠሩት ነገር የለም።

ስለዚህ አሁን እናንተ እንደምትሉኝ እንኳንስ እኔ ወንዱና ሴት እሳት በነበረችኝ በሴቶች በኩል ያለውን ዕውቀት ገብይታ እንድትመለስ ይዣት በሔድሁ ነበር። አትሒድ ከማለት ይልቅስ በመንገድም ከዚያም ከደረስሁ በኋላ ችግር እንዳያገኘኝና መማሪያ እንዲሆነኝ ገንዘብ አዋጥታችሁ ስጡኝ። የኔ ዘመዶች ገንዘብ ሲሉዋችሁ አትወዱም ይሆናል። ገንዘብ ሞታችሁ ነው። እንኳን የሩቅ አገር ስንቅና የኮሶ ስንብት እንኳ ከፍ ብሎ ፍሪዳ ዝቅ ብሎ ሙክት ወረድም ብሎ ሲካካ ዶሮ ይታሰብለታል እያልሁ ይህንን መላልሼ ስናገር እናቴ ያዳንቁሽና አባቴ አደገኛ ምን ቁርጥ ቢያደርገን ነው ገንዘብ ስትለን ካንተ ይልቅ ገንዘብ የምሳሳ። የቀንበር በሬያችንንም ቢሆን ሽጠን ላንተ ጉዳይ ብናውለው ምን ቅር የሚለን ነገር የለም። አይዞህ ለገንዘብ አታስብ።

Join us on Telegram @amharicbookss

ነገር ግን እኛን ቅር የሚለን፤ እኛ የምናዝነው እኛ የምንጨነቀው ዕድሜያችን የደረሰ ልጣችን የተራሰ መቃብራችን የተማሰ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ እኛን እንደ መጦርና አስታሞ አጥቦ አጥኖ ገንዞ እንደ መቅበር ወደ ውጭ አገር ልሒድ ማለትህ ብቻ ነው አሉኝ።

እኔም አዬ የእናቴ ነገር። የጊዜውን መድረስ የልጡን መራስና የመቃብሩን መማስ ተዉት። የማናችን ዕድሜ እንደሚቀድም አይታወቅም። በአቤል እንደሚታወቀው ሞት የተጀመረው በልጅ ነው እንጂ ባባትና በእናት አይደለም። ወይ እኔ ሙቼ እናንተ ትቀብሩኝ ይሆናል። ስለዚህ ቀዳሚውን የሚያውቅ ያው እግዚአብሔር ብቻ ነውና፤ የዚህን ዕውቀት ለሱ እንልቀቅለት።

ስለጡረታውም ጧሪ ፈጣሪ ስለሆነ እግዚአብሔር ያዘጋጅላችሁን አታውቁትም። ወይም የኔ ተምሮ መምጣት ይጠቅማችሁ ይሆናል።

ይህስ ልጅን ገንፎ በቅቤ ሊበላህ መጣብህ እያሉ እንደማስፈራራት ያለ ነውና ሞኛችሁን ፈልጉ። ከእናንተም ጉያ ብቀመጥ አታድኑኝም። ሰው ለአፈር ምግብ የተፈጠረ ስለ ሆነ እኔ ለየትኛው አገር አፈር የታዘዝሁ ምግብ መሆኔን አላውቀውም። እናንተም አታውቁትም። ለእኔ በግልጽ የሚታወቀኝና ወለል ብሎ የሚታየኝ ወደ ውጭ አገር ሔዶ መማርና ተምሮ ተመልሶ መጥቶ አገርን ማገልገል ብቻ ነው። በዚህ መካከል ያለውን ምሥጢራዊ ነገር የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ስለ ሆነ ከእግዚአብሔር እወዳደራለሁ እንደሚል ሰው መሆን አይገባችሁም

እኔ ከናንተ አላውቅምና ነው እንጂ፤ ስንኳን እኔ ልጅ እግሩ፤ እናንተም በተማራችሁ አገራችሁ እንዴት ደስ በአላት።

ትምህርት በጧትም፤ በማታም፤ አንዳንድ ቃል በልብ ሣጥን ቢወረውሩት መጠራቀሙ የማይቀር ነው። ያይጥ እንግዳ ከስልቻ ውስጥ ጐዝጉዙልኝ የጅብም እንግዳ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ ይባላል። ዛሬ በዓለም ላይ መልካም ነገር ይደረግልን ዘንድ ክፉ ነገር እናድርግ የሚሉ የግፍ ኃይለኞች መነሣታቸውን በጊዜው አዝማሚያ ሳላውቀው አልቀረሁም።

ይሁን እንጂ ሕልምን ፈርቶ ሳይተኙ አያድሩም እንደሚባለው፤ ገና ጦርነት ሳይነሣ አይቀርም ተብሎ ትምህርት የሚቀር አይደለም። ዓለም እንደሆነ መቼም ጦረኛ ነው። አንድ ጊዜም እንኳ ቢሆን ጦሩን የሰቀለበት ጊዜ የለም።

Join us on Telegram @amharicbookss

ከዚህ ቀደም ዛሬም ቢሆን ኢትዮጵያውያን ሳይሆኑ ኢትዮጵያን የሚሙኙ በስብከትና በልዩ ልዩ ማታለል ልባችንን ለመማረክ የሚከጅሉት በምን ምክንያት ይመስላችኋል? በቀላሉ ገምተውን እኮ ነው። አልተማሩም ብለውን እኮ ነው። ሳይማሩ እንቅደማቸው ሳያውቁ እናጨናጉላቸው በማለት ያደቡብናል። ይዶልቱብናል።

ስለዚህ ግምታችን ዝቅ ያለ ሆኖ እንዳንደፈርና ወደ ኋላ እንዳንቀር እንዳይኸይ ራሳችንን እንዳንጥል መታገል የታገልነውና የታገለንን መጣል ያስፈልገናል። እንግዲህ ወደ ፊት መቀጠል እንጂ የሥልጣኔ ዕርፋችንን ወደኋላ አንጨብጠውም። ወደ ኋላ መመለስ ቀርቷል። በሰፊው ሙሉ ተስፋ የተደረገበትና መሠረታዊ እምነት የተጣለበት ሐዲሳዊው ኑሮ እግር በእግር ተከታትሎ ለመግባት እንደ ንጋት ፀሐይ ጨረሮቹን ፈንጥቋልና ልባችንን እንስጠው። ይሙቀን። ቈፈን አይቅረበን።

በእንደዚህ ያለ ማዳከም የወጣቶችን አሳብ የተሰበረ መቃ ለማድረግ በፍቅራዊ መንፈስ ቀይም በመንፈሳዊ ፍቅር ልቡናን ማሸት በአእምሮ የተቀረጸውን የዕውቀት ማኅፀን ያሟሽሻዋል።

ታሪካችን እንደሚመሰክረው ጉዳያችን ከውጭ አገር ጋር የተያያዘ በመሆኑ ሥልጣኔያችንም ከውጭ አገር ሥልጣኔ ጋር የተያያዘ መሆን እንዳለበት መግለጫው የትምህርት መስፋፋትና የዕውቀት መራባት ነው። የዓለምን አድናቆት ብቻ በአፍ ላይ ሲያሟሙቁ መኖር ለተደናቂው እንጂ ለአድናቂው ምንም ዋጋ የለውም።

«ሰይጣን ቢታምም ባሕታዊነት ያምረዋል ይባላል። አሁንም ልማድ የሚሸነፍበት ጊዜ ስለድ ደረሰ በእናንተ ላይ ልቡሰ ሥጋ ሆኖ አትማሩ የሚል አሳብ መነሣቱ ምንም እንኳ የሚገርም ቢሆን የልማድ ሥልጣኑ ተሸንፏል።

ዕንቅልፍን ድል የነሣ ዓለም በፍልስፍና ገበታ ላይ ተቀምጧል። ጥበብንም እንደ ምግብ በዓይነት በዓይንቱ ያማርጣል። እህሳ ይህንን የሰማ ሕዝብ ዝም ብሎ መቀመጥ ያስፈልገዋል ብላችሁ ስተነግሩኝ ቃላችሁን ማመን ይገባኛል?

እንግዲህ እናንተም እኔም በእልክ መንገድ ሳይሆን አስፈላጊውን ማመዛዘን አለብን። የዘመኑ ኪነ ጥበብ እንዲያው በከንቱ ሊገኝ አለመቻሉን ስነግራችሁ ካላመናችሁ መልአክም ከሰማይ ወርዶ ቢነግራችሁ አታምኑም።

Join us on Telegram @amharicbookss

የሥልጣኔውን ደረጃ የረገጡት እንኳ ከዚያው ቁመው ሊቀሩ አልወደዱም። ጧት ከዕንቅልፋቸው ተነሥተው ማታ እስኪተኙ ድረስ ከመሻሻልና አእምሮአቸውን ከማደላደል በቀር የሚያርፉበት ጊዜ የላቸውም።

እነሱ ከቀን ወደ ቀን በሚተላለፉበት በ፳፬ ሰዓት ውስጥ መሻሻላቸውን ባለማቋረጥ ሲያገሠግሡ፤ እኛ ብዙ ዘመን አሳልፈን ለመሻሻል ብንነሣ ብርቅ አይሆንም።

እኔን ከሚያሳስበኝ ነገር እናንተ ለምን ነፃ ትሆናላችሁ። አብረን እንጨነቅበት። ብንሠለጥን ምሥጋናውን ጥቅሙ፤ ባንሠለጥን ነቀፋውና ጉዳቱ የጋራችን መሆኑን ለምን ትዘነጉታላችሁ። በዚህ ነገር ልባችሁ አይድከም። እኔንም አታድክሙኝ።

ተዳክሜማ ብቀር ወደ ኤውሮፓ ለትምህርት ለመሔድ ለተሰናዱት ለሌሎች ጉዘኞች ወጣቶች መጥፎ አርአያ እሆን የለምን።

ያገሬ እንጉርጉሮ ያለውን አልሰማችሁም ይሆን።

ወታደሮቹ ሲያነጣጥሩ፤

ገበሬዎቹ ጤፉን ሲዘሩ፤

እነመምሩ ቅኔ ሲመሩ፤

ነጋዴዎቹ ብሩን ሲቆጥሩ፤

ሸማኔዎቹ ሸማ ሲሰሩ፤

ሁሉም ያምረኛል በየምግባሩ፤

መባሉ ሙያ ጠቃሚ ቢሆን አይደለምን። ሙያው ሲባል፤ ይህ ከዚህ በላይ የተዘረዘረው ብቻ አይደለም። የማናውቀውና የማያውቀን ብዙ ጥበብ እንደ አሸን ፈልቋል። እንደ ምንጭ መንጭቷል። ታዲያስ። ዝምታውስ፤ ስንፍናውስ ምን ይጠቅማል።

Join us on Telegram @amharicbookss

አንዳንድ ወጣት ወደ ፈረንጅ አገር ለትምህርት ለመሔድ ሲነሣ፤ እንደዚህ ያለ ዝብዝብና ንዝንዝ የሚቀርብለት ከሆነ አገር ምኑን ሠለጠነ። ያንን ትምህርት የሚያመጣው ማነው። ሥልጣኔስ ምን አይቶ ማን ተከትሎ ሊመጣ ይችላል።

እማማየ ያዳንቁሽና አበባየ አደገኛ፤ አጐቴ ነውጠኛ፤ አክስቴ ጣዲቅ፤ አያቴ ሸዋየ፤ እንደትወዱኝ እወዳችኋለሁ እንደምወዳችሁ ትወዱኛላችሁ። ነገር ግን ከትምህርት አብጬ አልወዳችሁም።

እንግዲህ በሔድሁበት አገር መቸም ብቀር ያው ልቅሶዋችሁ ነው። በደህናም ብመለስ ደስታችሁን የሚወስድባችሁ የለም።

እናንተ አትሒድ ስትሉ አልቅሳችኋል። እኔም እሔዳለሁ ስል አልቅሻለሁ። ዋጋ ያለው የማንኛችን ልቅሶ መሆኑ የሚታወቀው ወደፊት ነው።

ተባብለን በእርግጥ በምንለያይበት ጊዜ ከዚህ በታች የሚገኘውን መዝሙር ዘመርሁላቸው።

በስመ ሥላሴ ፊቴን አማትቤ

ለመሔድ ስነሣ አብረህ ተነሥ ልቤ።

ልቤ ካልተነሣ ከሞት ሕሊና

የሞት ታናሽ እንቅልፍ ይጫጫናልና።

ፈረሰኛው ጊዜ ሲሮጥ ያለፋታ

አሁን ምን ይባላል የእግረኛው መኻታ።

አወይ የሰው ነገር ዛሬም ነገም ዕንቅልፍ

ወፍ እንኳ ነፍስ አውቃ ስትጮህ ስትለፈልፍ።

እረ ነጋ ነጋ ወፎች ለፈለፉ

Join us on Telegram @amharicbookss

ሥራው ተወዝፎ ምንድነው ዕንቅልፉ።

ለነገ ተብሎ ዛሬን ከዘለለ

ይኸ የዛሬው ቀን ምን ቀን ሆኖ ዋለ።

የወፎች መንጫጫት ምን ያስተምረናል

የዶሮውስ ጩኸት ምን ይሰብክልናል።

ወፍ ሆኖ ሲነግረን ጊዜ የሱን ነገር

ልብ አልሰማም እንጂ ጆሮስ ሰምቶ ነበር።

ልብ የጆሮን ያህል ሁሉን ቢያዳምጥ

ከተሰማው ሁሉ የለም የሚያመልጥ።

ሆኖ ላይሆን ሞልቶ ላይሞላ ትዳር

ምን ታታግለናል ከየጊዜው ጋር።

ብለው ጊዜያቸውን በዕንቅልፍ ያሳለፉ

እስከ ዘላለሙ ቀሩ እንዳንቀላፉ።

እኔ ይህን መዝሙር ዘምሬ ከዘመዶቼ የተሰነባበትሁበት ዘመን ከጥንቱ ልማድ ያልተላቀቀ ጠባይ ስለነበረበት ከነባህሉ እግሩን አንፈራጦ ለመኖር ሲመቻች ወጣቱ ዘመን አዳዲስ ልማዶች አስከትሎ፤ መጥቶ፤ ዘው ብሎ ለመግባት በሩን በመታ ጊዜ፤ አትገባም እገባለሁ የማለት ክርክር ተነሥቶ ሳለ፤ ሥልጣኔ በሽማግሌዎች ዘንድ ለመግባት ፍራት ፍራት ሲለው በወጣቶች ተረድቶ መግባት ሲጀምር የዚህን ፍጻሜ ሰላይ ለመሔድ በባቡር ተሳፈርሁ።

Join us on Telegram @amharicbookss

አራተኛ ክፍል።

ደህና ሁን ደህና ይመልስህ።

ደህና ሰንብቱ ደህና ቆዩኝ።

ዘመዶቼ ሲሰናበቱኝና ስሰናበታቸው በሞት እንጂ በሕይወት የተለየኋቸው አልመሰላቸውም። ገና ከመሰናበቴ በፊት ባቡሩን ባዩት ጊዜ ጠሉት። ልጃችንን ካሸፈተብንና የውጭ አገር ካስመኘብ አንዱ ይህ ነው። «አግዐዚ» ገና በልጅነቱ ባቡር ሲያይ፤ ይህን ጊዜ ጊዜ እኛም ተምረን ቢሆን እንደዚህ ያለ በሠራን ነበር እንዲሁም አኤሮፕላን የሚባል ነገር ባየ ጊዜ እኛም እኮ አኤሮፕላን እንደሠሩ ሰዎች ያለ ዕውቀት ኑሮን ቢሆኑ በራሪዎችንና ተሽከርካሪዎችን በመሥራት በቻልን ነበር እያለ ልቡ ስቅል ብሎ ታንድ ቀን አንድ ቀን ያለ ትምህርት ሌላ ነገር ባሳቡ ሳይገባ ጧት ማታ ይህኑ ብቻ በማውጣት በማውረድ በማንሣት በመጣል፤ በኀዘንና በትካዜ ይኖር ነበር። በመጨረሻውም ይኸው አንድያውን ሊሔድ ተነሣ እያሉ ሲጫወቱ ነበርና በባቡር ላይ ስሣፈር ባዩኝ ጊዜ አዘኑ። ወዲያው ለሱስ ያስበው ሊሆንለት ነው። አሁንም እግዚአብሔር ያድርግለት። እኛ ወዮልን እሰከ ወዲያኛው። እስኪመለስ ድረስ በኀዘን ሰውነታችን ወደ መቃብር ይወርዳል እያሉ ኀዘናቸውን ሲወያዩ ባቡሩ ለመነሣት ፉጨቱን ባሰማ ጊዜ እርስ በርሳቸው ተጫጩሁ። መርዶዬ ገና ሳልሔድ የመጣ መሰላቸውና ተላቀሱ። ዓይናቸው ወሀ ሁኖ አለቀ። እንደ በረዶ ሟሟ አዬ እናት መሆን? የናቴንማ ኀዘን ምን ብዬ ልናገረው። የእኔም መንፈሴ ታወከ። ሰውነቴ ተሸበረ። በኀዘን ስካር ራሴ ዞረ። መሔድ አይበለው። እነሱ እያለቀሱ ሲመለሱ ልቤ ተመለሰ። እንዲያውም ወደ ኋላ እየጐተተ አስቸገረኝ። ባቡሩ ግን ወደ ፊት መሔድ ግድ ስለ ሆነበት ጉዞዬ መንታ ሆኖ ለሁለት ተከፈለ። ልቤ ዋለለ። ስሜት ወደ ኋላ እየጐተተኝ ምን ይዞ ጉዞ እንደሚባለው እንዴት ልቤን ትቸው ወደ ባዕድ አገር እሔዳለሁ ልሒድ አልሒድ፤ ልቅር አልቅር እያልሁ ሳመነታና ካሳቤ ጋር ስወያይ አሳቤ ብልጥ ኑሮ ልብህን አታዳምጠው «ልቡ ሁለት የሆነ በመንገዱ ህሉ ህውክ ነው» የተባለው እንደዚህ እንዳንተ ልብ ላለው ነው። ዕወቀው። እሱ የሚፈልገው የመንድር አውደልዳይና አደዝዳዥ ሁነህ እንድትቀር ነው። ዘማች ለጦርነት ከተነሣ በኋላ ወደ ኋላው አይልም። አንተም አንድ ጊዜ ተነሥተሃልና፤ የተከተለ ይከተልህ። የቀረ ይቅር። ያለቀሰ ያልቅስ። የሳቀ ይሳቅ፤ ብሎ በጥልቅ ምክሩ ስለ አበረታኝ የግዴን ለመሔድ ተበራታሁ። ሆኖም ልብ ቀርቶኛልና ምንም ባቡሩ በቀጥታ ቢሽከረከር ለእኔ የአሸዋ ወይም የሸተቴ ላይ ሩጫ ሳይሆንብኝ አልቅረም። የሆኖ ሆኖ።

Join us on Telegram @amharicbookss

እንዲያ እንዲያ ነው

መንገድ የጋራ ነው

የተማረ በጣም ተከበረ

ያልተማረ ቀረ እንደታወረ

የሔደ ዕውቀትን ነገደ

የሰነፈ ችግሩን ታቀፈ

በማለት አሳቤ ስላልተለየኝ ከሱ ጋር ስወያይ፤ እሱም ሁሉንም ነገር ትቶ ዋና ትዝታው ያገሩ ነገር ሆነበትና ትካዜና ናፍቆት ስለ ፀናበት እንዲህ እያለ ይትከነከን ጀመረ።

ዋ አገሬ ካንቲ ወዲያ ሌላ ምን ፍቅር ይኖራል ፍቅሩ ሁሉ ተሰብስቦ ያለው በአንቺ ላይ ስለሆነ የናስት፤ ያባትስ፤ የጎትስ፤ የወንድምስ፤ የሚስትስ፤ የልጅስ፤ የገንዘብስ ፍቅር ያለአንቺ እንዴት ሊታወቅ ይችላል። ሁሉም እኮ ዘመድ መሆኑ የሚታወቀው ባንቺ ቆሞ ነው።

ገና ካሁኑ ናፍቆትሽ ትኩሳቱን ረጨብኝ። ገና ካሁኑ ፍቅርሽ በርበረኝ። ገና ካሁኑ ስሜትሽ የሆድ አጥንት ሆነብኝ። እስካይሽና እስክታይኝ ድረስ ጊዜው እንዴት ይልቅ ይሆን። በዚህ ዓይነት የልብ ስብራት፤ ከቶ ትምህርቱ እንዴት ይሳካልኝ ይሆን፤ ዘመኑስ እንዴት ይዘለቃል። ቀኑስ እንዴት መሽቶ ነው ሌሊቱ የሚነጋው። እያለ ይህኑ ከማሰላሰል በቀር፤ እኔን ጉዳይ ሳይለኝ መንገዴን እቀጥል ጀመር። እኔም አሳቤ እስኪ ና ተከተለኝ። እንግዲህ ክፋህም ለማህም ዘመዴ አንተ ነህ። የልቤማ ነገር ምን ይሆናል። ገና ካሁኑ ከዳኝ። የነገር ሁሉ መጥፎ የልብ ከዳተኛ ነው። ምነው ከምሄድበት አድርሶኝ አብረን በተመለስን እያልሁ ሳስብ፤ በሰውነቴ ውስጥ ብዙ ትዝታ ተወራጨ።

በዚህም ጊዜ የነበረኝ ሕይወት በሕልም ውስጥ ያለ ያህል ሆኖ ስለሚሰማኝ ዘመዶቼ ከተሰነባበቱኝ በኋላ እንደገና መለስ ብዬ በሩቅ ባያቸው ዕንባቸውን ያዘንቡታል። ወዲያው የኔም ዓይን ዕንባው እንደ ምን እንደ ፈለቀለት በማይታወቅ ፍጥነት ነጠብጣቡን ያወርደው ጀመር። ዘመዶቼ መሐረማቸውን ሲያርገበግቡልኝና እኔም መሐረሜን ከኪሴ ለማውጣት ባያዳርሰኝ እጄን ዘርግቼ ሳርገበግብላቸው ባቡሩ እየራቀ ሄደ። እነሱም ራቁኝ። እኔም ራቅኋቸው። ነገር ግን ይህ

Join us on Telegram @amharicbookss

ሕልም ይመለኝ ነበር። ፍቅሬና ናፍቆቴ መልሶ በመካከላቸው ያስቀመጠኝ እየመሰለኝ ከዚህ ቀደም እነጋገርበት የነበረውን የጉዞ ታሪክ እንደ ገና አንሥተን እንነታረክ እየመሰለኝ፤ ሳልም ደግሞም ሕሜ ሲለቀኝ ወደ አእምሮ ስመለስ የነበረኝ ትግል ከባድ ነበር። በዚህ ምክንያት አእምሮየ ተመስጦ ወደ ኋላዬ እንጂ ወደ ፊቴ የሄድኩ ሳይመስለኝ የብሱ አልቆ ከባሕር ደረስሁ።

በዚህ ጊዜ በመነሻና በመድረሻ የተደረገው ነገር ያደንቃል። ከባቡር የወረደው በመርከብ ከመርከብ የተራገፈው በባቡር ለመሳፈር የምድሩ ወደ ባቡር የባሕሩ ወደ ምድር ሲራወጥ ሁኔታውን ማየት ታላቅ ትንግርት ነበረበት።

አምስተኛ ክፍል።

የባሕር ላይ ጉዞ።

ስም አይጠሩ ከሚባለው የባሕር ወደብ ስንደርስ ባቡር ስለቆመ በእግር ወርጄ ለምሳ ወዳንድ ሆቴል ገብቼ፤ ከሆቴለኛው ስንነጋገር አሳቤ ፍጆታውን አላዛውር ብሎ አስቸገረኝ። እኔኑ እንጂ ሌላ አታነጋግር እያለ የስሜቴን ልጓም ይዞ ይስበኝ ጀመር። ሲያለቅሱ ውሎ መሳቅ፤ ሲስቁ አድሮ ማልቀስ አይቀርምና እባክህ ተወኝ። አሁን እንኳን ትንሽ ልፍታታ አልሁና የሆዴን ነገር አስታውስ ጀመር።

ከሚዋጠውም ከሚጠጣውም፤ የተቻለኝን ያህል ምሳየን ቀረቃቅቤ እፎይ ካልሁ በኋላ፤ ወደ ወደቡ ሔጄ በባሕሩ ዳር ከሚንሸረሸሩት ጋር እየተንሸረሸርሁ ያደረግሁት ተስፋና አለኝታ ብዙ ነገር አሳሰበኝ። ይህ ባሕር ማን ይባላል። የባሕሩስ ወደብ ማን ይሰኛል፥ ብዬ ብጠይቅ ተጠያቂው ከኢትዮጵያዊነት ያልራቀና፤ ኢትዮጵያዊነትን ያልለቀቀ፤ ስም ተመልክ፤ ዘር ከታሪክ የያዘ፤ ዓይነ ውሀው አንተኑ የመሰለ ነው አለኝ። ታዲያስ። እንዲህ ሲሆን ባሕሩ ከጥንት ግዛቱ ለምን ለምን ተነጠለ። ወደቡስ ከጥንት አገባቡ ለምን ተከፈለ። አሁንስ ያለው በማን እጅ ነው? ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ኢትዮጵያዊውን ባሕር ለመውሰድ እንዴት ቻለ፥ በማለት ረዥም ጥያቄ ለማቅረብ ሳሰናዳ፤ አሳቤ ተው እረፍ ነገር አትቈስቍስ። ለሁሉም ጊዜ አለው በተባለው መሠረት ለመውሰድ ጊዜ እንዳለው፤ ለመመለስም ጊዜ አለው ብሎ ነገር ሲጀምርልኝ ጉዳዩ ገባኝና አፌን ተመተምሁ።

Join us on Telegram @amharicbookss

በዚህም ቀን አዳር በዚያው ይሆን ዘንድ መወሰኑን ስለሰማሁ ወደ ሆቴሉ ተመልሼ ከአሳቤ ጋር ስነዛነዝ ሌሊቱ ወለል ብሎ ነጋ። እንደነጋም ወደ ውጭ ብቅ ብል ቀይ አስተኔ የሆነውን የጎሑን ጨረር በባሕሩ ላይ በሰፊ ጫካ እንደ ተለለቀ የቋያ እሳት ሁኖ ባየሁት ጊዜ አገር የተቃጠለ መሰለኝና በድንጋፄ ተያዝሁ። ከቶውንም ሣጥንህ ካለብት ልብህ ያለው ከዚያ ነው፤ እንደሚባለው፤ ሻንጣየን ይዤ ላምልጥ የማለት ስሜት ይወተውተኝ ጀመር።

እንዲያውም መርከቡ የመነሻ ፉጨቱን ባምባረቀው ጊዜ የእሳት አደጋ መከላከያ መሰለኝና ከዚህ አገር ምን እግር ጣለኝ በማለት ተጨነቅሁ። ነገር ግን አትኩሬ ከመመልከቴ የተነሣ፤ በባሕሩና በፀሓዩ ጨረር መካከል ያለውን ነበልባላዊ ፍልቅልቅታ ለይቶ ለማየት የሚችል አእምሮ ሰለተሰጠኝ ሁሉንም ትቼው እገረም ጀመር።

ስለዚህ ውበትንና ውነትም አዛምዶ የሥነ ፍጥረትን መልክ በሚያስገርም ሁናቴ ላይ ለመግለጽ ችሎታ ያለውን አምላክ ማመስገን ግድ ሆነብኝ። ይህን የመሰለ አንክሮ ሳለሁ፤ መርከቡ የሚነሣበት ጊዜ ስለደረሰ መርበትበት ሆነ። እኔም እንዳያመልጠኝ ሻንጣዬን ይዤ ስተን፤ ያየኝ ይገረም ነበር። ከመርከቡ ደርሼ እግሬ የብሱን በሚለቅበት ጊዜ ሌላ ስሜት አደረብኝ። በእርግጥ ከሀገሬ መራቄ ተሰማኝ። እንዲሁም አገሬ ከእኔ ስትርቅ እንደኔው ያለ ጥልቅ ኀዘን እንደሚስማት ታወቀኝ። እንዲያውም እናቴ ያዳንቁሽ ስትሰናበተኝ ካደረገችው ጭንቀት የበለጠ ኀዘን እንዳደረባት መንፈሴ ነገረኝ። ይህን ሁሉ ጥልቅ ስሜትና የጋለ ኀዘን በሆዴ ችዬ አንጀቴ ረመጥ የፈሰሰበት ያህል እያረረና እየተቃጠለ የአገሬን መሬት ተሰናበትሁ።

ከወደቡ አፋፍ እስከ መርከቡ ጫፍ በተዘረጋው መሰላል ላይ ስወጣማ፤ ያለው ሁናቴ የሞት ያህል እንጂ። ሌላ አለምሰለኝም። አላምን አልሁና እንደ ገና ወደ ኋላዬ መለስ ብዬ አገሬን ሁለተኛ ጊዜ ስሰናበታት ዕንባዬ ከዓይኔ እየተዘረገፈ በባሕሩ ላይ ይንዣረር ጀመር። በዚህም ጊዜ ብዙ ዕንባ እንደ ፈሰሰኝ ሰውነቴን ስለ ተሰማውና እንደ አጋጣሚ ባሕሩ ሲንቀሳቀስ ስለ አየሁት፤ ዕንባዬ ለባሕሩ የሙላት ረዳት ሆነው እንዴ፥ በማለት የልብ ልብ በቃኝ። ቢሆንም ይህ ስሜት የሞኝነት እንደ ሆነ በቶሎ ተረዳሁት።

ወዲያው ከመርከብ ስሣፈር የመርከቡ አሠራር የተፈለሰፈው ከትምህርት መሆኑን አብረውኝ ከተሳፈሩ ሰዎች ተረዳሁ። ወይ አገሬ። መርከብ አልሠሩልሽ። የፈረንጅ ትምህርት

Join us on Telegram @amharicbookss

አያስፈልግም ማለታቸው የሚገርም ነው። የፈረንጅን ብልሃቱን እንጂ፤ ክፋቱን አይማሩም፤ የተባለውን ለምን ዘነጉት። ዳሩ ግን ምን ያድርጉ። አላዩት። አልሰሙት። ይሁን እንጂ ባሕሩ ሳይኖር መርከቡ ምን ይሆናል። ሆኖም ምንም ባሕሩ ባይኖረን ለጊዜው ያለ ሕግ የተወሰደብን ባሕር በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትግልና ብርታት፤ በሕግና በፍርድ አስገዳጅነት በጊዜም ረዳትነት እስቲመለስ ድረስ የብስ አለን ምነው ባቡሩ ወይም ከሚዎንና ኦቶሞቢል አልሠራን አየር አለን። ምነው አኤሮፕላን አልፈጠርን።

ዳዊት በስድስት መስመሮች ስለ ግብረ እደ ዕጓለ እመሕያው የተናገረውን አፈጻጸም ለምን ዝም ብለን እናያለን። ከዚህም አንዱን ብንጠቅሰው ልባችንን ሳይመታው አይቀርም።

እጅ አላቸው አይዳስሱም፤ መባል እንዴት ያለ ከባድ ምሥጢር ያለው መሆኑ ሲመረመር የመጨረሻ ትርጉሙ አይሠሩም ማለት እንደ ሆነ ይሰማናል። ስለዚህ ነገር፤ ኢሳይያስም አልበዘነም። ለሰው ወቀሳ የጻፈው ዘለዓለም ሲታወስ ይኖራል። የቀድሞ ሰዎች መቼ ጥቅሙን ተረዱት። ቢረዱትስ ልጆቻቸውን እንዲማሩ ባደረጉ ነበር። ከዚህም የተነሣ ከዚህ የሚከተለው ስሜት ይታገለኝ ጀመር።

ታዲያ ለዚህ ምን ይበጃል። የሚበጀውማ ላለፈው ክረምት ቤት አይሠራምና ከዛሬ ጀምሮ ወጣት የተባለ ሁሉ በቦዘን ላይ አይገኝም። በቤቱ ውስጥ አይዋል። ሁሉም ወደ አገር ቤትም ሆነ ወደ ውጭ ለትምህርት እየሄደ ይማር። በዱሮው ስንፍና ወጣት ተይዞ አይቅር፤ ዕንቅልፍ አይመረው። ከልቡ ይነሣ።

እስከዚያውም ድረስ ያገር ቤቱን ትምህርት ያጠናቅ ያገርን ትምህርት ማጠናቀቅ ለሌላው መሰላል ይሆናል። ሀሁን ሳይቆጥሩና በለሉ አፍን ሳይፈቱ፤ አቤሴድን ላንከላውስህ ቢሉት አይመችም። መላስን እንቅፋት ይመታዋል። ሰነፍ በመከር ጊዜ ይተኛል የተባለው እንዳይፈጸምበት ይህን የተባለውን ማጠናቀቅ አለበት።

የመከርን ፍሬው ከረገፈ በኋላ ልሰብስብህ ቢሉት ያስቸግራል። የትምህርት ወቅትም ካለፈ በኋላ ትምህርትን ልማርህ ቢሉት ጭራውን አያስጨብጥም። ቀንዱን አያሲዝም።

Join us on Telegram @amharicbookss

«በዕለት ደስታ ብቻ ዕልልታን ከሚያበዙ ዕንቍራሪቶች ይልቅ ዋ ዋ የሚሉ ቍራዎች ዕድሜ አላቸው» እንደሚባለው የዱሮውን ልማድ ብቻ ይዞ ከመኖር ይህኑ የመጨረሻ ዕውቀት አድርጎ ከመተኛት ካዲሱም ሥልጣኔ ደብለቅ ማድረግ የሚጠቅም መሆኑ የታወቀ ነው። ንፍሮ እንኳ የሚጣፍጠው እብሽንብራው ስንዴ፤ በስንዴው ምሥር በምሥሩ ዐተር ሲቀይጡት ነው።

ከዚህ አስቀድሞ ያለው፤ ይቅርና በእኛው ዕድሜ እንኳን ወጣትና ሽማግሌ ለየብቻው እየሆነ ጊዜውን ይጓተተው ነበር። የወጣቱ አሳብ የግርማዊነታቸውን ቅን መንገድ እየተከተለ፤ የሠለጠነው ዓለም ከደረሰበት እንድረስ ወደፊት እንገሥግስ ወደ ኋላ አንመለስ፤ አዲስ መንፈስ እንልበስ፤ አሮጌ ባሕላችንን እናድስ፤ እያለ በተቻለውና ጊዜ በፈቀደለት መጠን ለመራመድ ሲፋጠን በታየ ጊዜ ከላይ እንዳልሁት፤ ሽማልጌዎቹ ዋ። የዛሬ ዘመን ልጅ ወረተኛ ነው። የዱሮው ልምድ ምን ወጣውና ነው እሱን ትተን የፈረንጅ ትምህርት እንማር የምትሉት። ይልቅስ እኛ እንደ አባቶቻችን ልማድ እንደኖርን እናንተም እንደ እኛ ልማድ መኖር አለባችሁ። ይህ የፈረንጅ ትምህርት ምኑም አይመራችሁ በማለት ክርክሩ ቀጥሎ ሳለ ፲፱፻፱ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ ሲባሉ ብዙ ሥራዎች ይከናወኑ ዘንድ መሠረታቸው ሲጣል ከላይ እንደ ተናገርነው ዱሮ የማናውቀውን ለማወቅና ያልነበረውን የነበረ ለማድረግ የወጣቱ አሳብ ሲሞክር አረጋዊ አሳብ ምን ቢያገድ አዲስም አናስገባ እኛም አንታደስ ሲል የተነሣው ጭቅጭቅና ክርክር ከቶ በምን ዓይነት አሳብ ተፈጽሞ ይሆን ላውቀው በወደድሁ ነበር በማለት ትኩስ ስሜት በሰውነቴ ውስጥ ካውያንው አሙቆ ልቤን ያሸው ይዳምጠው ጀመር፡

የዚህ ኃላፊነት የወደቀበት ግርማዊነታቸው ምን ይችል። ምን ይጸና። ምን ያለ ብርቱ ነው። ላይችል አይሰጠው እንደሚባለው እግዚአብሔር ይህን ከባድ ኃላፊነት የጣለባቸው እንዲችሉለት አውቆ ነው። ስለዚህ ነገር በምሔድበት አገር ሁለት ወይም ሦስት ዓመት ከቆየሁ በኋላ ከተወደደች አገሬ ደስ የሚያሰኝ አዲስ ወሬ ሳይደርሰኝ አይቀርም ማለትን አጫዋችና ወሀ አጣጭ አድርጌ፤ ተጉዤ ከአውሮፓ ካንዱ ክፍለ ሀገር ደረስሁ። እንደደረስሁም ከሀገሬ ምን ወሬ እንደሚደርሰኝ አሳቤን እስቲ ተጠያየቅ ብዬ እቀሰቅሰው ጀመር።

Join us on Telegram @amharicbookss

ስድስተኛ ክፍል።

የሀገሬ ትዝታ።

መድረስ አይቀርምና ባሕሩን ዘልቀው ከውጭ አገር የብስ ደረስን። እንደ ደረስንም ከመርከብ ስንወርድ ከዚህ ቀደም በሀገሬ የማላውቃቸው ድንቅና ብርቅ የሆኑ ልዩ ልዩ ውበቶችና ኪነ ጥበቦች ታዩኝ።

ከዚህ የተነሣ የሀገሬ አኳኋን ትዝ አለኝ። ትዝታዋም እሳቱን ለኰሰብኝ። ከቶውንም ረመጡን በተነብኝ። ጭፈራውን ብው አድርጎ አነደደው። ሰውነቴን አቃጠለው አንዠቴን አሳረረው። የናፍቆቷ ሽል በሆዴ ተላወሰ። የሠራ አካላቴን አፈራረሰው። ፍቅሯ በጥልቅ ሰውነቴ ገብቶ በረበረኝ። አገሬ አገሬ የሚባሉ ቃላት ባፌ ላይ ተጥፈው ሌላ ንግግር ከለከሉኝ።

ከሀገሬ ስነሣ ለትዝታ እንዲሆነኝ ብዬ ከመሬቷ አፈር ቆንጥሬ በመሐረቤ ቋጥሬ በሻንጣዬ ይዤ ነበርና ከደረስሁበት ከውጭ አገር አፈር ጋር ባመዛዝነው በለጠ። ባሸትተው ጣፈጠ። ብንተራሰው እንደ ሕልመ ዮሴፍ ለብዙ ነገር መክሥት ይሆነኝ ጀመር። ስንቱንስ ትዝታ ልንገራችሁ።

ሌሎቹ አገሮች ምንም በተግባረ እድ ቢያምሩና ቢሸቀረቀሩ የእኔን አገር የመሰለ ሌላ መልካም አገር የእኔ አገር የሚወዳደር ሌላ ደኅና አገር ላይገኝ ምን ያታክተኛል። ይሁን እንጂ የውጭ አገር ሰዎች ያሉበት አገር ምንም የተፈጥሮ ውበትና መልካምነት ባይኖረው በሰዎቹ ትጋት በሰዎቹ ብርታት በሰዎቹ ማማር፤ በሰዎቹ መጣጣር ለጭንጫው መሬት ያለውን የተሟላ የሥልጣኔ ልምላሜ አይቼ ይህ ብቻ በአገሬ በመጉደሉ ኀዘን ተሰማኝ፡

በእውነትም እንደዚህ ያለውን በደም ግባትና በመንክራዊ አሠአር የቆነጀውን የሥልጣኔ ውበት አይቶ በራስ በኩል ያለውን ጉድለት መመልከት ታላቅ የልብ ትኩሳት መሆኑን በማያወላውል ሁኔታ በማስታወሴ ተናደድሁ። ተቅበጠበጥሁ። ወጣቶች እናስገባ ሽማግሌዎች አባቶቻችን አናስገባም ብለው ክርክር ያቀረቡህ ጉዳይ አንተ ነህን። ቸኰልህ ምነው። ገና በወደቡ እንዲህ ያለ ድንቅ ነገር የገጠመኝ ወደ ዋናው ከተማ ስደርስማ አምላኬ ምን ሊያሰየኝ ይሆን፥ በማለት እየተገረምሁ ትዝታየን ቀጠልሁ። አገሬ ይህን የሥልጣኔ ምርት በወጣቶች እያፈስሽና እየተረፈስሽ ለማጌጥና ለመዋብ ለመክበርና ለመበልጸግ ለመሠልጠንና ከፍ ካለው ደረጃ ለመቆም ዕድልሽ እንዲቃና ተስፋ አለን።

Join us on Telegram @amharicbookss

አሁን በዚህ በአለሁበት ሥፍራ ዓይንሽን በዓይኔ ላይ አድርገሽ ኤውሮፖች የወለዷቸው ጥበበት ለመላው ዓለም እንደ ተረፉት ተመልከች። ተመልክተሽም አንችም ከነሱ እንዳንዱ ለመሆን ወደ መሆኛው መንገድ ገሥግሽ ብየ ምኞቴን ሳካፍላት፤ የጆሮቿ በሮች ክፍት ሆነው እንዳመጡኝ ይሰማኝ ነበር። እንዲያውም ምናልህ። ምናልህ። እስኪ መልሰው። በማለት ንግግሬን እያጣጣመች እይጠየቀችኝን ያህል ተሰምቶኛል። ይህም በአሳቤ እንዳለ። ሽማግሌዎቹና ወጣቶቹ እንደ ምን ሆነው ይሆን። ምነው የዚህን ፍጻሜ የሀገሬ ወፍ መጥታ በነገረችኝ። ወይም እኔ ወፍ ሆኜ በሰማይ አንዣብቤ ክንፎቼን አራግቤ ከመስኰቷ ላይ ዱብ ባልሁ።

ይህም ሳይሆን የዮናስ ዓሣ ነባሪ መጥቶ ዋጥ አድርጎ ወስዶ ከቀይ ባሕር ዳር ወይም ከህንድ ውቅያኖስ ጠረፍ ምነው በተፋኝ።

እንደዚሁም በባሕር ተጥሎ የነበረውን ሙሴን አሰብሁና ለሙሴ የእናት ሞግዚት ያዘዘለት አምላክ ለኔስ እንዴት አንድ ክንፈ ረድኤት ሳያዝልኝ ይቀራል፥ ብዬ ይህን ላስብ አእምሮየ ተመሰጠና ክንፍ አውጥቶ ለመብረር ወደ ኢትዮጵያ ሰማይ ተወነጨፈ። እንዲያውም ምናልባት ይዞኝ ወደ ሰማይ የሚወጣና የሚሔድ መስሎኝ እጄን ባርገበግብ እንኳን የወፍና የፌንጣ ያህል እንኳ መፈናጠር ሳይሆንልኝ ቀረ።

በዚህ ምክንያት የሚያስተክዝ ስሜት ያዘና በኅዘን መንዶ ይቀጠቅጠኝ ጀመር። ቢሆንም ያለሁበት አገር ውበትና ደም ግባት አትሒድ እያለ አሳቤን ይጋብዘው ስለ ነበረ፤ አሳቤ ከመብረር ሽብረክ አለና ያለሁበትን ሆቴል ከመመልከት የተነሣ ውበት ዕንባ አድርቅ ሆነብኝ።

ሰው ግብዝ ነው። በመሪር ኅዘን ላይ ሳለ ዓይኑ አንድ ነገር ያየ እንደሆነ፤ ኅዘኑን እርግፍ አድርጎት ያኑ ያየውን ያዝሁህ፤ ለቀቅሁህ፤ በማለት ላይ ይገኛል። እንዲሁም በደስታ ላይ ሳለ አንድ ኅዘን ልቡን የመታው እንደሆነ፤ ያዙኝ እፈሱኝ በማለት ለጋባዥ ያስቸግራል።

ስለዚህ እኔም በጽኑዕ ኅዘን ላይ ሁኜ እርር ኩምትር ስል በአካባቢየ ያሉት የሥልጣኔ ፍጥረቶች ሬሳ እንኳ በፊትህ ቢጋደም ሰውን ደስ እንዲለው ከማሳሳቅና ደስታን ከማጋበዝ በቀር የኅዘን ስሜት እንዲወጋህ ስለማያደርጉ ኅዘኔን አላወቁልኝም። ከቤቱ ውስጥ ሲገቡ የደስታው ፍካት ወደ ደጅ ቢወጡ የፍሥሓው ሙላት ኅዘንን ያሥረሳል። ታዲያ በምን ይወቁት።

Join us on Telegram @amharicbookss

ልዩ ልዩ መልክና ልዩ ልዩ ኅቡረ አምሳል ያላቸው የቤት ውበትና የሰው ቡቃያዎች አትክልቶችና ከአትክልቶች ጋር እየተሳለፉና እየታገሉ ሲሽከራመሙ የሚታዩት የምድር ጌጦች ሌላ ስሜት ያፈልቃሉ።

አበባዎቹ በፍልቅልቅነታቸው መንገደኛውን ሁሉ ይጠቅሳሉ የመንገደኞችም አፍንጫዎ ቢልቃጥ ሁነው ሽቶዎቻቸውን ይዘግባሉ። ፍሬዎቹ በየዘለላቸው ተንጠልጥለው በየቅርጫቱ ተቆለው ዋጡን ሰልቅጡን ግመጡን ላጡን አላምጡን ብሉን አሽትቱን ይላሉ።

የአበባዎቹ ለምለም ጆሮ በእጅ ነካ ሲያደርጉት ጣፋጭ መዓዛው ከጣት ይቀራል። የፍሬዎቹም ወለላ ጣት ያስቆረጥማል። ከንፈር ያስመጥጣል። እንዴት ያለ ጠለ ምሕረት ከላይ ቢወርድለት ነው ልምላሜው እንዲህ ያማረው። እንዴትስ ያለውን ማየ ሕይወት ቢያጠጡት ነው ቅጠሉና ቀንበጡ እንዲህ ያለፈለፈው። ይህን ሁሉ አይቼ ለማን ተመኘሁት ላገሬ መሬት ነዋ ለሌላ ለማን እመኝ ኖሯል። እረ ለመሆኑ ደግ ነገር ሲገኝ መልካም ታሪክ (ነገር) ሲያገጥም ዋ ምነው። ይህ መልካም ነገር ለሀገሬና ለወገኔ በሆነ። ከማለት በቀር ለሌላ ለማን ይታሰባል።

ሰዎቹ እንደ ሥጋጃ በለሰለሰው መንገድ የሚንሸረሸሩበትን የአንድ አንዱን ኦቶሞቢል አስደናቂነት ባየሁ ጊዜ መንገዱ እንደዚህ የሆነ ከዚህ ወጥተው የሚገቡበት ቤት እንዴት ያምር እንዴትስ የተሸቀረቀረ ይሆን። በማለት ናፍቆት ያዘኝ።

ያረፍሁበትን ሆቴል ተዉት። በጥዳቱ፤ በውበቱ በሽቅርቅርነቱ ልቤን ስለማረከው እንኳንስ በሕወቴ ሙቼም ቢሆን ሬሳዬ እሽም ብሎ የሚወጣ አልመሰለኝም። አብያተ ክርስቲያናቶቹ ወደ ላይ በቁመት ወደ ጐን በስፋት ሰው ሠራሽ በማይመስልና እጅግ ከፍ ባለ ድንቀኛ በሆነ አሠራር ተሠርተው ልባዊ የሆነ ጸሎት ሲደረስባቸውና ጥልቅ የሆነ ስብሐተ እግዚአብሔር ሲነገርባቸው፤ ጸሎቱንም ስብሐተ እግዚአብሔሩንም መስማት የሕንፃቸውን ውበት ማየት በባሕረ ፍሥሐ ገብቶ እንደ መዋኘት ያለ ነው። በዚህ ላይ ደግሞ ደውሎቹ በመንፈሳዊ ዜማ ሲደወሉና ቃጭሎቹ ሲቃጨሉ ይህንም የሰሙ ምዕመናን ወደ የቤተ ክርስቲያኑ ሲጐርፉና እንደ ደረሱ ተንበርክከው ሲሰግዱና፤ ፊታቸውን ሲያማትቡ በእውነት ከእግዚአብሔር ይቅርታን እንደሚያገኙ ይታመናሉ።

Join us on Telegram @amharicbookss

መነኰሳቱና ቀሳውስቱ ዲያቆናቱና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሆኑ ሁሉ በንጽሕና አጊጠው በቅድስና ተንቆጥቁጠው በመላእክተ ሰማይ ምትክ መላእክተ ምድር ሁነው በቀስታ ሲራመዱ በለሆሳስ ሲናገሩ የቃላቸው ጣዕመ ንባብ የገጻቸው ግርማ ሞገስ ያስገርማል። በማንኛውም በኩል ባላቸው ሥነ ርእይ ሲመለከቷቸው ኃጢአት ነጥብ ያላረፈባቸው ሁነው ከመታየት በቀር በሌላ በምንም አይከጀሉም።

በየጸሎት ቤታቸው ያሉት ሥዕሎችና የቅዱስ አምልኮት ምልክቶች ልብን በርኅራኄ ይሰሩበታል። አሳብን በትካዜ ይማርኩታል። ስሜትን በሐብለ ፍቅር ይስቡታል። ይህን ሁሉ አይቼ አንክሮ ስለያዘኝ። እኔም ማናቸውንም ኪነ ጥበብና ተግባረ ዕድ ቢሠሩት ነው እንጂ ቢያዩት አይሆንም። በማየትማ ቢሆን አፍንጫ ጐራዳዎችና ዓየን ልሞች ስንደዶ የመሰለ አፍንጫና እንደ አጥቢያ ኮከብ የሚያበራ ዓይን ባዩ ጊዜ እንደአዩት በሆነላቸው ነበር የሚል ስሜት ለአሳቤ ስሞታውን ያንጐደጕደው ጀመር። እንደ ገናም ስሞታውን ቀጠል አድርጎ፤ የድሮዎቹ የአገሬ ሰዎች አንዳድን ብረት ሠሪ ሲገኝ በዓይኑ ሰው አይቶ ይባላል እያሉ ስሙን ሲያጠፉ ምግባሩን ሲያከፋ ከመዋል ይልቅ ያዩትንም የሰሙትንም እንዲህ ሠርተው ቢሆን ይህን ጊዜ ማን ዐዋቂ ይሆንላቸው ነበር እያለ በአሽሙር ስለነካካኝ ሁሉንም ተውሁትና ምነው ባልመጣሁት፥ አሰኘኝ። የሆነ ሆኖ ምንም ደስ የሚያሰኝ ሥነ ርእይ ባይለየኝ አሳቤ ያለው ካገሬ ትዝታ ጋር ነበር።

ዕንቅልፌ ሁሉ የዶሮ እንቅልፍ ሆነ። ልቤን ወሰድ መለስ ያደርገዋል። ዓይኔ ብልጭ ድርግም ይላል። በሕልሜ ውስጥ ከሚደርስብኝ ቅጥቃጤ የተነሣ የተኛሁበት አልጋ ሲዘፍን ያድራል ቀን ያሰብሁት የተመኘሁት ሁሉ ትርፍ ትርፍ የሆነ ድቅስቃሽ ቅዠት ይዞ እየመጣ ወደ ሰማይ ሲያወጣኝ ወደ ምድር ሲያወርደኝ ወደ ባሕር ሲያጠልቀኝ ያድራል። በዚህ የተነሣ ታላቅ ሥጋት ያዘኝ። የባዕድ አገር ውበት ልቤን ከማረከው ትምህርቱን ምን ጊዜ ልማረው ነው እያልሁ እጨነቅ ጀመር።

ዘመዶቼን ስሰናበታቸው ወደ ውጭ አገር ሔደህ የሚጨበጥ ነገር ይዞ መምጣት አቅቶህ በወሬ ብቻ የቀረህ እንደ ሆነ ታፍራለህ። እኛንም ታሰድበናለህ ያሉኝ ለካ እውነት ኑሯል፥ በማለት ከአሳቤ ጋር መጨነቁ ባሰኝ።

Join us on Telegram @amharicbookss

መቼም ስሜቴ አቤቱታውን የሚያቀርበው ለታላቁ ዳኛ ለእግዚአብሔር ነው። ተሚጋቹም ከዚያው ውስጥ ለውስጥ ያሉት አሳቤና አሳቤ ስለ ሆነ አንደኛው አሳቤ ከዚህ በላይ ምኞቱን ለገለጸው አሳቤ እንዲህ ሲል ይመልስለታል።

ይህን ያህል የሚያስጨንቅህና የሰው አገር ዓይተህ ይህን ያህል የሚያስጐመጅህ ምንድ ነው። ከእኛ አገር የበለጠ ሀብታም አገር የት ቢሔዱ ይገኛል። በሰው አገር ቅጠልና አበባ የምትገረመው በእኛ አገር ቅጠልና አበባ የለምን።

ባጭሩ ለመረዳት ብትፈልግ፤ ገና አንድ እንኳ ገጽ ሳትገለብጥ ዳዊት በመዝሙሩ መጀመሪያ፤

ወዘሕጎ ያነብብ መዓልተ ወሌሊተ፤

ወይከን ከመ ዕፅ እንተ ትክልት ኅበ ሙሐዘ ማይ

እንተ ትሁብ ፍሬሃ በበጊዜሃ፤

ሲል ለምለምነቷና ፍሬያማነቷን፤ በዙሪያዋ ባሕሮች ያሉዋት መሆንዋንና ሕዝቦቿም ደጋግ ከመሆናቸው የተነሣ በመዓልትም በሌሊትም ሕግ ጠባቂነታቸውን በበገና ቅኚት እያንጐረጐረ የዘመረው መዝሙር ለማን ይመስልሃል። ሰው ሠራሹን የሥልጣኔ ውበት ትተን እግዜር ሠራሹን ቍንጅና ስንመለከት ከኔ አገር ከእግር እጣቢዋ የሚደርስ አንድም የለም።

ታሕት ጽላሎቱ ፈተውኩ ወነበርኩፐ

ወፍሬሁኒ ጥዑም ለጕርዔየ።

ሲል ሰሎሞን የተናገረለት የኔ አገር ዛፍ አይደለምን። ተፈጥሮ ጐደላት ሊባል አይቻልም። ካረስን ከቆፈረን ጠንክረን አትልክት ከተከልን፤ ካለማናት ካቀናናት፤ ከዚህ የበለጠ ሀብት ማግኘታችንን እንዴት ትዘነጋዋለህ። ወሀው ነው ተንጣልሏል። መሬቱ ነው በሰፊው ተዘርግቷል። ዕንጨቱ በያይነቱ በቅሏል። ከጡቶቿ ማርና ወተት ይፈልቃል። ምን ታጥቶ። ምን ጠፍቶ። ምን የሌለ ነገር አለ።

Join us on Telegram @amharicbookss

የሁላችን መጋቢያ ሆኖ የሚያሟግተን ይህ «አግዐዚ የሚባለው ወጣት አገር ለቆ መውጣቱ ወደ አገሩ በተመለሰ ጊዜ በዚ ያየውን ሁሉ እንዳየው አድርጎ ሠርቶ አገራችንን ሊያለማትና ሊያቀናት አይደለምን። አንተ በዚህ በሰው አገር በየአደባባዩና በየደጁ ያየኸውን አበባና ፍሬ ያስገርምህ ይሆናል። በዚህ አትደነቅ። ዋናው ነገር ይህ አይደለም። በዚህ አይግረምህ።

የብረታ ብረቶች የጨርቃ ጨርቆችን የሸክላ ሸኽሎችን የምግባ ምግቦችን፤ ይህን የመሳሰሉትን አዕማደ ሀብቶች የሚሠሩበትን ፋብሪካዎች አቋቁሞ መድፍና መትረየስ ከነጥይቱ ከነቦምቡ ከዚያው ካሚዮንና ኦቶሞቢል ከዚያው የሱፍና የጥጥ ልብስ ከዚያው እንዲገኝ ፍልስፍናውም ሲያንሱም ከዚያው እንዲመነጭ ማድረግ ነው ብልህ የሚአሰኘው። አግዐዚም አገር ለቆ የሔደው ይህንኑ ለመማር ሲል ነው።

አዎ እናቱ ስታለቅስ አባቱ ሲጨነቅ እምቢኝ ብሎ እስከዚህ ድረስ የመጣው የማን ጐፈሬ ሊያበጥር ነው። የሌላ ቆንጆ፤ የባዕድ ጐጆ ማየት ብቻ ምን ዋጋ አለው። ለሽርሽሩማ የኢትዮጵያ አውራጃዎች መቼ አነሱት። ልቀቁኝ ልቀቁኝ የማይል ነውና ወደ ላይኛው አሳብ ልመለስ። ከአትክልቶቹና ከአበባዎቹ ማማር የተነሣ ለዕድለኛው አስተያየት ሌላ ሥነ ርእይ ተለወጠለትና የተመስጦ ስሜት ይዞት ሔደ።

በተለይም የእግዚአብሔር አበባዎች የሆኑትን ቆነጃጅትና ሞንዳላዎቹን ወይዛዝር፤ የዕንቍ ነጸብራቅ የመሰለውንና የአልማዝ ጤዛ ያረፈብትን ውበታቸውን ማየት ምንኛ መታደል ነው።

በዕውቅና በረቂቅ ብልሃት የተሰፋ አጫጭር ልብሳቸውን ለብሰው ተረከዛቸውን በኸረ ሎሚ አስመስለው ደንበልበል ያለ ባታቸውን ገለጥለጥ አድርገው ጠጉራቸውን ወረዳ ተሠርተው *(ታሽመው)* ጉንጭና ጉንጫቸውን ያፈራ ብርቱካን አስመስለው ደረታቸውን ጣል አድርገው ጡታቸውን በደረታቸው ላይ ፈለል ፈለል እያለና እንቡር እንቡር እያለ የአደይ አበባና ጽጌ ረዳ የመሳሰሉ ልጆቻቸውን አስከትለው ዓይኖቻቸውን እንደ አጥቢያ ኮከብ እያቁለጨለጩና ጥርሶቻቸውን እንደ ነጭ አልማዝ እያንጸባረቁ ከንፈሮቻቸውን እንደ ፍሕሶ አበባ እያንተገተጉ ከባሎቻቸው ጋር ክንዶቻቸውን አስታቅፈው ሲንሸረሸሩና በፍቅር ሲነጋገሩ ከተፈጠሩ እንዲህ ነው መፈጠር ከማለት በቀር ሌላ ምንም ሊባል አይቻልም።

Join us on Telegram @amharicbookss

እነዚህን የፈጠረ አምላክ ምንኛ ይመስገን። እነሱ ባጠገቡ ሲያልፉ ፍዝዝ ብሎ የማይመለከት እንዴት ያለ ነው።

ባጠገባቸው የሚያልፍ ባለጉዳይ ፈዝዞ እነሱኑ ከመመልከት በቀር ጉዳዩን አያስታውሰውም። ቢሔድም ልቡ አብሮ ሔዷልና ሌላ ትዝታ የለውም።

አይንህ እሺ አይልም። ወደ ዞሩበት አብሬ ልዙር ይላል። የልብንማ ነገር ተወው። እነሱኑ እንዳሰበ ውሎ እነሱኑ እንዳለመ ያድራል።

አዬ ሞት ሲጨክን ቢውል በእነዚህ ይጨክን። ምናቸው ለሞት። የፍቅርን ታዕም ባያውቀው ይሆናል። አንቆ መውሰድንም እኮ ፍቅር ብሎት ይሆን እነዚህን የመሳሰሉ የወርቅ ፍልቃቂዎች ወስዶ ከአፈር መደባለቅና ውበታቸውን ማፈራረስ እጅግ ያሳዝናል።

ሞትስ ይሁን መቼም የማይቀር ነው። ምነው ኃጢአቱና ክፋቱ በቀረ። ይህን የመሰለ ሰብአዊ ውበት እንዴት በኃጢአት ባዜቃ ይነከር። እንዴትስ የክፋት መሣሪያ ይሁን…

ውስጡን ለቄስ ትተን በሰው አበባነት በኩል እንደዚህ ያለው ውበት ሲታይ ከነፋሱ የሚወነጨፈው የደስታ መዓዛ ከተማውን ሲያውደው ሰውነት በደስታ ከመርካቱ የተነሣ መጥፎ ነገር ባፍንጫ አይገባም። በዓይን ዓይታም። በጆሮ አይሰማም። በአፍ አይነገርም። ከመንገዱ ወላንሳነት የተነሣ እግር ከፈቀደው ላይ ቢያርፍ አይሰናከልም።

ይህን አይቶ መሠረቱ ምን እንደሆነ ሲመረመር መማር መሠልጠን መሥራት መፈልሠፍ መትጋት መንቃት ከሥራ ጋር መታገል መሰለፍ ሥነ ፍጥረትን እየተከታተሉ መሻሻልና ወደ ፊት መራመድ እንደሆነ ያስረዳል።

የመደነቁና የማድነቁ ፍላሎት ገና ጨርሶ ሳይወጣልኝ እንዲያው ዕፁብ ድንቅ በማለት ንግግሬን ከማቆም በቀር የማማሩን አኳኋን ምን ብዬ ልናገር።

ወደ ኤውሮፓ ተሻግሮ ከአንዱ ወደ አንዱ ተዘዋውሮ የያንዳንዱን አገር ውበት ዓይቶ ተመልክቶ የተመለሰ በጐደለው ይሙላው እንጂ እኔስ ጽፌ አልጨርሰውም። ተናግሬም አልዘልቀውም።

Join us on Telegram @amharicbookss

የቤቶቹ አቀያየስና የሕንፃዎቹ አናናስ የከተማው አቀማመጥና አሸበራረቅ የቤት ዕቃውና ወርቃ ወርቅ የሆነው የቤቱ ጌጣ ጌጥ ከፀሓይ ጋር ይወዳደራል። የፋብሪካዎቹ አበዛዝና የሠራተኞቹ አበረካከት በቀን በብዙ ሚሊዮን እየተቆጠሩ የሚከናወኑት የጥበብ ሥራዎችና የሥልጣኔ ፏፏቴዎች፤ በቴክኒክ ረገድ በየጊዜው እየተፈለሰፉ የሚለፈሉት የዕውቀት ፍልፍሎችና የጥበብ ተንቀሳቃሾች ሁሉ ይህ፤ ኅብራቸው ይህ ግብራቸው ይህ ቍጥራቸው ይህ ዲካቸው ሊባል አይቻልም።

ማናቸውም ጥበባዊ ተግባር በአንክሮ ሲመለከቱት በእውነት የሰው እጅ የሠራው አይመስልም። ሰውም ይህን ሠራ ለማለት ችሎታው ያስቸግራል።

ያው እግዜር በምድር ወርዶ ያነጸውና የቀረፀው ያደሰውና የቀደሰው፤ የጠረበውና ያለዘበው የፈለሰፈውና የነደፈው፤ ለሰው ልጅ የቀን ሠራተኛ ሆኖ በቀን በቀኑ ሠርቶ ያውልህ እመርበት አጊጥበት ክበርበት ሠልጥንበት ብሎ እጅ እጅ ያስረክበው ይመስላል። ያንዱ ውበት ተለይቶ ሳይጠገብ ሌላው ይተካል። እንዲሁም የሌላው አድናቆት የሰውን ልብ እንደ ማዕበል ሲያውከው፤ ሌሎቹ ውበቶች ሰውነትህን የኤክስፐዚስዮን መደብር አድርገው እየን እየን በማለት ይጓተቱታል።

ለጊዜው የውጭ አገር ቋንቋ አላውቅም ነበርና በደረስሁበት አገር ያሉት ሰዎች እንደ ብርቅ እየተመለከቱ ቢያዩኝ ምንም አይወጣኝም እኔም እንደ ድንቅ ባያቸው ምንም አይወጣቸውም።

ንግግራችን በዓይን ብቻ ሆነ። አንዳንድ ጊዜም የተረዱ ለመምሰል አንገት መነቅነቅ ይደረግ ነበር።

ከንፈሬ ሲላወስ አፋቸው ሲንቀሳቀስ ማየት ብቻ አስገረመኝ። የነሱ ድምጽ ለኔ እንደ ደወል ሆነ። መስማሚያ ታጣ የኔም የነሱም ንግግር ያልተፈለፈለ ፍሬ፤ ያልተፈለቀቀ ጥፍጥሬ ያህል ተገመተ። ሆኖም ከመዋል ከማደር የተነሣ የሚናገሩትን ከሚሠሩት ጋር በማተራጐም አፌ መሔጃ ከንፈሬ መላወሻ፤ ሲያጣ የግድ ለመድኋቸው ለመዱኝ። እያደርም የአፌ እሥራት እየተፈታ መጽሐፉም ዝም ቄሱም ዝም አለ ማለት ቀረ። አፍ ለአፍ መካፈት ተጀመረ። ፍሬ ነገራችን ተመረመረ።

Join us on Telegram @amharicbookss

ነገር ግን የቆዳ ነገር አስቸጋሪ ሆኖ ነበር። እነሱ በቆዳቸው የሚኮሩበትን ያህል እኔም በቆዳዬ ታላቅ ክብር እየተሰማኝ ስለምኮራባቸው ኢትዮጵያዊነት ታላቅ ክብር ያለው መሆኑን በአኳኋኔ ሁሉ እየተረዱ በኢትዮጵያዊነት የሚገባኝን ክብር አልከለከሉኝም ነበር። በስኒማና በቲያትር አዳራሽ በሆቴልና በእስፖርት ክበብ ባፈቀደኝ ሥፍራ ብቀመጥ፤ ተነሣ የሚለኝ ሳይኖር ወደኔ እየመጡ ባጠገቤ ይቀመጡ ነበር። እኔም ወደነሱ እየሔድሁ ስቀመጥ፤ የክብር ፊት አልነሱኝም። እንግዲህ ወደ ከተማው ሥነ ውበት ልመለስ።

በዚያውም በነበርሁበት ከተማ ከአንድ ፋብሪካ ቤት ገብቼ የሚሠሩትን ልዩ ልዩ የቴክኒክና የፍልስፍና ሥራዎች በማየት መደነቅና መገረም በዝቶብኝ ፍዝዝ ብዬ ስመለከት፤ ከነባሮቹ አንዱ ምነው ምን ሁነሃል። አገርህ ወዴት ነው አለኝ። እኔም እንደ መንቃት ብዬ፤ አግሬማ አፍሪካ ነው። ምና አፍሪካ። ኢትዮጵያ። ታዲያ በኢትዮጵያ እንደዚህ ያለ የለም እንዴ ምን ያስገርምሃል፥ ቢለኝ መኖርስ አለ። በሀገሬ ያለውን ከዚህ በማየቴ ነው የምገረመው ብዬ የዘዴ መልስ ሰጠሁትና ተላቀቅን።

ዋ ዛሬ ያ ያየሁት ሁሉ በጦርነት ምክንያት እንደምን ሆኖ ይሆን። ዋ ፈራርሶና ተደምስሶ ይሆናል። ምንም ቢጠፋ ጠፍቶ አይጠፋም። ለኤውሮፖች ሥልጣኔ እንደ ልምድ ስለሆነ አሁን ሳይውል ሳያድር ከቀድሞው የበለጠ አድርገው ይሠሩታል። ድንቁርናን ስንፍና ልምድ ሆኖ አትሥሩ እያለ እንደሚያስቸግርና ዕንቅልፍ እንደሚያሲዝ፤ ሥልጣኔና ዕውቀትም ልምድ ሆኖ ሥሩ፤ አትስነፉ እያለ ይወተውታል። ዕንቅልፍ አያስወስድም።

ሰባተኛ ክፍል።

በኢትዮጵያ ተራራ የሥልጣኔ ጮራ።

ከሔድሁም ከትንሽ ጊዜ በኋላ የንግሥትን ሞት ሰማሁ። ያ መልካም ሰውነታቸው በሞት ተነጠቀ በማለት አለቀስሁ ተከዝሁ ነገር ግን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አነሣሥ ታላቅ ተስፋ ሆነኝና አጽናናኝ። አረጋጋኝ። ከቶውንም ባለሁበት አገር አስደናቂና ታሪካዊ ነገር ወደ ኢትዮጵያ ይገባ ዘንድ የሚቻለው በግርማዊነታቸው ዘመነ መንግሥት ነው በማለት ባገኘሁት ስሜት፤ ኢትዮጵያ በሥልጣኔ ተመሥርታ ብርሃን በእጅዋ ጨብጣ ከቀደሙት አገሮች ጋር ለመተካከል ስትፋጠን በገሃድ አየኋት። ወዲያው ይህን ነገር እውነት አድርገው ብዬ ለእግዚአብሔር ጸሎት አቀረብሁ።

Join us on Telegram @amharicbookss

እንግዲህ መፋጠን ከጀመረች እግር ካወጣች ሳትደር አለመቅረቷን የሚያስተማምን ተስፋ በሰውነቴ ሰለሞላ የሀገሬ ናፍቆት በጣም ጸናብኝ። ፍቅሯ በሰውነቴ ውስጥ ተንቆራጠጠ። በደም ሥሮቼ ውስጥ ተራወጠ። ከቶ በሀገሬ ሳለሁ ሀገሬ ይህን ያህል ትናፍቀኝና እናፍቃት ኖሯልን እያልሁ ከማጠናው ትምህርት ጋር በአንጐሌ አሰላሰለው ጀመር።

ከሔድሁም የተማርኩትን ትምህርት ብመዝነው አነሰብኝ። ጊዜው ግን በዛብኝ። ወደ ሀገሬ ስመለስ ለማገልገያ በቂ ዕውቀት ሳልይዝ የተገኘሁት እንደሆነ ምን ያህል ወቀሳና ኃፍረት ይደርስብኝ ይሆን ከማሽላ ከአዝመራ ውስጥ የዋለ ገበሬ፤ ማታ ሲመስል ለልጆቹና ለሚስቱ፤ ወይም ለእናቱና፤ ለአባቱ እሸትና፤ ጥንቅሽ ይዞ ካልሔደ እንዲሁም ከገበያ የዋለች እናት ለልጆቿ ሎሚና ሸንኮራ አገዳ ወይም ሱኳርና ይህን የመሳሰለውን ይዛ ካልተመሰለች ለተቀበዮቹ መሆኑ አይቀርም።

በእኔም እንደዚህ ያለ ነገር እንዳይደርስብኝ አጥብቄ ልማር አልሁና፤ በትምህርቴ ላይ ስትኲራኲር እንዲህ የሚል ቃል በጆሮዬ ይንጐድድ ጀመር።

ዕድሜ ለኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያ በወጣቶቿና በተራሮቹዋ ላይ የሥልጣኔ ጮራ ታየ። ድንቁርና ቁርበቱን ጠቅልሎ ተሰደደ። የቀድሞውም አሮጌ አሳብ ሁሉ ተወገደ። አስናፊና አሰናካይ ልማድ እንኳን ከልጅ እግሮቹና ከሽማግሌዎቹም ቢሆን ቀርቷል። ስለዚህ በኢትዮጵያ ቀዋሚ ነገር ተመሥርቷል። ዛሬ እንደ ዱሮ አይደለም። ማናቸውም ነገር ተሻሽሏል። መለያየት ቀርቷል። አንድነት ሰፍኗል። ዕውቀት ከወጣቶች ጋር የባለ ቃል ኪዳን ጓደኛ ሆኗል።

ባስተሰሰብም ባነጋገርም ባሠራርም ባኗኗርም ባስተዳደርም ባለባበስም የኤኮኖሚ ጉዳይ በማወቅና ጊዜን በመጠን ልክ በመፍጠር ሁሉን ነገር እንደ አስፈላጊነቱ ለማደራጀት የሚቻልበት መንገድ ተዘርግቷል።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥልጣኔ ያመጣው የጊዜው ዕውቀት ከሕፃናት ጋር ጡት አጣቢ ሁኖ እንዲያድግ በዕውቀት ያደገው ወጣት በተራራው ኢትዮጵያን እንዲያሳድግ ለሰውም ለሀገሩም የአስተዳደሩን ዘዴ አስናድተዋል።

Join us on Telegram @amharicbookss

በጃንሆይ ትግል አገራችን ኢትዮጵያ የኤውሮፓ አምሳያ ትሆን ዘንድ ዕድሏ ፈቅዷል። ድንቁርናን ስንፍናንና መታከትን ዙሮ የሚያየው አልተገኘም እየተባለ የሚያወራ ተላላፊ ድምፅ እየተመመ መጥቶ ያለሁትን ቤት ሞላው።

በዚህ ጊዜ የተሰማኝ ፍሥሓ እጅግ የበዛ ነበር። በዚህ ስደሰት እንዲሁ ደግሞ የደስታ መዓዛ ዓየር በምዘዋወርበት መንገድና በምውልበት የትምህርት ቤት ይከበኝ ጀመር። መልካሙ ሽታው እውድ እውድ አደረገኝ። እኔም ሕሊናየን ከፊት አድርጌ አየሩን ስቀበል እንደ ደወል ያለ ድምፅ ይሰማኛል። ልቤም ዷዷ ይላል። የልቤ ላይ የደም ትርታ ይዘላል። ጆሮየንም አሳከከኝ ከቶ ምን ያሰማኝ ይሆን ብዬ ተጨነቅሁ። ወዲያው «ኢትዮጵያ ደስ ይበልሽ። የብርሃንሽ ጊዜ ደረሰልሽ» እያለ አንድ መልአክ የመሰለ መልከ መልካም ጐበዝ በፊቴ ቆሞ የምስራች ሀገርህ ብርሃን ወጣላት እያለ ሲያጫውተኝና ጨዋታችንም ሳያቋረጥ ግርማዊነታቸው ፲፱፻፳፫ ዓ.ም ጥቅምት ፳፫ ቀን ንጉሠ ነገሥት ሆኑ። የዓለም መንግሥት እንደራሴዎች ሔደው የንጉሡን በዓል አከበሩ በኢትዮጵያ ታላቅ ታሪክ ታየ። ምድር ዕልል አለች። ተራሮች አሸበሸቡ። ኰረብቶች አጨበጨቡ። ኢትዮጵያ ደስታዋን እንኳን ለምድርና ለሰማይ አካፈለችው። በዚህ ቀን ከዚህ ቀድም ያልተደረገ ደስታ ተመሠረተ።

ኢትዮጵያ እቴ ሸንኮሬ

ጫጉላሽ አብቧል ዛሬ።

አሼ ወይና ለምለም

እንዳንቺ የለም።

ሾላዬ ሾላዬ

ፍሬውን በልቼ ዛፉ ከለላዬ።

እረ ስማ አገሬ

ደስ ብሎኛል ዛሬ።

እየተባለ ተገጠመ።

Join us on Telegram @amharicbookss

ነገሪቱ በየተራራዎቹ ተጐሰመ። የኢትዮጵያ ሕዝብ በመላው «ይደልዎ ይደልዎ ሲል ድምፁን ከፍ አድርጐ አሰማ። ኢትዮጵያ ከዚያን አስቀድሞ ቀን ለቀን መብራት እያበራች ሰው ስትፈልግ ነበር። በዚህ ቀን ግን ያን የፈለገችውን ሰው አገኘች።

እንደተመኘሁ እንደተመኘሁ

አንተን አገኘሁ፡

የወይን አበባዬ የወይን

እኛም ወደናል ይሁን።

ተብሎ ተዘፈነ የሚል ወሬ ስለ መጣልኝ በዚህ ጊዜ የነበርሁበትን ደስታ ምን ብዬ ልናገረው እንዲያው ዝም ነው።

ከምድር የሆንኩ ከሰማይ አላወቅሁትም። በመንፈስ ዓዜን ጠቅልዬ ክንፎቼን አራግቤ ከንግሥ በዓሉ ለመካፈል ተነሣሁ። ገና ከሀገሩ ስነሣ ከዚያው የቀረው ልቤ በቅጽበት ደረሰና ዕድል ቀረብህ። በኢትዮጵያ ላይ ውቅያኖሳዊ የሆነ የደስታ ጐርፍ ጐረፈ። የንግሥ በዓሉ በተከበረበት ቀን የተሰበሰበው ሰው ያለ ልክ ብዙ ነበር።

ምድር አጌጠች። እንጨትና ደንጊያው ተሸለመ። ቤቶች ሁሉ ሙሽራ መሰሉ። የሰማይ ጭፍሮች እንኳ ሳይቀሩ ከበዓሉ ውስጥ ውለዋል። የኢትዮጵያ መንግሥትና የግርማዊነታቸው መንበረ ዳዊት ታይቶ በማይታወቅ ክብር ከብሯል። ኢትዮጵያ እንደ ዛሬ ደስ ብሏት አያውቅም። እረ ታሪኩ ብዙ ነው። ምንም ቢሆን በቃል ተወርቶ አያልቅም። በዚያም ቀን ዓይን ከታሪክ ጠግቦ ዋለ። ጆሮም የደስታ ቃል በመስማት ረካ።

ምንም ታሪኩን እንደዚህ አድርጌ ብነግርህ አንተም ያየህ ያህል ብትረዳው መስማት እንደ ማየት አይሆንም ብሎ ቢያጫውተኝ፤ በነፋስ ጋልቤ ክንፌን አራግቤ ለመሔድ ምንም ብመኝ የኤውሮፓን መሬት ለቅቄ ከኢትዮጵያ መሬት ለመገኘት ባለመቻሌ አዘንሁ ሃሳቤ ግን ሔዷል። እኔም

Join us on Telegram @amharicbookss

ወዲያው ወዘኔ ወዘኔ

ነፋስ አወዛውዞ በጣለሽ ወደኔ

እያልሁ ስለ ሀገሬ ደስታ እወዘወዝ ጀመር።

ከደስታዬ የተነሣ ባጠገቤ ሁነው አኳኋኔን ለሚመለከቱት

እንዲህ ስል እተርክላቸው ጀመር።

የእናት አገሬ ስሟ ብዙ ነው። ከዚህም ጥቂቱ የሚከተለው ነው።

የዓለም ስሟ ኢትዮጵያ

የመጽሐፍ ስሟ አግዚእ ጎረያ (አምላክ መርጧታልና

የማዕርግ ስሟ፤ አግዐዚት (እመቤት ናትና

የፈረስ ስሟ፤ መዋዒት (አሸናፊ ናትና

ይባላል ስለ አልጓቸው በጣም ተገረሙ። እነሱ በዚህ ሲገረሙ፤ እኔን ደግሞ ገረመኝ። ይህን ከዚህ በላይ የተገለጸውን የምሥራች ጆሮዬ በሰማ ጊዜ ደስታ መላውን አከላቴን ወረረው። ይህን የምሥራች አነጋጋሪ አድርጌ ተቀምጬ ሳለ የአሳቤ መደገፊያ መካም ምኞት መጣና ሁለተኛ አነጋጋሪ ሆኖ እህ ይኸውልህ እንዲህ ሆነ መሰንበት ደግ ነው እንዲህ ተደረገ። ለኢትዮጵያ ቀን ወጣላት በጠላት ጆንበር ጠለቀበት። እንግዲህ ምን አለ። ብሎ ከሥልጣኔ ድንበር መድረስ ነው። ኢትዮጵያ ትመኝ የነበረውን ብርሃናዊ መሪ ካገኘች፤ ከእንግዲህ ከዚህ ቀደም ከሰማሁትና ከተረዳሁት ውበት ከኤውሮፓ ጥበብ ምን ይቀርባታል። ከ፱፻፱ ዓመተ ምሕረት በፊት የነበረው የዱሮው ልማድ ወጣቶችን ተከትሎ ለሚመጣ ሥልጣኔ ሥፍራ በጭራሽ ይለቃል። ያየር መብረሪያ አኤሮፕላን የባሕር መንሳፈፊያ መርከብ፤ የመሬት መሽከርከሪያ ባቡርና፤ ልዩ ልዩ መኪና የሕግ ትምህርትና የሕክምና ብልሃት የመድፍና የታንክ የመትረየስና የጠመንጃ የማናቸውም ብረታ ብረትና የእንዱስትሪ አሠራር በኢትዮጵያ ይስፋፋ። ብዙ ትምህርት ቤት ይከፈታል። ብዙ ወጣት ከትህርት ይወለዳል። ምን ጠፍቶ። ምን ታጥቶ። ኢትዮጵያ እንደዚህ ያለ መሪ ካገኘች ሥልጣኔም

Join us on Telegram @amharicbookss

ካስገባች ልጆችንም በዕውቀት ካጐለመሰች ጠረፍዎቿ ሁሉ ተመልሰውላት ባዕድ ሳይገባበት አገርዋ ሳይከፈልባት ከፍ ባለ አስተዳደር ትኖራለች በማለት በትንሹ ኩሬ ሣይሆን በጥልቁ በቀይ ባሕር ዋኝቶ ይወጣ ዘንድ የልቤን ተስፋ ለቀቅሁት።

ስምንተኛ ክፍል።

በእንደዚህ ያለ አለኝታ ስኖር።

የዚህ ትዝታ ስተኛ እያበነነኝ ስነቃ ሰመመን እየሆነብኝ ምነው ሆኖ አይቼው። በማለት፤ ስትከነከንና ያየኋቸውን መልካም መልካም የስልጣኔ ሥራዎች ሁሉ ለሀገሬ ስመኝና በእንደዚህ ያለ አለኝታ ስኖር ሰላም እንደታመመ የፋሽስት እብድ ውሻ እንደ ለከፈውና በዚህም ልክፍት ለሕይወቱ የሚያሠጋው ነገር በዓለም እንደ ተቀሰቀሰ ሰምቼ ዋ ሰላም። እንዲህ ሊሆን ነው። እንግዲህ ለዓለም ምን ሊበጀው ይሆን። የዛሬ ዘመን ሰላም የይሁዳን ሰላም ሆኗልና ለዓለም እግዚአብሔር ይሁነው።

የዤኔብ ማኅበርሳ ስለ ዓለም ሰላም የጤና ጥበቃ መከላከያ አላደራጀ ይሆን ከቶ ለዚህ መድኃኒት ቃጣለትን። እንግዲያ የዓለም መንግሥታት ለምን ደከሙ። ሰላምንማ ከመሽታው ለማዳን ካልታገሉ። የፋሽስት ወይም የናዚስት ወሮ በላ የንዳድ በሽታ ሆኖ ዓለምን ሳያንቀጠቅጠው እንዴት ይቀራል፥ እያልሁ በዚህ አሳብ ስዋኝ፤ የይግረመው ነው መሠለኝ በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም ጣሊያን ፋሽስት የኢትዮጵያን በሥልጣኔ መፋጠንና ወደ ትልቅ ደረጃ ለመድረስ በዕውቀት መንገድ መገሥገሥ፤ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥትንም ታላቅ ታሪክና ትጋት ስለ ሰማች፤ ለዚህ እንቅፋት ለመሆንና በግፍ የሥልጣኔያችንን ዕድገት ባጭር ለማስቀረት በምቀኝነትና በተንኮል በአጥቂነትና በግፍ ኃይል ተነሣታ የኢትዮጵያን ወሰን አልፋ በወልወል ላይ አደጋ ጣለች። በዚህ ምክንያት ጦርነት ሊሆን ነው የሚል ወሬ በየ ጋዜጣው ሁሉ ያጋጥመኝ ጀመር።

በለምለም መላሴ ደንደሮ በላሁበት እንደሚባለው ሁሉ የሀገሬን ልማት በሰማሁበት ጆሮዬ የሀሬን ጥፋት መስማቴ ታላቅ አደጋ ሆነብኝ። አዘንሁ። ተበሳጨሁ። ፊቴን እንኳ ለመንጨት አሰብሁ። ነገር ግን ያለሁበት የፈረንጅ አገር ነውና። አገር እንዳላሰድብ ብዬ ሞከር አድርጌ ተውሁት። ይሁን እንጂ አላስችል ስለ አለኝ ተደግፌው የነበረውን ጠረጴዛ በጡጫ መታሁት። በዚሁ ጊዜ

Join us on Telegram @amharicbookss

ባጠገቤ የነበሩት ሰዎች እንደ ዕብድ አዩኝ። ጉዳይ አላልኋቸውም። በዚህ ታላቅ ብስጭት ሳለሁ ባለሁበት አገር እንደ ገና አንዳንድ ወሬ ይሰማ ጀመር።

የኢትዮጵያ የአቤቱታ ድምፅ በዤኔብ ማኅበር በተሰማ ጊዜ እንዳልተሰማ ያህል ይገመት ጀመር የጠቡ ነገር በዕርቅ መንገድ እንዲፈጸም ኢትዮጵያ ምንም ፈቃዷ ቢሆን ፋሽስት ጦርነቱ ከመቀጠል አልታገደም። የዤኔብም ጉባኤ ፍርድ ሊሰጥ አልቻለም የሚባለው ወሬ ንፍስ ንፍስ ሲል እስከ ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ደረሰና ለዋናው ጦርነት መደራጀት ሲጀምር ብቻዬን ሆኜ እህህ እል ጀመር። እንዲህ እያልሁም በገናየን ይዤ ያንኑ የዱሮውን እንጉርጉሮ አንጐራጉር ጀመር።

እህህ ነውና ያከሳው ደረቴን

ሳልበላ መቼ አደርሁ አንድ እንጀራ ራቴን።

እትት በረደኝ ነቱ ቀዘቀዘኝ

ካገሬ ከወጣሁ ምንም ሙቀት የለኝ።

ሰው ያለ ጊዜያቱ የሚመኘው ሞቱን

እየተቸገረው ነው እያጣው ብላቱን።

ብቻዬን ስሔድ ተከትለህ

እህ ምን ትለኛህ።

ሁሉ እየቤቱ ሲበተን

እህና እኔ ቀረን።

እስከ መቼ ነው የኔ እህታ

ስማኝ አምላኬ የኔ ጌታ።

ዓለም ከፍርድ ተሳስቷል

Join us on Telegram @amharicbookss

ይግባኙ ሁሉ ለአንተ ቀርቧል።

አስጥለኝ ብዬ ብለምንህ

ምነው እኔኑ ማስጣልህ።

ላንተ የሚሳን የለምና

እባክህ አውጣኝ ከፈተና።

እርዳኝ ተራዳኝ ፈጣሪዬ

አንተ ነህና ተስፋዬ።

እባክህ ጌታዬ ሎሌህን እገዘኝ

ግፍ ተሸክሜአለሁ እስኪአይንገዛግዘኝ።

ቀንበር ያዘልሁባት ጀርባዬ ጐበጠ

ግፍ የሰማሁበት ጆሮዬ ተላጠ።

እባክዎ ጌታዬ ደህና ዘመን አምጣ

የወጣ እንዲገባ የገባ እንዲወጣ።

በዚያም እህና እኔ ተቀምጠን ዋ ከቶ የኢትዮጵያ ነገር እንደምን ሆኖ ይሆን። ከድኽነት ሁሉ የሀገር ደሀ መሆን ታላቅ ጉዳት ነው። ርጉም ጠላት ሀገሬን እንዳይረግጣት ምነው አምላኬ እግሩን በሰበርክልኝ።

በኢትዮጵያ ሥልጣኔ ለመግባት ሲቀዳደም፤ ወጣቶቻችንም፤ እኩሉ በቡቃያነት፤ እኩለ፤ በአበባነት፤ እኩሉ በፍሬነት እንዲሁም እኩሉ ገና ለትምህርት በመደራጀት ሳሉ፤ ይህ የጠላት መነሣት የተጀመረውን የሥልጣኔ ድቅን ሁሉ ለማጨናጐልና ባገራችን ላይ መጥፎ ተውሳክ ለማምጣት ስለ ሆነ፤ ከቶ ምን መሆን ይሻላል።

Join us on Telegram @amharicbookss

ዋ ሀገሬ እንደ እንጀራ ጠቅልየ እንዳልጐርስሽ ወይም አንቺ አንከብክብሽ እንዳትጐርሽኝ ያለሁት በባዕድ አገር ነው። ያ የዘለዓለም ደመኛችን ፋሽስት አፍሮ ይመለሳል እንጂ ምንም ቢሆን የኢትዮጵያን ነፃነት ደፍሮ በደኅና አይቀመጥም። ተራሮቿ ቢሆን የኢትዮጵያ ነፃነት ደፍሮ በደኅና አይቀመጥም። ተራሮቿ እግዚአብሔር ለኛ ነፃነት መከላከያ ሲል የመሸጋቸው ናቸው አርበኞቿ የማይጣሱ የአምላክ ግምቦች ናቸው። ይልቁንም ንጉሠ ነገሥቷ በፖለቲካም በጦርነትም በማናቸውም ወገን በሰልፍና በኃይል የመጣባቸውን ተቃዋሚ ሁሉ ድል አድርጎ ለመመለስ እግዚአብሔር በክንዱ የደገፋቸው በመሆናቸው ኢትዮጵያ እንደ ተጠቃች አትቀርም።

ምንም የሚያሰጋን ነገር የለም እያልሁ በገናዬን ስደረድርና ሳንጐራጉር በጣም የምታምርና ግርማ ያላት የሚያስፈራ የጦር ልብስ የለበሰችና ጣምራ ጦር የቃጣች፤ በዳማ ፈረስ ላይ የተቀመጠች፤ የአንበሳ ጐፈር በራሷ ላይ ያሠረችና የአንበሳ ለምድ የደረበች የፈረሰኛ ሱሪ የታጠቀች ፍቷ ቄጣ ያለ ወይዘሮ መጥታ።

ብታመም እድናለሁ እንጂ አልሞትም

እግዚአብሔር ቢገሥፀኝም

ለሞት አሳልፎ አልሰጠኝም።

መክበቡንስ ከብበውኛል

ነገር ግን ድል ነሳኋቸው በእግዚአብሔር ኃይል።

የተባለው የዳዊት ቃል ይፈጸምልኛ ወርቅንና እንደወርቅ ያለውን ጥሩ ነገር ፈተና አያጣውም።

የዓይኔ ብርሃን የነፃነቴ ዓይን በማይ ጨው መካከል በጦር ሜዳ ላይ ተሰልፎ፤ እሞታለሁ ብሎ በቆረጠ ጊዜ ማይ ጨውን የዌተርሎ ዕድል እንዳይገጥማት አጥብቄ ፈርቼ ነበር። ማይ ጨውን ግን ከዌተርሎ የተለየ ዕድል ስለ ገጠማት የጀግናውና የስመ ጥሩ መሪያችን እጅ እንደ ናፖሊዮን እጅ በባዕድ እጅ አልገባም። ወይም የመሪያችንን ሕይወት ያለጥርጥር በግርማ ቀርቦ የነበረው ሞት ሊያገኘው አልቻለም።

Join us on Telegram @amharicbookss

አንበሶችን በግርማ ተመለሰ። ታማኞቹም «ኰሎ ኅደግነ ወተሎናከ» ሲሉ ሐዋርያት ክርስቶስን እንደተከተሉት። እኩሎቹም «ካንተ ከተለየን ዓለም ለምናችን» እያሉ ከመንደር ወደ ዱር ተሰደዱ። የቀሩትም በውስጣዊ ስሜታቸው ማቅ ለብሰው አመድ ነስንሰው በኀዘን ተጠመዱ። ስለዚህ ነው እንደገና ድል አድራጊነቴን ያወቅሁት። ከጦር ሜዳ ስመለስ ድል የመሆን መንፈስ አልስተሰማኝም እያለች ያላትን ተስፋ በነበረችኝ ጊዜ ከብዶኝ የነበረው ጭንቀቴ ቀለል አለኝ።

ከዚህም አያይዛ የአቤልን በግፍ መሞትና የደሙን ድምፅ ያደረገውን ስትሰማ ለጊዜው ቃየል ርኡድና ጽንጉጽ ብኍንና ብኩን ሆኖ ከኖረ በኋላ በመጨረሻው ምን ሆነ? ማወቅ የሚያስፈገውን ይህንን ነው። ቃየል የሞተው በሰው እጅ በደንጊያ ተወግሮ፤ ያውም በዕውር እጅ ነው። ይልቁንም የሚያስገርመው በልጅ ልጅ እጅ መገደሉ ነው። ወንድሙን የገደለ በልጅ ልጅ ሲሞት አያስገርምም።?

ኢትዮጵያንም ለጊዜው ገደልን ያሉ እስከ ዘለዓለሙ ሳይሞቱ አይቀሩም ስትል፤ ሁሉ በሠፈረው ቁና መሠፈሩን በቆፈረው ጉድጓድ <u>መቀበሩን ነግራኝ ሔደች።</u>

ዘጠነኛ ክፍል።

ግርማዊነታቸው በኤውሮፓ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ኢትዮጵያን እንደ ገና ለመመሥረትና ጠላትን ለማባረር ሕዝባቸውን ለመታደግና አገራቸውን ነፃ ለማውጣት ባሉበት አገር ጦርነቱን ቀጠሉ። ቃላቸውን ለአርበኞችና ለመላው ዓለም ሳያቋርጡ አሰሙ።

ከሎንዶን ወደ ጄኔብ ሔደው፤ በጉባኤው ቆሙ። ከቶ ያቺ የጄኔብ ጉባኤ ዛሬ ምን ይመልስላት ይሆን። ለመውረር ለማሸበር ለጥቃትና ግፍ ለመሥራት ለማናቸውም ለዓመፅ ሥራ ሁሉ የተነሣው ፋሽስት፤ በኢትዮጵያ የአረመኔነት ሥራ መሥራቱንና ለወደፊቱ ለኤውሮፓ አኳኋን ሰፊ አስተያየት ያለበትን ልብ የሚነካ ንግግር ሲናገሩ ለጊዜው ጉባኤው ቃላቸውን አዳመጠ። ከንፈሩን መጠጠ። ማለት በከንፈሩ አለቀሰ። ልቡ ግን ዕንባ አልወጣዉም። ለተጠቃ መንግሥት የበሰላ ዋስ ሆኖ የሚታገትና የሚታገድ ዋስ ጠፋ። ሰብአዊ ሕግ አፉን ያዘ። አምላካዊ ሕግ ግን፤ ፍትሐ ነገሥቱን አውጥቶ፤ ፍርዱን ለመስጠት ስለ ተሰናዳ፤ ፋሽስት በሕግ ፊት የሞተው ከታሪክ እብፊት እንደሆነ ታሪክ ራሱ መታዘቡ አልቀረም። ግርማዊነታቸውም

Join us on Telegram @amharicbookss

ይህን ነገር እግዚአብሔርና ታሪክ ይፈርደዋል» ብለው ወደ ሎንዶን ተመለሱ። ጉባኤውም የክብር ቃሉን አዋርዶ ስሙን አጥፍቶ ነግ በኔን ይጠባበቅ ጀመር። ጃንሆይ ግን ዓለም ምንም ተስፋ ቢያስቆርጣቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ያላቸውን ተስፋ ሳይቆርጡ በትግላቸው ጠነከሩ። ኢትዮጵያን ለማጥቂያ የተሰለፈውን የጦር ኃይል ለማሻርና የምሽጉን ቁንዲ ለመናድ ብቻቸውን ተሰለፉ። የአጥቂዎችን ኃይል ደጋፊ የነበረው ዓለም ግን ይህን ጥንካሬ ይህን ብርታት ይህን ጋሻኝነት ለጊዜው እንደ ሞኝነት ሳይቆጥረው አልቀረም ነበር።

ፋሽስቶች በበኩላቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያደርጉት ፕሮፓጋንዳ አንሰዋቸው የድፍረታቸው ድፍረት ቆራጡንና ገምናናውን ጋማውን ሳያስተኛ አንድ ቀን የጠላቱን ሻኛ በጡንቻው ለማዳሽቅ እንደ ተቆጣ አንድ ተጀነነ እንደ ተኰፋነነ በሙሉ ተስፋ ሁኖ የሚጠባበቀውን አንበሳ በቀፎዋቸው ለማግባት አሰቡ። ከቶ ይህ አሳብ ካልተከናወነ ኢትዮጵያ የኃይለ ሥላሴ እንጂ የሙሶሊኒ እንዳልሆነች በእርግጥ ተገነዘቡ።

ታዲያ ምን ይሁን ጠቅል እንደ ሆነ እንኳን ማህል ኢትዮጵያንና ሌሎችንም የኢትዮጵያ ቀመስንና ነክ የሆኑትን ሁሉ ለመጠቅለል በዕድል ላይ ያለ ነው። ከንፈር ቢነክሱት አልሆነም። ጉራ ቢነዙት አልተሳካም። ውሸት የስህተቶችን ቀዳዳ ሊደፍን አልቻለም። ሱሪያቸው ከጉልበታቸው እየበነነ ሔደ። ኮታቸው ከክንዳቸው ተቦጫጨቀ። መለዮአቸው ከግንባራቸው እየወረደ ዓይናቸውን ሸፈነው። አሰናኦር ግንብ ለጦር ኃይላቸው ሁሉ የመፈራረስን ዜና ያረዳው ጀመር።

ዋ ይህ ሁሉ የሆነው በምን ምክንያት ነው።?

መ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በውጭ አገር ሳሉ ሥራ ባይፈቱና ያሰናዱት የጦር ፕላን የተሳሳተ ባይሆን ነዋ። ሁለተኛም ባገር ያሉት ጀግኖቻቸው የጃንሆይን ቃል ዓላማ አድርገው ትግላቸውን ባያቋርጡና ትጥቃቸውን ባይፈቱ ነው።

የዓለም ራዲዮ ያደነቆረና ተራሮችን ያናወጸ መስሎ እንደ ነጐድጓድ ይነጉድ የነበረው የጣቶች ዲስኩራቸው የገደል ማሚቶ ሁኖ ቀረ። የማንንም ጆሮ ሳያደነቁር በለጥዎሳስና በቃለ ሕሊና ለአምላክ የተነገረው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቁርጠኛ አሳብ ግን አሸናፊነትን ወሰደ።

Join us on Telegram @amharicbookss

እንግዲህ የማን አሳብ ቀልሎ ቀረ። የቀለለውን ታሪክ ነግሮናል። በክብደቱም ድል ያገኘውን ታሪክ ነግሮናል። በክብቱም ድል ያገኘውን ታሪክ አስረድቶናልና ይህን አቆይተን <u>የአፍሮ አይገቤን ታሪክ እንቀጥላለን።</u>

ዓሥረኛ ክፍል።

አፍሮ አይገቤ።

አንድነቱን የጠበቀ ዝምድናውን ያጠበቀ በጀግንነቱ የታወቀ ሕዝብ ጠላቱን አሳፍሮ እንጂ እሱ አፍሮ አይገባም። ቢወድቅም እንደ ወደቀ፤ ቢጠቃም እንደ ተጠቃ አይቀርም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ኩሩ ስለ ሆነ ውርደትን አይቀበልም። እንኳን ራሱና ሌላው ሊጠቃ የማይወድ በመሆኑ፤ በክብሩ ላይ ታሪክን ከሚያጐድፉ ነገሮች አንዲቱ ነጥብ እንኳ ብትሆን ብታርፍበት አይፈቅድም።

ንጽሕናና ቅድስና ማለት ነፃነት ነው። እነዚህን ሁለት ነገሮች ርስሐተ ኃጢአት ሊነካቸው እንደ ማይገባ ነፃነትም ጥቃት ሊነካው አይገባም። የኢትዮጵያም ሕዝብ ነፃነቱ የሚመለከተው እንደነዚህ ሁለት ነገሮች፤ ከቶውንም ከነሱ አብልጦ ስለ ሆነ ሞቱን ከሕይወት አያሳንሰውም። ሕይወቱንም ከሞት አያበልጠውም።

ቢሞትም ለሀገሩ፤ ባይሞትም ለሀገሩ ነውና፤ ወረራዎችና ግፎች በሱ ዘንድ ኢምንት እንጂ ሌላ መልክ የላቸውም።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ንጉሠ ነገሥቱንና አገሩን አፍቃሪ፤ ለነፃነቱ ሙዋች፤ ለታሪኩ፤ መካች ባሠማሩት የጦር ሜዳ ድል አድርጊነት አፍሮ አይገቤ መሆኑን እያወቀው ፋሽስት ምን አደከመው። ዋ እንዲያው እኮ ድክም ብሎ ነው። ዘር ይሔዳል እንጂ እርሻ አይሔድምና ሂዶ አፈር በልቶ ወይም አፈር በልቶ ሊቅር ይሆናል እንጂ በደኅናው አላንቀዠቀዠውም።

ጠላት ከዚህ ቀደም በ፲፰፻፹፰ ዓ.ም አድዋ ላይ ተዘርቶ ሳይበቅል ተወቅቶ ፍሬ ሳይገኝበት መቅረቱን ምን ጊዜ ረሳው። የትናንቱ ለዛሬ ምን ጊዜ ተረሳ። የዚያን ጊዜም እንደ ዛሬው ብዙ የጦር መሣሪያ ነበሩት። ለወረራም አመጣጡ በግፍ ነበር።

Join us on Telegram @amharicbookss

እግዜርንም አላውቅም ኢትዮጵያንም አልለቅም ሕግ አያግደኝም ፍርድ አይመልሰኝም ብሎ እሳት ሆኖ መጥቶ የእሳት ልጅ አመድ የተባለው አልተፈጸመበትምን። አሁንም እንደ ሚፈጸምበት ታሪክ ነቢይ ነው።

ጅብ እንኳ ወደማይውቁት አገር ሔዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል ይባላል። ሲያውቀንና ስናውቀው እንደዚህ ምን ቅብጥ አደረገው።

የጥንታዊቱና የውዲቱ ኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪክ ጐዳና የሚገኘውን ታላላቅ ፈተና መውጣት እንደሚያስፈልገው ያውቃል። ዳገቱን ካልወጡና ቊልቊለቱን ካልወረዱ ምቹ ሜዳ አይገኝም። እንግዲያው እንግዲህ ከሆነ ምን እንላለን። ምነው እንል። ነገር ግን የምንለው አንድ ነገር ብቻ አለ። ድል የእኛ ብቻ መሆኑን ማወቅ ነው። እኔ ለሀገሬ ነቢይ ነኝ ሀገሬም ለኔ ጥንተ ሕይወቴ ናት።

አሳቤ አንተ እኮ ታዛቢ ነህ። ጆሮህን ጣል አድርገህ እንደ ዋዛ ታዳምጠኝ ይሆናል። ይህ ትንቢት ሳይፈጸም የቀረ እንደ ሆነ ኋላ ምን አለ በለኝ። እንዲያውም ከመላሴ ጠጉር ይነቀል እያልሁ ይህን ሁሉ በማሰላሰልና ከቶ ጦርነቱ ከምን ደርሶ ይሆን። በማለት ጥብጥ ኩርምት እያልሁ ስጨነቅ፤ ስጠበብ ወሬውንም ስናፍቅ፤ ፋሽስት መርዝ ረጮታ በግፍ መሣሪያ ተዋግታ በወራሪነት ወደ ኢትዮጵያ ገባች በሀገሪቱም ላይ ከዚህ ቀደም ተደርጎ ያልታወቀ እጅግ የከፋ የአረመኔነት ሥራ ተሠራ። አገር ተዘረፈ። ሕዝብ ተጨፈጨፈ። ሁሉም ለእሳትና ለጥይት ተዳረገ። ምንም የቀረና የተረፈ የለም ብሎ ወሬ ነጋሪው መርዶውን ገና ሲጀምርና ንግግሩን ሳያጋምስ በነገሩ መካከል የሀገሬ ቃጠሎ ዘተተኝ። የመከራው ስሜት አፌን ደም ደም ልቤን ባር ባር አለው። በዚህ የተነሣ ጥይቱ በደረቴ እሳቱ ባናቴ ያረፈ ያህል ቊስሉ ተሰማኝ። ጭንቅ ይዞኝ ከቆምሁበት ወደቅሁ። በወደቅሁበትም ፃዕረ ሞት እንደያዘው እንፈራገጥ ጀመር። ከዚያው ከወደቅሁበት ቀና ብዬ በወንበር ተቀምጬ።

የጥቁር ስንዴ ክምር

ሸክሊት (ጨበር) ናደችው ስትንር

ንሳ መልሳት ተይ መጨ

ነገር ካልሰሙት አይቆጭ።

Join us on Telegram @amharicbookss

እመቤቲቱ የእኔ እናት

ባሪያ ለማድረግ አሰቧት።

ሲያልፍ አይነካትም ባርነቱ

እሷ እመቤት ናት ከጥንቱ።

ከነስሟ እንኳ አግዐዚት

ስም ከታሪክ ጋር ያላት።

ሀገሬ ሀገሬ

ባንቺ ነው ማማሬ።

ወለላ ነች አገር ወለላ ነች

ሁሉን እንዳመሉ ትሰበስባለች።

የሰማይ አሞራ ልጠይቅሽ ወሬ

ተቃጥሏል መሰለኝ ሸተተኝ አገሬ።

ለጠፋው አገሬ ላለቀው ወገኔ

እርር ኩምትር ብዬ አለቅሳለሁ እኔ።

ዓይኔ ደም አውጥቶ ዛሬ ነው ማልቀሻው

ነፃነት ከታጣ ወዴት ነው መድረሻው።

ወገኔ አይምረርህ ጽዋውን ጨልጥ

ብረት ጦር አይሆንም ሳይቀጠቀጥ።

ኲሰን በጭካኔ የዋጠ ጉሮሮ

Join us on Telegram @amharicbookss

አፉን የሚያጣፍጥ አለው ማታ ዶሮ።

የመከራው ጽዋ የጭንቁ ገፈታ

ላለም ቀርቦለታል በተርታ በተርታ።

ይህ ፍርድ የተሰጠ ለኛ ብቻ አይደለም

ይቀባበለዋል ግልባጩን ሁሉም።

ነገር ግን እስከዚያው ፍርዱ እስኪለወጥ

ቃጠሎው አይወጣም ከቤታችን ውስጥ።

እባክህ ፈጣሪ ከባሕረ ምሕረትህ

ቅዳና አፍስስበት በሚነደው ሕዝብህ።

እጅግ በረታብን የቅጣትህ ጨንገር

እሳት ለንጨት እንጂ መቼ ለሰው ነበር።

የመርዝ ጦርነት ያውም ከላይ ካየር

አያውቅም ተደርጎ ያለ ዛሬ በቀር።

ይህን ክፉ ወሬ ከሰማሁ ጀምሮ

አእምሮ የሌለው ሁኛለሁ ደንቆሮ።

ሰውነቴ አለቀ፤ ኰሰሰ ቀጠነ

ገረጣ ወየበ ከሣ መነመነ።

ሥጋዬ አልቆ ደርቆ ፍቅፋቂው ቀርቷል

አጥንቴ ተራቁቶ፤ የሚለብሰው አጥቷል።

Join us on Telegram @amharicbookss

ተነሣ ጌታዬ ለምንት ትነውም

አቤት አቤት ይላል የፍጥረትህ ደም።

ጨነቀኝ ጠበበኝ እሆነውን አጣሁ

አግባኝ ወዳገሬ አልቅር እንደወጣሁ

እስከ ዛሬ ድረስ የባዕድ ወሀ ጠጣሁ

ከእንግዲህ አገሬ ተቀበይኝ መጣሁ።

እርጥቧ ለመለሚ ውቢቱ ሀገሬ

እመጣልሻለሁ ሁሉንም ተምሬ።

ክብርት ኢትዮጵያ ወይዘሮ ብርሃኔ

ካንቺ ከተለየሁ ቀርቷል ሰው መሆኔ።

እያልኩ ስጸልይ ስለምን አምላኬን

መጥጬ መጥጬ ጨረስኩት ከንፈሬን።

ሥጋየ አልቆ አንጥንቴ ብቻ ስለ ቀረ

እኔን ያየ ሁሉ ይገረም ጀመረ።

አለችኝ የምላት የማምናት ነፍሴ እንኳ

ጣጥላኝ ለመሔድ ተለወጠ መልኳ።

ወጋኝ ቆረቆረኝ ጐኔ ማረፊያ አጣ

እንዲህ ያለ ኑሮ ባፍንጫዬ ይውጣ።

ብላ ጠፍታ ልትሔድ መንገድ ስትጀምር

Join us on Telegram @amharicbookss

ጨርቋን በጇ ይዤ ሰጠኋት ምክር።

ልሒድ ልሒድ ማለት አይሆንም ይቅርብሽ

በዚህ በባዕድ አገር በንነሽ ትቅሪያለሽ

ቆረቆረኝ ያልሽው *(ወጋኝ የምትይው)* ይህ ቅዱስ አጥንት

የተፈጠረ ነው ከቅዱስ መሬት።

በሥጋየ ማለቅ ምን ያስገርምሻል?

ቀን በተገኘ ጊዜ ይመለስልሻል።

አንቲ ግን ከወጣሽ መመለሻም የለሽ

አርፈሽ መቀመጥ ነው አጥንትም ቢወጋሽ።

እያልሁ ስነግራት አዳምጣና ሰምታ

ምክሬን ተቀበለች በታላቅ ደስታ።

እያልሁ በበገና ሳንጐራጕር አንዳንድ ጊዜም በገናዬን ጣል አድርጌ ምድር ስጭር ቀኑን እውላለሁ። ሌሊቱም እንደ ቅኔ ቆጣሪ በአሳብ ስጨነቅ ዓይኔ ሳይከደን ፍጥጥ ብዬ አድረዋለሁ። ሲነጋም ያው ነው። ሲመሽም ይኸው ነው። እንዲሁ ስትከነክንና እህህ ስል ኅዘኑ ይብስብኝ ነበር። ዕንባዎቼ በመዓልትም በሌሊትም ሲመነጩ ለመወረድ አልበቃ ብሏቸው ፊቴን በመላው አላብሰው በከንፈሮቼ ላይ ሲዝቀዝቁ እየጣሱ ወዳፌ በመግባታቸው።

ሲሳየ ኮነኒ አንብዕየ መዓልተ ወሌሊተ የተባለው እንደ ተፈጸመብኝ ይሰማኝ ነበር።

ወሬውም መቀጠሉን አልገታም። ንጉሠ ነገሥቱ በዋናው የጦር ግንባር ተሰልፈው በታላቅ ጀግንነት ተዋጉ። በቆራጥነትም

Join us on Telegram @amharicbookss

ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው የተቀደሰ መሥዕዋት ለመሆን በምሥዋዑ ፊች ቀረቡ። ነገር ግን እግዚአብሔር ስላልተለያቸው ክፉ አልቀረባቸውም።

የኢትዮጵያ ትንሣኤ ይሆኑ ዘንድ ስለ ተመደበ ሕይወታቸውን ጠበቀ። መኳንንቱም ጳጳሳቱም ሊቃውንቱም ተሰብስበው፤ መብራታችን አታጥፉብን በማለት ስለ ለመኑዋቸው የጦሩን አቅድ ለመለወጥ ወደ ኤውሮፓ ተሻገሩ። አርበኞቻቸውም ባንድ በግርማዊነታቸው ቃል አሰማሪነት በየበረሃ ተሰማርተው ጠላትን ግን ወንድ ወንዱ ቁምጣውን ታጠቀ። ጠጉሩን ላይላጭ ብጽዓት አደረገ። ጸሎት ማድረሻ ዳዊቱን ጠላት መመለሻ ብረቱን አነገበ። ሞትን እንደ አልማዝ ጌት መንገላታትን እንደ ምቾት ቆረጠው። ቆልቶ እንጂ ጋግሮ መብላት ቀረ ከነጥሬውም የሚገኘው ብዙ ቀን በአክፍለት ጨብሶ እንደ አልማዝ ጌጥ መንገላታትን እንደ ምቾት ቆጠረው። ቆልቶ እንጂ ጋግሮ መብላት ቀረ ከነጥሬውም የሚገኘው ብዙ ቀን በአክፍለት ጨብሶ «እየታረደ ነው። ጀግኖቻችን እስከ አዲስ አበባ ድረስ እየሔዱ አስጨነቁት አንሸቀሸቁት።

ደጃች ፍቅረ ማርያም አባ ተጫን በምሥራቅ በኩል በአዲስ አበባ መካከል ገብተው በጥይት ቆሉት። አንገረገቡት። በሣንጃ ዘከዘኩት። ሸከሸኩት። ማ ማ ሚያ አሰኙት።

እንዲሁም በአዲስ አበባ ሰሜን ደጃዝማች አበራ ካሣ በአዲስ አበባ ደቡብ አባ ነፍሶ ባልቻ ተጠግተው መድረሻና መተንፈሻ እስኪያጣ ድረስ ፍርሃት ለቀቁበት። የት ልግባ። የት ልድረስ። አሰኙት። አዲስ አበባ እራስዋ አዲስ እሾህ ሆነችበት እንጂ ደስ በሚያሰኝ በአበባነት ባሕርይ አልተቀበለችውም። ስንቱን ልንገርህ። በሚያሰኝ በአበባነት ባሕርይ አልተቀበለችውም። ስንቱን ልንገርህ። በውጭማ ያለው ምን ይነገራል። እሾህና አሜከላ ይብቀልብህ የተባለው ስለ ተፈጸመበት መስክ መስሎት የረገጠው መሬት የዣርት ውስፌ ሜዳ መስሎት የሮጠበት ምድር ገደል እየሆነ

ወይ ጣጣ በዚህም አያስወጣ

ወይ መከራ በሁሉም ዳሞትራ

እስኪል ድረስ የገጠመው ጭንቀት ተነግሮም አያልቅ። ምድሪቱም ገራምነቷን ተወች። ሰላማዊነቷን ለወጠች። የነብር እመጫት ሆነች። ጋማዋን አስቆጣች። ጠላት ምንም በወራሪነት ቢገባ አልተመቸችውም። ምነው ወደ ኢትዮጵያ በመጣሁ ቀን እግሬን በሰበረኝ የማለት አሳብ አድሮበታል። ባብቷል።

Join us on Telegram @amharicbookss

ተምበድብዷል። ተንዘፍዝፏል። ድል መሆን አልቀረለትም። በዚያው ተውጦ ይቀራል። ከሦስት ዓመት ግፋም ቢል ከ፭ ዓመት በኋላ እጁን ይሰጣል። መሣሪያውን ያስረክባል የሚል ወሬ ደረሰኝ።

አሥራ አንደኛ ክፍል።
እኔው ሙቼ እኔው አልቃሽ አለ መሆኔ።

ይህንም የደረሰኝን ቃል ሰምቼ ምርር ብዬ ሳለቅስ ለቅሶየን የሰማ ኤርምያስ መጥቶ ያላቅሰኝ የሚሙሸኝ ጀመር። ሁላችንም ጨርቃችንን ጣልን። ማን ያረጋጋን ማን እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይበለን። ቢለንስ ምን ጥቅም አለው። አገሬ ጠፍታ በምን ላይ ነው የምጽናናው። ሀገሬ ትኩስ ሬሳ ሁና መጥታ በፊቴ ተዘረጋች። እኔም ተነሥቼ እዬዬ ልዘርጋ እያልሁ ለቅሶዬን አምባርቀው ጀመር። ወዲያው ምነው ክርስቶስ መጥቶ እንደ ኢያኢሮስ ልጅ ተነሽ ብሎ ባስነሣልኝ እል ጀመር። ከሚያውቀኝም አንዳንዶቹ እየመጡ ይብላኝ ለእርም እያሉ ልብሳቸውን እያራገቡ አላቀሱኝ። የእዝንም አገቡልኝ። መቼስ ምን ይደረጋል። አይዞህ እያሉ ያጽናኑኝ ጀመር። እኔ ግን ያልተነካ ግልግል ያውቃል በማለት ገመትኋቸው።

ጴጥሮስ በደብረ ታቦር ጫፍ መኖርን ስለ ወደደ አንድ ቤት ለሙሴ አንድ ቤት ለኤልያስ መሥራት ያስፈልጋል እያለ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ሠሪነቱን ሲያደላድል አሳቡ ሳይጨርስ ከወደላይ የነጐድጓድ ድምፅ ሰምቶ እንደ ወደቀና አሳቡም ተበትኖ እንደ ቀረ እኔም ተምሬ ወደ ዘመዶቼ ተመልሼ አገሬን ረድቼ ንጉሠ ነገሥቴንና ወገኔን አገልግዬ እኖራለሁ እያልሁ በአሳብ ሰሰናዳ እንደዚህ ያለ መደንግፅ የሆነ ቃል በመስማቴ የሚያብረከርክ ድንጋፄ ወደቀብኝ። እኔ ካሳቤ አሳቤ ከኔ ተለያየን። የኀዘኑ ስሜት የልብ ሥር ውጋትና የሆድ ቁርጠት ሁኖ እንደ ዲኦግኒስ በርሜል ያንከባልለኝ ጀመር።

እንደ ሎጥ ሚስት እንደ ደንጊያ ደርቄ ወይም እንደ ዮሳ ባለሁበት ፍግም ብዬ የምቀር መሰለኝ። ነፍሴም ከባሏ እንደ ተጣለች ሴት ልሒድ እያለች ታንገራብድ ጀመር። የሆነ ሆኖ ነፍሴ አንገራብዳ ከተመለሰች በኋላ ቁና ቁና ሙሉ ተነፈስሁ። ይሁን እንጂ አሁንም ነፍሴ መኖሯን እጠራጠር ነበር። ናባል በድንጋፄ ሞተ ሲባል ከታሪክ እየሰማሁ እንዴት ድንጋፄ ይገላል በማለት የነበረኝ ጥርጣሪ ለካስ እውነት ኑሯል አሰኘኝ። ነፍሴ ግን ጠንካራ ኑራ በመንፈስ ኃይል መኖሯን ካስታወቀችኝ በኋላ አብረን እንጨነቅ ጀመር።

በዚህ መከከል ፲፱፻፴ ዓ.ም መስከረም ፳፩ ቀን በሕልሜ በአዲስ አበባ ደርበ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ተገኝቼ በጸሎት ላይ ያለሁ ከቶውንም ቅዳሴ የማስቀድስ ይመስለኛል።

ዲያቆኑ በኀዘን ዜማ

እስመ በእንቲአሁ ይቀትሉነ ኵሎ አሚረ

ወኮነ ከመ አባግዕ ዘይጠብሑ

ንቃሕ እግዚኦ ለምንት ትነውም

ብሎ በሰበከ ጊዜ የምሥጢሩ አሳዛኝነትና የዜማው ስርቅ ርቅታ ሰውነቴን ሰበቀው። ቄሱ ወንጌሉ ብሎ ወጥቶ ከሉቃስ ወንጌል ከሁሉም አስቀድሞ ይዘው ይወስዷችኋል» ብሎ ከዚህ አያይዞ በምዕመናን ላይ ከአሕዛብ የሚደረገውን የመከራ ብዛትና የስቃይ ጽናት ማኅዘኒ በሆነ ቃል በሰማ ጊዜ ስሜቱ የጋለ ወስፌ ሆኖ ልቤን አንቸከቸከው። ምዕመናንም ሁሉ በዕንባ ሲዋኙ አየኋቸው።

እኔም ይህን ሁሉ አልሜ እንደ ገና ከሕልሜ ተመልሼ በእውኔ ሁኜ ስተክዝ፤ ወሬ ነጋሪው ገና ዜና መዓቱን ቀጠለ። ፋሽስቶች እንደ ሶምሶን ቀበሮዎች እሳታቸውን በጅራታቸው አስተሳስረው በያገሩ ገቡበት። እንደ ኤልሳዕ ድቦች በየመንደሩ ተራጩበት። ከዚህም በቀር የዓመቱን አጐራረፍ የመከራውን አቿጐዳጐድ፤ ምን ብዬ ላዋይህ። ዋ በየካቲት ፲፪ ቀን የሆነውማ ምን ተብሎ መርዶው ይቀርባል። ብሎ በነገረኝ ጊዜ በዚህ የተነሣ አገሬን ኢትዮጵያን እወቅስ ጀመር። በፊት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሲነግሡና ያን ያህል የደስታ ጐርፍ ሲጐርፍ በዚያው ተገኝቼ ሳልካፈልና ሳልሳተፍ ቀረሁ፡ ምንም ከዚህ ካለሁበት ድረስ ደስታው ቢመጣልኝ በአካለ ሕሊና እንጂ በአካለ ሥጋ ከዚያ ባለመገኘቴ ዕድሌን አምቼው ነበር።

አሁን ደግሞ ከሀገሬ መከራ ሳልሳተፍ ልቀር ነውን እያልሁ ስትከነከንና ስግመነመን፤ ከዚህ በታች ያለው ወሬ እግር በእግር መጣ። ተሰርቆ ከሕግ አፈትልኮ በተነሣው በፋሽስት ላይ ሰይጣን ነጋሪቱን ጨነ። ፋሽስታዊይቱ ኢጣሊያ አስረሽ ምችው አለች። የኢትዮጵያ ወንዝ ሁሉ ደም ይሆን ዘንድ በሊጋባዎቹ በነግራዚያኒ ቃል አዋጅ አናገረ።

በዚህ ምክንያት የሰው ደም በከንቱ እንዳይፈስ ወደፈተና አታግባን ተብሎ ምንም ቢጸለይ ወደ ፈተና መግባት ስላልቀረ፤ ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ የፈተናውን አወጣጥና አገባብ ደኅና አድርጎ ተማረ።

Join us on Telegram @amharicbookss

ወቦ ነጂ ጓዝ ሸካፊ ሆኖ የመጣውን የፋሽስትን ከተቲ ካቲ ካቲውን ቢሰብረውና ማጅራቱን ቢለው የበላውን ተፋው የጨበጠውን ጣለው።

ፋሽስት የኢትዮጵያን የልምላሜ ማማር አይቶ ቢዳብሳት የአንኮበር ቅጠል ሆነችበት። ለበለበችው። አንገበገበችው አንሰፈሰፈችው። አቃጠለችው። ዋይ ዋይ አሰኘችው። እያደርም መርዝ ሆኖ የማይሽር ቍስል ጣለችበት ሲል ወሬ ነጋሪው አጫወተኝ።

መቼም በባዕድ አገር ሁኖ ዋና ትምህርት የሚገኘው ከክፍል ወደ ክፍል በመዞርና የሚታየውን ነገር በማየት ነው።

ከዕለታት አንድ ቀን ወደ አንድ ትምህርት ቤት ሔጄ በየክፍሎቱ እየተመላለስሁ የትምህርቱን አያያዝ ስመለከት የጂኦግራፊ ትምህርት ከሚሰጥበት ክፍል ደረስሁ። በዚህም ጊዜ እንደ አጋጣሚ አንዱ አስተማሪ የኢትዮጵያ ሥዕል ያለበትን ካርታ ዘርግቶ «ይህቺ ኢትዮጵያ ናት። ዱሮ ነፃ መንግሥት ነበረች ዛሬ ግን የፋሽስት ይዞታ ሁናለ» ብሎ ሲተርክ በሰማሁት ጊዜ አእምሮዬ ሰከረ ናላዬ ዞረ። ዘልዬ ጕሮሮውን ላንቀው ወደድሁ። ሁሉንም ትቼው ስካሩ አዙሮ ጣለኝ። ከዚያም ተነሥቼ እንደ አሞራ በርሬ ወደ መኖሪያዬ ሥፍራ ሔጄ ሳብድ ስጠኸኝ ከምን ወይም ከማን አፍ እንደ ወጣ የማይታወቅ የሙዚቃ ድምፅ የሚከተለውን መዝሙር ይቃኝልኝ ጀመር።

> አወይ አደፋፈር ይሉኝታ ማጣት
>
> የጠቅልን አገር የፋሽስት አሏት።
>
> ይህን ታሪክ ብሎ ደፍሮ የሚያስተምር
>
> ተማሪ ነው እንጂ አይባልም መምህር።

የሚል በቀጭን ፉጨት በተስረቀረቀ ድምፅ የሚዘምር ረቂቅ የሆነ ልብ የሚመስጥ ቃል ካለሁበት ቤት ከጣራው ላይ ተሰማኝና ቀና ብዬ ሳዳምጥ።

> ክንዴ የወንዜ ልጅ የሀገሬ ሽታ
>
> ካንተ ጋራ እንዳንተ እኔም ልንገላታ።

Join us on Telegram @amharicbookss

አይዞህ ያገሬ ልጅ አትዘን ወንድሜ

በደጎና ከቆየህ ከዘገየህ በድሜ

አሁን ታየዋለህ የዚህን ፍጻሜ።

ጥንቱን ከፈጣሪ ሲፈጠር ይህ ዓለም

ግዛቱ በውሰን ሰዉ በደም ቀለም።

ደግሞ ነፃነቱ በሰንደቅ ዓላማ መንግሥት ሲቋቋም

ተለይቶ ነበር ገደብ ሆኖ ሰላም።

ሰላም ገደብ ሆኖ ሁሉን ባያቆም

ይጻጻፍ ጀመረ ባለደም በደም

እግዜር የተጣላው ግፈኛው ፋሽስት

የመጣ ቢመጣ ቢሆን ጦርነት

የሚጋፋኝ የለም ደረት ለደረት

እያለ ተመካ ደነፋ ፈከረ

ዓለም በጄ ብሎ አዋጅ አናገረ

ይህን ባደረገ ከጥቂት ቀን በኋላ

የኰራበት ጊዜው ያልፋል እንደ ጥላ

አለና የሙዚቃውን ቅኝት ዝግ ባለ በዜማ ድርስ አቆመው።

Join us on Telegram @amharicbookss

አሥራ ሁለተኛ ክፍል።

ስለ አበርኞች ብርታት።

ምንም ዋናው ከተማ በኢጣልያን ቢወረር ከኢትዮጵያ አብዛኛው አገር በአርበኞች እጅ በደሽ ተይዞ ነበር። ስለዚህ በኃይል ቢያቅተው በዕርቅ አባበለ። ነገር ግን ተንኰሉ ታወቀበት። ከወጥመድ ለመግባት የፈቀደ የለም።

የኢትዮጵያን ነፃነት ገፉት አልወደቀም። ገደሉት አልሞተም የሚል ጥርኘ ብርኘ ያለ ኀዘን ከፍሥሓ ያለበት ነገር ሰማሁ።

ከቶውንም

ያም ወርዶ ያም ወርዶ ዲቡን ነቀነቀው

ጐበዝን ደስ አለው ፈሪን ግን ጨነቀው

ሰማይ ቢንቀጠቀጥ ምድር ብትሆን ቁና

አገር እንደ ዋዛ መች ይለቀቅና

ጠላት በብረት ኃይል ቢመጣ አሰፍስፎ

ዳዊትን ሆነና የጠቅል ለፎ

ጐልያድን ጣለው ድንጋይ አወንጭፎ

ይገርማል ይደንቃል እጅግ ወገቡን ጠግኗል

ገበሬው መለሰው በድግር ቦምቡን

ነጭ ለባሹ ጣለው ብረት ለበሱን

ጀግና የጨበጠው ዕርፍም ሆነ ዱላ

ሰባብሮ ይጥላል የአገኘውን ሁላ

Join us on Telegram @amharicbookss

አልተገኘም እንጂ ያሸናፊነት ክብር

በጣም በዝቶ ነበር የፋሽስቶች በትር

ሠራዊት ቢበዛ መሣሪያ ቢንጋጋ

ከፈጣሪ ጋራ የለም የሚዋጋ

የሚል የአርበኞቻችን ቀረርቶ ሲአስተጋባ በኤውሮፓ ሰማይ ይሰማ ጀመር። ዋ አገሬ ካንቺ ብሆን ነበር እንጂ አሳቤን ብቻ ብልክልሽና የጀግንነትሽን ድምፅ ብቻ ብሰማው ምን እርዳታ ይሆንልሻል ዋ፦። አለኝታዬ ዙሮ መግቢያየ አንቺማ ከጠላት እጅ ወድቀሽ ለኢትዮጵያውያን ምን ሕይወት አላቸው። እህህ ያንቺ ነገር ብርድ ብርድ አለኝ። አንሰፈሰፈኝ አተኰሰኝ። በሽታ ሆነብኝ። እስከመቼውም ድረስ ጸጸቴ አይወጣልኝም እያልሁ ይህን በመሰለ ጭንቅ ተያዝሁ።

ከዚህ ላይ ደግሞ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ስለ ሕዝባቸውና ስለ ሀገራቸው ወደ ውጭ አገር ሔዱ ማለትን በሰማሁ ጊዜ በገና ምት ዐውቅ ነበርና ከዚህ በታች ያሉትን መዝሙሮች በበገና አንጐራጉር ጀመር።

ተዘክሮ እግዚኦ ለዳዊት *(ለኃይለ ሥላሴ)* ወለኲሉ የውሃቱ።

ዘከመ መሐለ ለእግዚአብሔር ወበፅዓ ለአምላከ ያዕቆብ።

ከመ ኢይበውእ ውስተ ጻላሎተ ቤትየ፤

ወከመ ኢየዓርግ ውስተ አራተ ምስካብየ፤

ወከመ ኢይሁቦን ንዋመ ለአዕይንትየ፤

ወኢድቃሰ ለቀራንብትየ፤

ወኢዕረፍተ ለመላትሕየ፤

እስከ እረክብ መካኖ ለእግዚአብሔር፤

ወማኅደሮ ለአምላከ ያዕቆብ፤

Join us on Telegram @amharicbookss

እስከ ማዕዜኑ ትረስአኒ ለግሙራ፤

እስከ ማዕዜኑ ይትዔበዩ ጸላዕትየ ላዕሌየ።

ንሣእ ወልታ ወኲናት ወተንሥእ ውስተ ረዲኦትየ እያልሁ ንጉሡ ዳዊት መጥቶ ፒያኖውን በኃዘን ቃና እየመታልኝ ሳንጎራጉር ጴጥሮስ መጣና ይህን የምትለውን አላውቀውም በል እያለ ሲፈታተነኝ ዶሮ ጮኸ። ወዲያው ጳውሎስ ከተፍ አለና የኃይለ ሥላሴን ፍቅሩን ማን ያስተወናል። ሞትም ገደልም ቢሆን ሊያስተወን አይችልም እያለ የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር።

ብርቱ ናቸውና ተራሮችሽ፤

አትፈሪም ከጠላቶችሽ።

ድል አድራጊው ንጉሣችን፤

ይኑርልን ለክብራችን።

ሲል ለቆ ቢተወው አእምሮየ ተመሰጠና ከጳውሎስ ጋር ተያይዤ «እንሰደዳለን። ነገር ግን አንጣልም። እንወድቃለን ነገር ግን አንጠፋም።» እያልሁ ሙሾ ሳሟሽ ዳዊት ቀረብ አለና ምን ያስጨንቅሃል። «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» ብዬ የተናገርሁት ትንቢት እንዲያው በከንቱ ነውን በእነዚህ በተዘረጉት እጆቿ የድል ዘውድ ተቀብላ ጠላቷን ከመሬት ስተመታው ለማየት እንደምትችል እርግጠኛ ነኝ።

ከዚህም በቀር ወጸላዕቱሂ ሐመደ ይቀምሑ ያልሁት በከንቱ መሰለህ። በአፌ የተናገረበት እግዚአብሔር ነው እንጂ እኔ አይደለሁም። የእግዚአብሔርን ቃል የሚጠራጠረው ማነው።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና የኢትዮጵያ ጠላቶች አመድ ይቅማሉ። አፈር ይሆናሉ። ይህም እንዲሆን ቃል ለምድር ለሰማይ ብሎ ቃል ገብቶልኝ ሔደ።

ጴጥሮስም፤ የዶሮውን ጩኸት ሰማሁና አላውቀውም በል ስለ አለኝ ቃል፤ አዘነ ተጸጸተ። ከዚህ በኋላ ኤርምያስ መጣና አገጩን ከጉልበቱ ላይ ጣል አድርጎ ቁጭ አለ። ምን ወሬ ይዞልኝ መጥቶ ይሆን እያልሁ

Join us on Telegram @amharicbookss

ዓይን ዓይኑን ስመለከት እዬዬዬ ዋዬ ዋይ ዋዬ እያለ ለቅሶውን ያንባርቀው ዕንባውን ይዘረግፈው ጀመር። እኔም ነገሩ ገባኝና ተነሥቼ ጩኸቴን አቀለጥሁት።

ከዚህም በኋላ የሆነው የሁለታችን ለቅሶ ምን ተነግሮ። ዓይናችን እስኪፈርጥ፤ ስንላቀስ የቀሩት እንደ ጉድ ይመለከቱን ጀመር። ወዲያው ሁሉም ተለይተውኝ ስለ ሔዱ እህና እኔ ቀረን። ከዚህ በኋላ ራበኝና፤ ከአንድ ሆቴል ገብቼ፤ ምግብ ቀርቦልኝ ስጋበዝ አሳቤ እንቅልፍ ሆነና ያንጐላጀኝ ጀመር።

አሥራ ሦስተኛ ክፍል

ጸሎተ ንዋም

በተኛሁበት እንደ ዶሮ ቅንቅልፍ ብንን ሸለብ ሲያደገርገኝ በዚህ ጊዜ ምን አልባት እንቅልፌ ቢለቀኝ አልሁና።

ማርያም ድንግል እመ ረከብኩኪ፤

ኀዘነ ልብየ እነግረኪ፤

በገዳምኑ ወበዓታት ኀበ ኀሠሥኩኪ፤

እግዝእትየ ማርያም እጼውዕ ስመኪ።

ቀዊምየ ኀበ ሀሎኩ አስተርእይኒ ገጸኪ

ወኀበ ስእለትየ ካዕበ ጽልዊ እዝነኪ።

ብዬ አንጐራጐርሁና ከዚህ አያይዤ ደግሞ፤

በእንተ ፍቅረ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ኬንያ፤

እስእለኪ ማርያም በሃሌ ሉያ፤

ኀዘና ስምዒ ወብካያ

ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ።

Join us on Telegram @amharicbookss

እያልሁ በኅዘን ዜና፤ ጸሎተ ንዋም ካደረስሁና፤ ካስታኰትሁ በኋላ ባልጋዬ ላይ ግድም አልሁ። ለካስ ሰምታኝ ኖሮ አንዲት የጠጠር ወሀ የመሰለች ቍንጅናዋ ከሁሉ በላይ የሆነች መልከ መልካም ወይዘሮ አክናፏን ዘርግታ መጐናጸፊያዋን አወራርዳ አጣፍታ ዓይነ ርግቧን ገልጣ፤ ወገቧን በቀሽመሪ ታጥቃ መጥታ በመኝታዬ አጠገብ ቁጭ ብላ የአልማዝ አለንጋ የመሰሰሉትን ሁሉቱን የቀኝ እጅዋን ጣቶች በቀኙ ጕንጯ ላይ ደገፍ አድርጋ ትመለከተኝ ጀመር። እኔም በእንቅልፍ ልቤ ባያት የዓይኗ ጨረር ገረፈኝ። የውበቷም ጽርየት አጥበረበረኝ። ቢቸግረኝ ዓይኔን አሸው ጀመር። እሱዋ ግን አተኩራ እኔኑ እኔኑ በመመልከቷ ሆዴን ባር ባር አለው ስፈራ ስቸር በጐንደርኛው ንግግሬ እረገና። ምን የሆነች ሴት ናት። እንዲህ አድርጋ የምትመለከተኝ። ሰውም አይታ አታውቅምን እያልሁ ሳሰላስል ምን ሰው ነህ። ምን የሆንህ ፍጥረት ነህ። ከዚህ ከሰው አገር ሆቴል ገብተህ (የምታንጐላጅ ብላ ወዲያው ዋ አንተው የኔ ከናካቴው ነህን እኔን ያከናውተኝ። እናት እንደ ሌለውና ሰብሳቢ እንዳጣ ሁሉ የሚያነጋግር አጥተህ ብቻህን ክልትው ብለሃል እያለች በሕልሜ ስትነጋገረኝ አንድ ጥቁር ኪታ (ሸሚዝ) ያጠለቀ ጠርብ የሚያህል እንቶ ፈንቶ ውዲላ መጥቶ በብረት መንዶ በተዋደደ መጥረቢያ አንገቷን ብሎ ለመጣል ሲሰነዝር የለበሰችውን መጐናጸፊያ ጥቅልል አድርጋ አጅሞልሙላ ተቀብላ ማጅራቱን ጠምዝዛ ስትጣጣርና በትር ያሚያቀብላት ስትፈልግ አፈትልኮም በመጥረቢያው እንዳይመታት የሰው ያለህ እያለች ስትጮህ ለጊዜው የሚደርስላት አጥታ ስትጨነቅ ከልጆቿ አንዱ ቁርጠኛው ልጅዋ በጀግንነትና በቆራጥነት ሰይፉን መዝዞ ደርሶ ከመጥረቢያው ስለት ፊት ተደቅኖ በሰይፍ ያወራርደው ጀመር።

በዚህ መካከል ፋሽስታዊ ኢጣሊያ ትመስለኛለች ምጣዷ ተሰብሮ የምትጋግርበት አጥታ የአቦካችውን አቀጣጥና ጠጥታ ተቅማጥ ይዞ ሲነዳት በመጨረሻው እንደ ሲሣራ ጐስቋላ ክፍቸር ብላ ያለ ክብር ሙታ ስትቀበር ያች ከላይ ታነጋግረኝ የነበረችው ወይዘሮ አይታ ራሷን ተሠርታ ሎቲዋን በጆሮዋ አድርጋ ሴሪቴዋን በጐፈሬዋ ዙሪያ አክሊል ሠርታ

ዕልል በይ ጉሜ

ዕልል በይ ጉሜ

ጉሮ ወሸባዬ ጉሮ ወሸባዬ

እንዲያ እንዲያ ሲል ነው ጉዳዬ።

Join us on Telegram @amharicbookss

ከገደሉም አይቀር ይገድሏል ፋሽስት

ጨካኝ አረመኔ የሌለው ምሕረት።

ገዳይ ገዳይ ገዳይ ገዳይ

ሰው ላገሩ አይሞትም ወይ።

ገዳይ ገዳይ፤ ላገሩ የሞተ፤ ገዳይ ገዳይ፤ ላገሩ የሠራ

ገዳይ ገዳይ፤ ዘላለም ይኖራል ገዳይ ገዳይ ስሙ እንደ ተጠራ።

እያለች እየተንጐራደደች የግዳይ ዘፈን ስትዘፍን እኔም ለመፎከር ሲዳዳኝ ብንን ብዬ ተነሥቼ እገረም ጀመር።

ከዚህ ራዕይ የተነሣ ሰውነቴን ላብ ላብ አለው። አለቀስሁ። ዕንባዬ ፈሰሰ መሐረሜ ራሰ። በመላው ሕሊናዬ ጤሰ። ምን ታመጣብኝ ይሆን በማለት ከንፈሬ ተላወሰ። ዋ ተምሬ ወደ ሀገሬ ሳልመለስ እሞት ይሆን እያልሁ ስለራሴ እጨነቅ ጀመር። አገሬንማ ምን አስቤ። ከቶውንም ዋ እያልሁ ከዚህ በታች ያለው እንጉርጉሮ አንጐራጐር ጀመር።

ተማሪ በሞተ ባ፲፰ ዓመቱ

ተምሮ ይመጣል ትላለች እናቱ።

የተባለው ሊደርስብኝ ይሆን ወይስ ጐጃሜይቱ ልጅዋ ወደ ቤገምድር ሔዶ በእሳት ተቃጥሎ ስለ ሞተባት

ይማርልኝ ብዬ ቤገምድር ሰድጄ

ቀለም ገባው አሉ እሳት ሆነ ልጄ።

እንዳለችው ሁሉ ከዚህ ከባዕድ ሀገር እማራለሁ ብዬ መጥቼ ምናልባት አገር ቢሸበር የጦርነት ቃጠሎ ቢነሣ ተቃጥዬ መቅረቴ አይደለምን እያልሁ እትከነከን ጀመር።

Join us on Telegram @amharicbookss

ይልቁንም በአገሬ አንድ መከራ አይምጣ እንጂ እኔስ እንደ ሆንሁ ልሁን እያልሁ ከራሴም ይልቅ ለሀገሬ እጨነቅ ጀመር።

ሀገሬ፤ ዙሮ፤ መግቢያዬ አለኝታዬ ባፈርሽ ተቀብሬ ሰርዶ በበቀለብኝ ምነው። ከፊኔ በአንቺ አፈር ላይ በበቀለው ሰሌን በሆነልኝ በማን ዕድል። ዋ ምን ፈቀረኝ። ስለ ሀገሩ በሀገሩ የሞተ እያልሁ ስትከነከን ያው የኀዘን ተካፋዬ ዳዊት መጣና

በእግዚአብሔር አምኛለሁ

ሰውነቴን ምን ትሏታላችሁ።

እንደ ያፍ በየተራራው እዞራለሁ

አምላኬ አምላኬ እየኝ ለምን ትተውኛለህ

ወደ ሞት ጥላ መካከል ብሔድ አልፈራም

አንተ ከኔ ጋር ነህና።

በትርህና መንዶህ እነሱ ገሠፁኝ

በዘመኔ ሁሉ ምሕረትህ ይከተለኝ።

ክበር ተመስገን አምላኬ

ላንተ እሰግዳለሁ ተንበርክኬ

ፈጥነህ ስማኝ አምላኬ።

ሁለቱም እጄ ለጸሎት

ተዘርግቱአል ወዳንተ።

እያለና ይህን የመሰለውን እየዘመረ እኔም

አገሬን አድን ከወራሪ

Join us on Telegram @amharicbookss

አንተ ነህና መሐሪ።

እያልሁ እየዘመርሁና እጽናና ዘንድ ዳዊት መክሮኝ ዘወር አለ። በዚሁም ስጽናና ኀዘኔም ሳይለቀኝ ደስታውም ሳይርቀኝ እንደ አዳም በዕንቅልፍና በንቃት መካከል ሳለሁ አንድ፤ ስሙን የማላውቀው መደንግፅ የሆነ ሰው በአምባላይ ፈረስ ተቀምጦ መጥቶ፤ የጐኔን አጥንት ነቀለው። መዠረጠው። ቀና ብል ጊዮርጊስ ነው መሰለኝ። ምን አመጣህ ብለው፤ የወገኖችህ አጥንት በዚያ ሲከሰከስ ያንተም በዚህ ይድረስ ብዬ ነዋ።

ኀዘንን የሚያውቀው ኀዘንን የቀመሰ ስለሆነ፤ መከራን ከቀመሱ አንዱ እኔ ላዋይህ መጥቻለሁ። ዛሬ በወገንህ የደረሰውን መከራ፤ እኔ ሰባት ዓመት እንደ ተቀበልሁት መከራ አይተህ ማየት ነው። የወገንህ ገድል ከገድሌ ጋር አንድ ሆኖ ሲነበብ ይኖራል። እንዴት ሰው ሆኖ በሰው ላይ ይህን ያህል ግፍ ይውላል።

ቢሆንም ተስፋ አትቁረጥ። እኔ ከብዙ መከራየ በኋላ ያገኘሁትን ብዙ ክብር መመርመር አስተማሪ ይሁንህ። አገርህ ሙታም አትሞትም።

ወድቃም አትቀር እያለ ሲያጽናናኝ፤ የጊዮርጊስ አፍ አፍ ስመለከት አቤል ቃለ ደሙን በሙዚቃ ቀርጾ የሙዚቃን ንፍ በተስረቀረቀ በኀዘን ቅኝት እየገረፈ መጥቶ፤ በፊቴ፤ ቀጥ ብሎ ቁሞ ረቂቅ የሆነ የኀዘን ምት በመዝሙር ባሰማኝ ጊዜ ዕንባዬ ካይኔ ይዝረከረክ ጀመር። ልቤ ተመሰጠና ሳይታወቀኝ ሔጄ ከሙዚቃው አፍ ላይ ተለግቼ ሳለቅስ በግድ አላቀቀኝና፤ አይዞህ ይህን ጥልቅ የሆነ የኀዘን ምት በሰማህበት ጆሮህ በጣም ደስ የሚያሰኝ መዝሙረ ፍሥሓ ትሰማበታለህ አለና ቃየል ሳይመጣብኝ ቶሎ ልሒድ ብሎ ሔደ።

እኔም ወየው ጉድ። ወደዚህ አገር የመጣሁት እማራለሁ ብየ ነበር እንጂ፤ እንደዚህ ያለ ነገር መች አምሮኝ መጣሁ፥ እያልሁ ስተከካዝ፤ የዘካርያስ ልጅ ዮሐንስ ከትከሻው በላይ ባዶ ሁኖ ራሱን በፃሕል አድርጎ መጥቶ በፊቴ ይለገታል። እኔም እሱን በማየት ቅጡ ጠፋኝ። እሱም የመጣበትን እንዳይነግረኝ፤ አፍ የለውም። ለካስ አፉ ያለው ከራሱ ጋር ኑሯል። ራሱ በፃህሉ ላይ እንዳለ ይኸውልህ፤ በሀገርህ፤ የወንድሞችህ ራስ እንደዚህ እንደኔ ከአካሉ በግፍ እየተቆረጠ ወድቋል እያለ ሲነግረኝ እኔም ከድንጋፄዬ የተነሣ የወንድሞችህ ራስ ሲል ስለ ሰማሁት ቃል ይወንድምነህ? ያለ መሰለኝና ራሴን ይዤ እጮህ ጀመር።

ወዲያው እሱው ነገሩን ቀጠል አድርጎ፤

Join us on Telegram @amharicbookss

አንገትም ቢቆረጥ ዓይንም ቢፈርጥ

ትንሣኤ አለና ተስፋ አትቁረጥ።

ብሎኝ ከፊቴ ተሰወረ። ይህን ሳሰላስል ያዕቆብ የልጁን የዮሴፍን የደም ሸማ እንደ ፎጣ ባንገቱ ላይ አስሮ ሲመጣ አይቼ ይህም የሚመጣው የኔው ጉድ ነው እያልኩ ስጨነቅ ከ፲፬ሺህ በላይ የሚሆኑ የገሊላ ሕፃናት ትኩስ ደማቸውን እያንጠባጠቡና በደም ጫማ እየዳሁ መጥተው ከበቡኝ። ራሄልም መጥታ ትጮህ ታገር፤ ጀመር። ከዚህ በኋላ እኔም ድምፄ እስኪዘጋ ዓይኔ እስኪፈርጥ፤ ስናለቅስና ስንጯጯህ አንድ ነጭ ርግብ የመሰለ ከወደፊቱ የመልአክ ቅርጽ ያለው ባለ ክንፍ መላክተኛ መጥቶ ጩኸታችሁ በዕዝነ ፈጣሪ ደርሷል አንድ ቃል ብቻ አሰምቶ እልም አለ። ከኀዘኔ ብንን ብል ሁሉም ጥለውኝ ሒደዋል። ወደ አእምሮዬ ተመልሼ ብመለከት ያው እህህ የተባለው አነጋጋሪዬ በጐኔ ተሸጧል።

ወደሱ ዞወር ብዬ እህህን እስኪ በል አነጋግረኝ እያልሁ እሱን ሥራዬ ብዬ ያዝሁ። በሀገሬ ብሆን ከቶውንም ከመከራው መካከል ብገኝ ከዚህ የበለጠ ምን ይመጣብኝ ኑሯል። በኀዘን ጦር መወጋትና በጥይት መመታት ምን ልዩነት አለው ደሜ ባይፈስ ይኸው እንባዬ ይንዠቀዠቃል። ደምና ዕንባ ያለ አንዳች ምክንያት እንዲያው በከንቱ አይፈስም። ሰውነቴ በእሳት ኀዘን ተቃጠለ። በኀዘን ንፍር ውሀ ተቀቀለ፤ አንጀቴ ተበጣጠሰ። ልቤ ነበዘ። አእምሮዬ ናወዘ ዓይኔ ቦዘ።

የቆላ ወፍ ባሏ ሞቶባት በኀዘን ተጨብጣ ክንፎቿን ማራገብ አቅቷት፤ በጽኑ ድካም ላይ ሳለች ሌሎቹ ኀዘን ያልነካቸው ተነሺና ወዲያ ወዲህ ብረሪ ቢሏት።

ኀዘን ክንፌን ሰበረው

በምን ክንፌ ልብረረው።

አለች ይባላል። ይህም የወደፊቱ የኀዘን ቅኔ ልዩ የኀዘን ዜማ ስላለው፤ የዜማ መምህራን የድጓ ምልክት አድርገውታል። ስለዚህ እኔም ሰውነቴ በኀዘን ስለተቃጠለ መንቀሳቀስ እስኪያቅተኝ ድረስ፤ ሬሳም የምሆንበት ጊዜ ነበር። እንደዚህ ያለ ከሕይወት በማይቆጠር ኑሮ ላይ ሳለሁ፤ ኢዮብ በመከራ ተቆራምዶ፤ ፊቱን አጨማዶ፤ ውንክር ውንክር እያለ ሲመጣ፤ ገና በሩቅ አይቼ፤ ደግሞ አንተ ከየት ነው የመጣኸው። ደግሞስ ይህን ያህል አጥንትህ የወጣው ምን ሁነሀል። ብለው እኔስ ሁኜ ወጥቶልኛል፤ ገና ኋኙ አንተ ነህ።

ዳሩ ግን አንተ ምን ሁነሃል። ሸረር ብለሃል። ውዲቱ ለምለሚ አገርህ ግን ከመከራ ወድቃለች ብሎ የኔኑ መከራ ከኔ የራቀ አስመስሎ አጋድሞ ቢነግረኝ፤ ከፋኝ። እንደ ገላው ገላዬ ፈረሰ አካሌ ተቆራረሰ። ወዲያው ሰማህ ኢዮብ፤ አንተ እንኳ ያንድ ያንተ አካል ብቻ ቢፈርስ ታላቅ ኅዘን ደረሰብህ። የሀያ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ገላ ሲቆስልና ንብረቱን ሲፈርስ፤ ለምን እንዲህ ያለ ነገር ካፍህ ይወጣል። እኔ ምንም አይደለሁ። ሕይወቴም ጤናዬም ዓለሜም ክብሬም ባጭሩ ነፍሴ፤ ነፍሴ፤ ነፍሴ አገሬ ስለሆነች፤ ያለርሷ ነፍሴ የሌለው በድን ነኝ መሪር ቃል ተናገርሁት።

እሱ ግን አስትዋይ ኑሮ ትንቢታዊ ቃል እየጠቀሰ

እስከዚያው ድረስ አንተ ንህና ሁን

እንደ ነበረ ይሆናል አሁን።

ተብሎ እንደ ተነገረው፤ ሁሉም ነገር እንደ ቀድሞ መሆኑ አይቀርም።

እናትህ ኢትዮጵያ፤ እስከዚያው ድረስ ትፈተናለች እንጂ መሞት የለባትም። ይህ እስኪሆን መጥኔውን ይስጥህ።

እናትህ ከዚያው ከቁርጠኛ ልጅዋ በቀር ለጊዜው ከትከሻዋ ጠጋ ብሎ መስቀሏን ያሸካክማትና ያገዛት አንድም እንኳን ስምያን አልተገኘም። ጥንቱንም ሲፈጠር ሰው የጠላው ፋሽስት እያነጠነጠና እያዘጠዘጠ፤ ሀገሪቱን በብረትና በመርዝ ኃይል እያወደመ ወረራ ጀመረ።

በሁለት ወገን ስለት ካለው ከስለታም ሰይፍ ይልቅ የተሳለ በሆነ ፖለቲካ እያታለለና እየወሸከተ ልቅሰና የጥርስ ማፋጨት ወዳለበት ወስዶ ለማሠቃየት የሚያደርገው ስብከት «ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው ይበልጣል» እንደ ተባለው ለማድረግ ተስፋፍቷል።

እንግዴህ ስንቱ ይነገር። ስንቱ ይወራ?። እያለ ወሬ ከወሬ ሲንጐደጐድ፤ አእምሮዬ ተሠወረ። ልቡናየ ታወረ። በሀገሬ ሳለሁ የዚህኑ የግፈኛ ታሪክ እያነሣን ካንድ ባልንጀራየ ጋር እንደ ናትናኤል፤ ከበለስ ሥር ቁጭ ብለን የተጨዋወትነው ታወሰኝና፤ እሱን እሱን ሳሰላስል መንፈስ ገና ውጭ አገር ሳይጠራህ ከበለስ በታስ ተቀምጠህ አይቼህ ነበር የምትል ወሬ ነገሪት (ኢትዮጵያን (ትመስለኛለች) መጣችና ከፊቴ ድቅን አለች ዋ የኔ እናት ነሽን ብዬ ከናፍቆቴ የተነሣ ከእግሯ በታች ወድቄ እግሮቿን ስላለም፤ ከበለስ በታች አየሁህ ስላልሁህ

Join us on Telegram @amharicbookss

አመንህን ገና ከዚህ የበለጠ ደስታ ታያለህ ብላ ትንቢት ስትጀምርልኝ ወሬ የተጫነ የነፋስ ፈረሰኛ መጣና ጭነቱን ያራግፈው ጀመር።

ከሞት የተረፈና ከአሳዳጅ ያመለጠ ተስፋየ አንተን ስጠኝ የሚባለው ባልንጀራየ ከዘመዶቼ ደብዳቤ ይዞ በየብስና በባሕር የደረሰበትን ልዩ መንገድ አቋርጦ ፈተናውን ድል ነሥቶ፤ ካለሁበት ከተፍ አለ ደረሰ። ከሰማይ የወረደ መሰለኝ። ደነገጥሁ ደንገጠ። መሰሳማችን ቀርቶ አንገት ላንገት ተያይዘን ተላቀስን። ካንድ ሰዓት በኋላ ሳምሁት ሳመኝ። ጠየቅሁት ጠየቀኝ።

ደብዳቤውን ከኪሱ አውጥቶ ያውልህ አለኝና ገልጬ ባየው በውስጡ ያለበት የመርዶ ቃል አንጀት ይበላል። ልቦና ይከፋፍላል። እንደ ፍላጻ ውስጥ አንጀት ይወጋል። ለማንበብም ስሞክረው የስሜቱ ሹል ጦር ትክል ብሎ ሰውነቴን ሸነቆረው። እምሽክ አድርጎ እንደ ሰይፍ አረደኝ። ሸነተፈኝ።

ኢትዮጵያ እንደ ኢዮብ በትር ተመታች ለማለት ገና ኢዮ ብሎ ብን ሳይጨርሰው ሰውነቴ በድንጋጤ ፈርሶ ያንቀጠቅጠኝ፤ ያንጠረጥረኝ ጀመር። ከእንቅጥቃጤየም የተነሣ ጥርስና ጥርሴ እየተፋጩና እየተከሳከሰ በሽታ ሆነብኝ። ምንአልባት ይህ ነገር ወባ ሳይሆን አይቀርም በማለት እንደ አገራ ልማድ፤ ማን ደጋን በጫነብኝ እያልሁ እመኝ ጀመር። ወሀም ቢሰጡኝ ብርጭቆው በእጄ ላይ እየዘፈነ ወሀው በላየ ፈሰሰ።

እህልም ቆርሼ ወጥ አጥቅሼ እጐርሳለሁ ስል እጄ አፌን ትቶ ጉንጨን እየለቀለቀው ተቸገርሁ። ንግግርም ስሞክር አፌ ይተሣሠር ጀመር።

ደብዳቤው ግን ማን ፈርቶ። ለማን አዝኖ ለማን አስቦ። መርዶውን ቀጠለ። ኢትዮጵያ እንደ ሠለስቱ ደቂቅ በእሳት ጉድጓድ ተጣለች። ባጭሩም እንደ ፈጣሪ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተወገረች። ተሰቀለች። ታሠረች። ተቸነከረች። ተጸፋች። ተገረፈች። መስቀሏን አሸከመው ጐተቷት። አሁንም ያለችው በቀራንዮ ሜዳ ነው።

ፋሽስቶች ብቻቱ ለ፳ ዓመት ማገዶ የሚበቃ ጨፈቃ የሚያህል የጦር መሣሪያ ይዘው መጥተው መከራ አመጡባት።

ሕዝባችን ታረደ። ከተማችን ነደደ። ከሞት የተረፈው ወገናችን ተሰደደ። ኢጣሊያ እንደ አረሆይቱ እንደ ሄሮድያዳ ልጅ ሆና በሄሮድሶቿ ፊት ዘፍና እንደ ዮሐንስ የኢትዮጵያውያንን አንገት በሰይፍ

Join us on Telegram @amharicbookss

አስቀረጠች። እልዛቤልን ሆና እንደናቡቴ ባለርስቱን በገዛ ርስቱ በግፍ አስገደገለች «የአሕዛብ ዘመን እስኪጠፋ ድረስ ኢየሩሳሌም ትረገጣለች» የተባለው በኢትዮጵያዊት ኢየሩሳሌም ደረሰ።

ከሥቃዩ ነጻድነት የተነሣ ጣቱን ወይም መሐረሙን በወሀ ነክሮ ምላሱን እንዲያበርድለት ተስፋ ያደረገው የነበረው የእግዚአብሔር ጠለ ምሕረት ገና እንደራቀ ነው። በሰላም ደጁን ዘግቶ ተኝቷል። ርኅራኄ ዓይኑን ጨፍኖ ፊቱን ሸፍኖ ተቀምጧል።

ሰማዩ በአኤሮፕላን አክናፍ፤ ምድሩ በታንክና በመድፍ ተሸፈነ። በምድሩም፤ በአየሩም በባሕሩም የሚሸተው የመርዝ ክርፋትና የባሩድ ቅርናት ነው። የተቀደሰውን ነገር እያረከሱ፤ በእሳት እየለኮሱ የረከሰውንና የተነወረውን ተግባር ይሠሩበት ጀመር።

ጥቁር ተነቅሎ፤ ዘሩ ጠፍቶ፤ ፋሽስት ብቻ እንዲበቅልና ዘሩ እንዲለማ የግፍ መሠረት ተጣለ የሚልና ይህን የመሰለውን የመርዶ ቃል ከተመለከትሁ በኋላ ዝቅ ብሎ ቢሆንም ተስፋ አንቆርጥም።

ይህም የኢትዮጵያ ብቻ የግሏ አይምስልህ። የመላው ዓለም ድርሻ ነውና፤ ሁሉም እንደ ጠበል ሳይራጨው አይቀርም። አሁን ሁሉም የመቃብር ቤቱን ይምሳል። ሁሉም የመቃብር አፈሩን በራሱ ላይ ነስንሶ ተቀምጧል።

ከጥቂት ዓመት በኋላ የተነሡት ግፈኞች ሁሉ ይወድቃሉ። ከወደቁበትም አይነሡም። አይንቀሳቀሱም። አፋቸው ኩበት፤ መላሳቸው እንጨት ይሆናል። ክንዳቸው ይዝላል። ጉልበታቸው ይደክማል፤ ኢትዮጵያን የበደሏት በደል፤ በእግዚአብሔር ፊት ይታሰባቸዋል።

ወገኖችህ ሊማርኳቸውና ሊዘርፏቸው ሊያጠፏቸውና ሊደመስሷቸው የመጡባቸውን ይማርኳቸዋል። ይህም ነገር የጊዜው ጊዜ የሚፈጸም መሆኑን እመን። አትጠራጠር።

የወገንህ የደሙ ድምፅ ወደ እግዚአብሔር ይጮሃል። ዘር እንዲተርፍና የጠላት ኃይል እንዲቀነስ አርበኞች በበረሃ ሁነው ይከላከላሉ። ስደተኞችም በውጭ አገር ሁነው ይታገላሉ። በጠላትም ጥፍር የተያዙት ሁሉ በጸሎተ ሕሊና ይዋጋሉ። አንድም ጋሻውን የሰቀለ የለም። ሁሉም አንግቦታል። በዚህም በዚያም ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋ አልቆረጠም። ይታገላል። ይጋደላል። ዕንባዎችም በእግዚአብሔር ፊት ይንፋዋፋዋሉ።

Join us on Telegram @amharicbookss

በፋሽስት የፈርያን ስጥመት እንዲታዘዝበትና የስናክሬም ጥፋት እንዲደርስበት ያለጥርጥር ያመናል። ያለውልውል ተስፋ ያደርጋል።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ካሉበት ብዙ ተላላኪዎዎ እንደ ርግበ ኖኅ የጥፋት ውሀ የሚጐድልበትን ምክንያት የሚያስረዳ ምልክት ያመጡልናል፡ እንደ ቅዱስ ገብርኤል የደስታ ድምፅ ያሰሙናል።

አንተም ባለህበት እኛም ባለንበት፤ እንበርታ፤ ልባችን አይላላ ፈተና የሚበዛበት አገርና ሕዝብ የታሪክ አገርና የታሪክ ሕዝብ ነው።

ወርቅነታችን ሊታወቅ ነው። እኛን ለመፈተን መከራ ያመጣብን ፋሽስት ውዳቂና ስብርባሪ ሸህላ ሆኖ የሚቀረው። ተፈታኙ እንደ ወርቅ ጠርቶ ሲወጣ ፈታኙ አተላ ሆኖ ከድብደባ ይጣላል።

አገራችን ነፃ ትወጣለች። እኛም የተጫነብንን ቀንበር እንሰብራለን። ኢትዮጵያ በጦር ተቀዳሚ እንደሆነች በመሪዋ ዕድልና ታላቅ ትግል የድል ተቀዳሚ ለመሆን ዕድሏ ሳያግዛት ይቀራል ተብሎ አይታሰብም።

ከዕድልም በኋላ ሌላ ዕድል አላት። ከጦርነቱ በኋላ የሚቀጥለው ታሪክ አዲስ ነው። ያዲሱም ታሪክ ዘመን ሕዝብ አዲስ ሆኖ ኢትዮጵያ ከመቸውም ይልቅ ትስፋፋለች። ትሰለጥናለች። ከፍ ከፍ ትላለች።

ከቶውንም የዱሮው የባሕር በሯ ሳይቀር የመለሳል ወሰንዋም የጥንቱን መሥመር ለመያዝ የሚችልበት ጊዜ ይደርሳል። ይህን ተስፋ ጠብቀው። አትልቀቀው። በልብህ ቋጥረው። ባንገትህ እሠረው ጊዜ አለው። ለሁሉም ጊዜ አለው ከተባለው አንዱ ይህ ነው።

አንዱ ጦርነት ያን ጊዜ ስለ ሆነ መበርታት ያን ጊዜ ነው። አሁን እንዲህ ሆነ ብለህ ትምህርትህን ከመቀጠል አትቦዝን። ባዶህን እንዳትመጣ ተጠንቀቅ። ከጥበባት ሁሉ አንዱን ጥበብ ነጥቃችሁ ወደ አገራችሁ የተመለሳችሁ እንደ ሆነ፤ ለሀገራችሁ የሚበጅ ሥራ ለመሥራት ትችላላችሁ።

ከዚህ ቀደም የተማሩት ወጣቶቻችን በፋሽስት አልቀዋል። በነሱ ምትክ መተካት ያስፈልጋል። እንዲያውም በብዙ ሚልዮን የሚቆጠሩ ሊቆች ለኢትዮጵያ እንደሚያስፈልጓት እያሳሰበ መጪው ዘመን አደራውን ይጥልብናል።

Join us on Telegram @amharicbookss

እኛም ቢሆን ግብዝ አይደለንም። አማርኛና ግዕዝ በተናገርንበት አፋችን የፈረንጅ ቋንቋ አንናገርበት የምንል አይምሰልህ። እኛ የምለው ንግግሩን እንደ ፈረንጅ ተናገራችሁ ሥራውንም እንደ ፈረንጅ መሥራት አለባችሁ ነው።

ዓለም ከትግል ዐርፎ፤ ትግልም ከዓለም ተለይቶ አያውቅም። ሰው የተፈጠረው ለልፋት ዓለም የተከናወነው ለአልፊነት ስለሆነ፤ እምታገልህንና ታግለህ የምትጥልበትን ዘዴ በርትተህ ይዘህ የመጣህ እንደሆነ ተጠቅመህ ታስጠቅማለህ። ተመስግነህ ታስመሰግናለህ ከብረህ ታስከብራለህ።

አገራችን ለምለም፤ ፍሬያማ፤ በቀላል ድካም ብዙ ጥቅም ለመስጠት የምትችል፤ ገነታዊ አቀማመጥ ያላት ሥፍራ ነች። ውበትም እንደ ዕድል ነው። ሌላው ሁሉ በብድርም በትምህርትም ሲገኝ፤ ውበት ብቻ አይገኝም።

አንዲት ልጅ አገረድ፤ ጓደኞችዋ በጨዋታ አነሣሥተው መልከ መልካም ብትሆኚ ትወጃለሽ ወይስ ባለሞያ ቢሏት «መልኬ ይመር እንጂ ሙያውንስ ከጐረቤት እበደረዋለሁ» አለች ይባላል።

እውነት ነው። አገራችን ለምለም መሆንዋን ትያዝ እንጂ ሥልጣኔውንስ ወጣቶቿ ከውጭ አገር ሒደው ተምረው መጥተው፤ ያጐርፉታል። ስለዚህ የነብርን ጅራት አይዙም ከያዙም አይለቁም ነው። የአሁኑ ወጣት ሥልጣኔን አጥብቆ መጨበጥ አለበት።

ከዚህ ቀደም እኛ ዘመዶችህ ወደ ኤውሮፓ መሔድ ይቅርብህ ብለን አከላክለንህ ነበር። ነገር ግን አንተው ራስህ እብድኅንፃ መንፈስ ተቃኝተህ በጥንካሬህ ካሰብኸው ደረስህ። እንግዴህ ምን ይዞ መጣ መባል እንዳለብህ ዕወቀው። እኛ ዘመዶችህ ሳንማር አንተን ተማር ብለን ማፅናናታችን አይግረምህ። በፊተኛው ጊዜ አለመማራችን ለአሁኑ ጊዜ አስተማሪ ሆኖናል። ጸጸትን ጥሎብናል።

ኤውሮፖች ብትላቸው እንዲሁ ተምረው ተቀዳድተው ተበድረው ተዋውሰው ነው እንጂ ሥልጣኔ እንዲያው ከሰማይ እንደ ኳስ ዱብ ብሎ ወይም ከገደል ተቀርፎ አልወረደላቸውም። ተማርም ስንልህ ቋንቋ ብቻ አይደለም። የማዕድናትን አወጣጥና የፋብሪካን አሠራር የቴክኒክን አገልግሎትና ልዩ ልዩ የሆኑትን የብረታ ብረት ብልሃቶችም ነው። ይህ የተባለው ካልተጨመረበት የቋንቋ ብዛት የሚሰጠው አገልግሎት ጥቂት ነው።

Join us on Telegram @amharicbookss

ስለዚህ ትምህርት ተላይ ተላዩ ኩረፌውን ማንሣትና ካናት ካናቱ ገፈታውን መጨለፍ ብቻ ሳይሆን ከሥር ገብተህ ጥለቀው። ደንብቀው። አንቅረው። አሟጠው። ምጠጠው። ጨልጠው።

ወደ ሩቅ አገር ሔደህ አንድ የተጨበጠ ዕውቀት ይዘህ ካልመጣህ ዘምቶ ተወረስ መሆንህን መዘንጋት የለብህም። ያለዚያ ግን አንደኛው ወደ ሩቅ አገር ሳትሔድ ቀርተህ እዚሁ የዘመቻ ፈሪ እምክፈል በተሻለህ ነበር።

ዛሬ እንጫወት ነገ ትማራለህ እያለ የሚያታልልህን ሴታ ሴት ውበት ከምንም አትቍጠረው።

አሁንም ደግመን ደጋግመን ትይዘው ዘንድ የምናስጠነቅቅህ ትምህርት ቢሉህ ከኰሌጅና ከዩኒቤርስቲ የተቀዳና የተደነበቀ ነው እንጂ፤ ከየሚሲዮኑ የተለቃቀመና በጆሮ ጠገብነት የተጠራቀመ አይደለም።

እንግዲህ እግዚአብሔር ቍጣውን በትዕግሥቱ መዓቱን በምሕረቱ መልሶ ኢትዮጵያን እንደ ገና አድሶ ንጉሠ ነገሥታችንን በደኅና አምጥቶ በዓይነ ሥጋ ለመታየት ያብቃን።

ፊርማ ዘመዶችህ

አደገኛና ነውጠኛ

ያዳንቁሽና ጣዲቄ

አሥራ አራተኛ ክፍል
በትግሉ መጨረሻ የተገኘው ድል።

እንደ ኢትዮጵያ አቈጣጠር በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም በኢትዮጵያ የተነሣው ቃጠሎ፤ ወደ ተጫረበት ምድጃ ተመልሶ የእግዚአብሔር ፍርድ ያስገደደውን ለመፈጸም እንደ ኤውሮፓ አቆጣጠር በ፲፱፻፴፱ ዓ.ም ደረቅና እርጥብ ብው ብሎ ነደደ።

ለዚህም መጀመሪያው እሳት ቈስቋሽ በፊት ጃፓን፤ ቀጥሎ ፋሽስት፤ በኋላም ናዚስት፤ አንድ ላይም ተደምሮ አክሲስ ሲሆን፤ ለእሳቱ ማቀጣጠያ ከኢትዮጵያ በኋላ፤ እነፖሎኝና፤ እስከ ግንዶቹ እስከ ፈረንሣይና

Join us on Telegram @amharicbookss

እንደ ፈረንሣይ እስከ መሰሉት ድረስ፤ ተራ በተራ የእሳት እራት ለመሆን ዕድላቸው በመከራ ወድቆባቸው የነበሩት የባልክንና የኤውሮፓ ምዕራብ አገሮች ነበሩ።

ያ ከላይ የተጠቀሰው አክሲሳዊ እሳት የማንንም ጐፈሬ አልመረጠም። የሁሉንም ቸብቸቦ ላስ አደረገው። የዚህም ታሪክ በዝምታ ካልታለፈ በቀር፤ ዝርዝሩ ይበዛል። ዓለም ትችለው ዘንድ አቅቷት የነበረው የመከራ ማዕበል የወረቀት ገጽ ይወስነዋል ማለት ዘበት ይሆናል።

በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ የጦር ጓደኛ አዘዘላት። የዓለም መንግሥታት መሪዎች በጄኔቭ ሸንጎ ተቀምጠው የሰቀሉትን ጦርና ጋሻ ቁመው ለማውረድ ግድ ሆነባቸው።

ፍርድ ሳይመለከቱ፤ ከመንጋዎች መካከል ቁጥር አጉድለው አበሳ የሌለባትን አንዲቱን ጠቦት የጣሉለት አውሬ እንደ ገና እነሱኑ ሊውጣቸው አፉን ስለ ከፈተ ነፍሳቸውን ለማዳን የመድፋቸው አፍ ተከፈተ።

እነሱ በሌላው ሳይሆን በገዛ ራሳቸው እንደዚህ ያለ ኃይለኛ የሆነ አደጋ በደረሰ ጊዜ፤ ካደረጉት አመካከት ጋር የእኛም ጋሻ አብሮ ስለ ተመለከተ፤ ከጋራ ጉልበት የጋራ ድል አድራጊነት ይገኝ ዘንድ የተረጋገጠ ተስፋ ተጣለ።

በዚህ መሠረት ኅያሉና ገምናናው የይሁዳ አንበሳ ጠጉሩን አስቆጣ፤ ጋማዎቹ ግርማቸውን ለበሱ። መዳፎቹ ጠላትን ለማዳሸቅ ከጠንካራዎች የበለጠ ጥንካሬ ተሰጣቸው። ጭራውን ወደ ኢትዮጵያ አቅጣጫ ቢያወራጨው ዱሮቹን ሁሉ ቀሰቀሳቸው። ደኖች ሁሉ አንበሳ አንበሳ ሸተታቸው።

ሕዝቅኤል አንበሳዊት» ሲል በትንቢቱ ውስጥ ያነሣሣት ሀገር ኢትዮጵያ ሁና ተገኘች።

በዚህ ጊዜ የስደተኞች ነፍስ «ተመየጢ ሀገረኪ እስመ ሞቱ እለ የኃሥሡ ይቅትልዎ ለወልድኪ» የሚል ቃል በዕዝነ ሕሊና ስለሰማ አሳቤ ተነሣ። ፈረሱን ጫነ።

ወሬው መቀጠሉን ሳያቋርጥ ያ በያዕቆብ ቃል አንበሳ ዕጓለ አንበሳ» ተብሎ ከተሰየመ በኋላ እዴከ ዲበ ዘባኖሙ ለፀርከ» ተብሎ የተመረቀና አሸናፊነቱ የተመሰከረለት የይሁዳ አንበሳ ፲፱፻፴፪ ዓ.ም በሰኔ ወር ወደ ካርቱም ሒዶ ጣሕሩን ባሰማ ጊዜ ኢትዮጵያ ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት፤ ስትል አዋጅ ነገረች።

Join us on Telegram @amharicbookss

ጀግናዪቱ ኢትዮጵያ በዚህ ጊዜ ከአራት ዓመት በሚበልጥ ዘመን መካከሉ ሳያቋርጥ የቆየው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደገና በጠላት ላይ አራስ ነብር ሆነበት።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መትረየሳቸውን ደግነው፤ ተኳሽና አስተኳሽ፤ ተዋጊና አዋጊ ሁነው፤ ከጦሩ ግንባር ተገኝተው የጦር ሥራ ይሠሩ ጀመር የሚል የጦር ማስታወቂያ በሰማሁ ጊዜ ቸር ወሬ ያሰማህ» እምአይቴ ረከብከ ዘከመዝ ብሥረተ ብየ» ማስታወቂያ የተነገረበትን የራዲዮ ጣቢያ እስመው ዘንድ ወደድሁ። ከቶውንም ተሳለምሁት። እንደዚህ ያለ ወሬ ጆሮ ሰምቶ አያውቅም። ከወዴት ተገኘ። ቅዱስ ሚካኤል ነው የነገረኝ፦ ወይስ ቅዱስ ገብርኤል አወራልኝ። መልካም ባለምሥራች እንደዚህ ነው። እስከ አሁን ድረስ የሚመጡት ወሬ ነጋሪዎች የሚያወሩልኝ ሁሉ መዓት ነበር። አሁን ግን ይህን የምሕረት ቃል በመስማቴ ደስ አለኝ። በኅዘን ተኵራቶ የሚኖር ሰው መጨረሻው ደስታ ሲሆንለት። ከዚህ የበለጠ ዕድል ሌላ ምንም የለውም።

ትናንትና ማታ በልቅሶ ይጨበሰብስ የነበረው ዓይኔ ዛሬ ጧት የደስታ ኵል ኵል ተኵሎ፤ ይቁለጨለጭ ጀመር። ልቤ በደስታ ስለ ተዋጠ። ፊቴ በደስታ ተቅለጠለጠ።

እንደ እርሳስ ተጭኖኝ እንደ ብረት ቀንበር ጨቁኖኝ የነበረው ጭንቀቴ ሁሉ ከላዬ ሲወድቅ ተሰማኝ። በዚያ ፋንታ የእግዚአብሔር ጸጋ ሲያድርብኝ ታወቀኝ። በሽታዬ ሁሉ ለቀቀኝ። ሳቅ ተከልክሎ የነበረው ጥርሴ ፍልቅቅ ፍልቅቅ ይል ጀመር። ያረረው ከንፈሬ ወዛ። ሞጌው የወጣው ወዘናዬ ተመለሰ። የተቃጠለው አንጀቴ ራሰ። የደረቀው ደሜ ተላወሰ። ከሞት አፋፍ የደረሰው ሕይወቴ ተመለሰ። የደረቁት አጥንቶቼ ለመለሙ። ያለቀው ሥጋዬ ባጥንቶቼ ሞላ። የተነቃቀሉት ጠጉሮቼ እንደ ገና በቀሉ። ዕንባው ከማለቁ የተነሣ እንደ ዋሻ ጐድጐዶ የነበረው ዓይኔ፤ ቡጢ አካከለ። ተሸራምጦ የነበረው አፍንጫዬ የስንድድነቱን አቀማመጥ ያዘ። ፋጫ የመሰለው መልኬ መልአከ እግዚአብሔር መሰለ። ዕንባ የገመሰውና በይ ያበጀው ፊቴና ጉንጫጉንጬ ድንቡሎነቱን አገኘ። ከእንግዲህ ወዲህ እንኳንስ ሞትና ሌላም ከሞት የባሰ የለም እንጂ ቢኖር ሕይወቴን ለሀገሬ እንዳልቆጥብ ሙሉ ቆራጥነት አደረብኝ።

ይህን ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ደስታ እንደ ሰማሁ ሻምፓኝ ገዛሁና፤ የደስታዬ ተካፋይ ለመሆን የተሰበሰቡት እንግዶች ሻምፓኝ የያዘውን ብርጭቆ ከጨበጠው በኋላ፤ ሁሉም «መልካም ጤና እያሉ ብርጭቆ ለብርጭቆ ያጋጩ ጀመር።

Join us on Telegram @amharicbookss

እኔ ግን ዓለም ጠቡንና ግጭቱን እንደ ዋዛ የሚጀምረው በደስታ ጊዜ መሆኑን ተገንዝቤ ይህ የብርጭቆ ግጭት፤ የመድፎችን ትግል አስከታይ እንደ ሆነ ማንም አላወቀው ይሆን። እያልሁ በአሳቤ እገረም ጀመር። ከቶውንም የጨበጥነው የሻምፓኝ ብርጭቆ የአዳም ልጅ በጦር አውድማ በሚያደርገው ግጭት የሚራጨው የደም ጽዋ መስሎ ታየኝ።

በዚህም ጊዜ የሻምፓኝ ጽዋ ከተጨበጥነው አንዱ ስለ ዓለም ሰላም ጽዋየን አነሣለሁ ሲል ላደረገው ንግግር መልስ፤

እኔ ቃሌን ከፍ አድርጌ «እርግጥ ነው። ዛሬ ሁሉም ጽዋው ስለ ደረሰው፤ በተራው ተነሥቶ እስኪወድቅ ድረስ መራራም ሆነ፤ ጣፋጭ በጽዋው የተቀዳለትን መጨበጥ አለበት። የዛሬ አራት ዓመት ከዓለማት ጋራ ማኅበረተኛ የነበረችው ኢትዮጵያ መጥፎ ዕድል ገጥሟት የመጀመሪያው ጽዋ ለሱዋ ስለ ደረሰ፤ ወደ ድግስዋ መጥቶ ከጽዋዋ የተሳተፈ ባለመኖሩ ሁሉም ባለሳምንት መሆኑን ዘንግቶት ነበር። ዛሬ ግን ራሱ የጽዋው እግር በሁሉም ደጅ እየሔደ መጡብሹን ስላረጋገጠ፤ ሁሉም ስለ ጤናው ሲል ጽዋውን መቀበል ግድ ሆኖበታል፤» ብዬ ይህን የመሳሰለውን በተነጋገርሁ ጊዜ፤ ሁሉም እውነት ነው። እውነት ነው በማለት ድምፃቸውን አሰሙ።

ከዚህ በኋላ ሁሉም ወደየ ስፍራቸው ሲመለሱ እኔና ደስታዬ ብቻችንን ቀረን።

ከዚህም በኋላ ካለሁበት አገር ወደ እንግሊዝ አገር መጥቼ የእንግሊዝን ባለሥልጣኖች ጠይቄ ጠበንጃ ተቀብዬ የጦር ልብስ ለብሼ ተሰልፌ ደሜን አፈስ ዘንድ ወደ ኢትዮጵያ ከተዘረጉት ከጦር መሥመሮች በአንደኛው የጦር ግንባር ገብቼ እወጋ ጀመር።

በዚህም «ማርያም ግን የማይቀሟትን ያማረ ዕድል መረጠች የተባለው ቃል ለእኔ እንደሆነ ተሰማኝ። ወገን ተገኘ። የሀገር ጭምጭምታ፤ የነፃነትም ሽታ ተሰማ። ኅዘን እየቀለለ፤ ደስታ እየቀጠለ ሔደ።

የተረገዘው ጭንቀት ሁሉ ይወለድ ዘንድ በጭንቁ አፈ ማኅፀን ላይ ቀረበ። የፋሽስት ጉራ ሟሸሸ። የሙሶሎኒ ወንድነት ተኰላሸ።

Join us on Telegram @amharicbookss

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ አስቀድሞ የነበረው ያምስት ዓመት ኑሮው ምንም እንኳ በጭንቅና በብርቱ አደጋ ላይ ቢሆን ተስፋ አልቆረጠም ነበርና፤ ተስፋው ሰለደረሰለትና ንጉሠ ነገሥቱ በድል አድራጊነት ሰለተመለሱት ጮቤ መታ። እንደ ፌቆ ዘለለ። ዕልል አለ።

ከዚህ በኋላ ጠላት ፈጽሞ ወደቀ። የነጠቀውን ተነጠቀ። በቆፈረው ፈፋ ወደቀ። ተማረከ። በጉልበቱ ተንበረከከ። እጁን ሰጠ። ባንዲራው ተረገጠ። አርማው ሁሉ ተቀጠቀጠ። ድለኛ ሆነ።

የአዲሲቱ ኢትዮጵያ መሥራች ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በመንበረ መንግሥታቸው ተቀመጡ። ኢትዮጵያ ከሞት የተነሣችበትን ዘመን አዲስ ዘመን ብለው ሰየሙት። የሀገራቸውንና የሕዝባቸውንም አስተዳደር ባዲስ መንገድ መሩት።

ከኢትዮጵያ ጦርነት በኋላ ኢጣሊያ ፋሽስት በሊቢያ ጥቂት ጊዜ የሒትለርን ጅራት ጨብጣ ስትከላከል ቆየች። የቃል ኪዳን ጓደኞቹ ሲሲልን ሲወሩ፤ በጦርነቱ አኳኋን የኢጣሊያ ደካማነት በፍጹም ከተገለጠ በኋላ፤ ፋሽስት ሊሞት ሲጠራሞት፤ ናዚስት ልትሞት ነውን ትንፈራገጣለህና ቢለው፤ ዋ እንግዲያ ሽልቻ አለፋለሁ ብሎ የሞቱን ጉዞ ቀጠለ።

አሥራ አምስተኛ ክፍል።
አዲሱ ዘመን ኑሮአችን።

ከመከራ በኋላ የደስታ ዕረፍት ከባርነት በኋላ የተሞላ ነፃነት ሊገኝ፤ ምን የማይገኝ ክብር ይሆናል። ይህም ማለት አገር ከተገኘ ክብር ክብርም ከተገኘ የኑሮ መሻሻል አይገድም ማለት እንደሆነ ማንም አይስተውም።

ዕድሜ ለኃይለ ሥላሴ እንኳን አገራችን በእጃችን ገባች እንጂ፤ ከእግዲህስ ወዲህ ለኑሮዋችን እናውቅበታለን። ከመቼውም ይልቅ «ተከተል አለቃህን፤ ተመልከት ዓላማህን ተፋቀር ከወንድምህ ተደጋገፍ ከዘመድህ፤ ተምረህ ሠልጥን ሠልጥነህ ተመስገን» የተባለውን መፈጸሙን እናምናለን።

የባዕድማ አገዛዝ ምነው ታይቶ። የጠላትንስ ገዥነት ተወው አታንሣው። እንደ ወደቀ ይቅር። ከቶ ክብራችን በእጃችን መሆኑን ማወቅ ከማን ተደብቆ ይቀር ይሆን።

Join us on Telegram @amharicbookss

ወሰን ሰገድ መልካም ተናግረዋል። እበላ ያለ ናዝራዊ «የአባቶችህን አልጋ ታገኛለህ። ነገር ግን ዕድሜህ አጭር ነው ቢላቸው» «አልጋው ይገኝ እንጂ ዕድሜዬ ያለው በእጄ ስለሆነ እኔ አውቅበታለሁ» ብለው መልካም ሥራቸውን በመቀጠላቸው እሳቸው የተናገሩት እንጂ መነኩሴው ያወራው ሳይሆን ቀረ ይባላል።

እነሆ በእግዚአብሔር ቸርነትና በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ብርታት አገሩ ተገኝቷል። ነፃነት ተመልሷል። የተበተነ ተሰብስቧል። የተሰደደ ወደ አገሩ ተመልሷል። የወጣ ገብቷል። ዓይናችንን ያፈነው የዕንባ ጉም ተገፏል ከመከራ ስጥመት ወጥተን በሙሉ ደስታ ላይ እንገኛለን።

ይህ ሲሆን የተላለፍንበት ከምን ወደ ምን ነው። ከየትስ ወዴት ነው። በኋላችን ወደ ቀረው ኑሮ እንመለሳለን። ወይስ ወደ ፊት የሚቀጥል ሌላ አዲስ ኑሮ እንጀምራለን። እውነት ነው። ወደ ፊት እንጂ ወደ ኋላ መመለስ የለብንም። እግዚአብሔር ከመከራ ከወጣንና ላዲሱ ኑሮ ካበቃን አዲስ ኑሮ መቀጠል እንደሚያስፈልገን እናውቃለን። ወደ ኋላም የቀረውን አንዘነጋውም። ገልመጥ እያልን ስናየው ታላቅ ትምህርት እናገኝበታለን።

እግዚአብሔር ሰው ሁል ጊዜ ወደ ፊቱ ያለውን እየተመለከተ በስተኋላ ከቀረውም ይልቅ ወደ ፊት ያለውን ኑሮውን እንዲያስተውል፤ ዓይኖቹን በስተፊቱ ፈጥሮለታል። ለኛም ይህ አዲሱ ጊዜ አዲስ ዓይን ስለ ፈጠረልን ወደ ፊት አርቆና አዝልቆ ማየት አለብን። ማየት ብቻ አይደለም። በማየት በተገኘው የአእምሮ መሣሪያ ላዲሱ ኑሮ አዲስ ሠራተኛ ሁኖ ለመገኘት ጊዜ በመከራ ኰልቶ ያደሰው አዲሱ ሕዝብ አዲስ ጊዜ መፍጠር ያስፈልገዋል።

ማውራት እንጅ፤ መሥራት አይሆላቸውም። መጀመር እንጂ መፈጸም፤ አይቻላቸውም እንዳንባልና የተጫጨነው አዲስ ዕድል ከመንገድ እንዳይመለስ የቀድሞውን ትርኪ ምርኪና አርቲ ቡርቲ ግዛ ምዛና፤ አንጃ ግራንጃ እርግፍ አድርገን ትተን በታላቅ ትጋት መነሣት አለብን።

የሮጡ አምልጠውናል። የሠሩ በልጠውናል። እኛም ሠርተን ሥራችንን ብናሻሽል በተራችን መብለጣችን የማይጠረጠር ነው።

ከዛሬ ሺህ ዓመት በፊት የሥልጣኔው ተራ የሤማውያን እንጂ የያፌታውያን አልነበረም። ከሁለቱም አስቀድሞ ኢትዮጵያ የሥልጣኔ ቅድሚያ እንደነበራት ብዙ ምስክር አላት።

Join us on Telegram @amharicbookss

ወድቃ ተነስታ፤ እንደገና በመታደስ ላይ ያለችው ኢትዮጵያ፤ ጠላትን ለመውጋት የጨበጠቻቸውን ጦሮቿን ካስቀመጠች በኋላ፤ የምትጨብጣቸው የሥራ መሣሪያዎችን የቀለም ብርዖዎ ብቻ አይደሉም። ዕርፎትንና የፋብሪካዎችን እጀታዎች መጨበጥ አለበት። ያለፈው ጊዜ የቀረበለት የድል አገልግሎት በቂ አይደለም። ድል ያደረገ ሕዝብ እንደገና የንብረት ትግል ስላለበት፤ በንብረቱ የማይደክም ጀግና መሆኑን ሊዘነጋው አይችልም።

በኰሳ ማግሥት ባገኘሁ ሁለት እናት እንደሚባለው በዚሁ በመከራችን ማግሥት፤ ንብረትን ከነውዝዋዜው ድል ለማድረግ የምንችልበት ጠንካራ መሣሪያነት ያለው የልብ መንፈስ ሊኖረን ያስፈልጋል።

ጊዜ እንደ ሸክላ ዕቃ ካገለገለ በኋላ እንደ ገና የሚታደስ መሣሪያ ስለሆነ ጊዜውን ለማደስ የሚጠራጠር ሕዝብ ዘወትር ታዳሽ መሆኑን ማስተባበል የታሪክ ሥራ አይደለም። እርግጥ ነው። ይህ ጊዜ የምንለው የትውልድ መተላለፊያ ዓለምን አስችግሮታል። የሚይዘውንም አሳጥቶታል። ቅጠሉም አስጠፍቶታል።

የዓለም እርምጃ ያለው በሁለት ጠገግ ላይ ነው። ይህንም ለማወቅ ሩቅ ሳንሄድ ጠገጎቹ ሰላምና ጦርነት መሆናቸውን ልንረዳ እንችላለን። የሆነ ሆኖ ሰላም በጥቅም ረገድ የሚያገለገለውን ያህል ጦርነትም ሳያገለገለግል አይቀርም። እንዲሁም ጦርነትም የሚጐዳውን ያህል ሰላም ሳይጐዳ አለመቅረቱ አይጠረጠርም።

ይህም ማለት በዘመነ ሰላም ዝም ብሎ እጅን አጣምሮ መሣሪያ ሳይሠሩ መከላከያን ሳያደራጁ እንዲያው ሰላም ሰላም ቢሉት ሰላምነቱን አለመጥቀሙን በሰነፎች አቀማመጥ የሚረዳው የለም።

እንጨት እንኳ ከአንድ ወር ውስጥ የሚነቅዝበትና የማይነቅዝበት ወቅት ስላለው የወራትን አመል ያወቁ አባቶች እንጨት ሲቆርጡ ወሩን ከወሩም ቀኑን ቆጥረው ነው። ለምሳሌ እንደሰማነው እስከ መስከረም ቀኑን ፲፭ ፅንዕት ሲሆን ከዚያ በኋላ ፅንፅት ነው ይባላል።

የሌሎችም ወሮች ቀኖች ነቀዝ፤ የሚሆኑበትና የማይሆኑበት፤ ኢየዓርግና ኢይወርድ አላቸው። ግንቦት ጋብቻ የማይደረግበት ምክንያት ይህ ሳይሆን አይቀርም በማለት ይገመታል።

Join us on Telegram @amharicbookss

ዘመናትም እንደዚሁ ናቸው። መንፈቃቸው ሰላም፤ መንፈቃቸው ጦርነት ስለሆነ ዓለምን ነቀዛም እንጨት፤ ጊዜውንም ምስጣም ፍጥረት አድርገውት ይኖራሉ። ስለዚህ በሰላምና በጦርነት መካከል ላለው ጉዳትና ጥቅም ዘዴኛ መሆን ላዲሱ ኑሮ ያስፈልገዋል። ዘዴኛነትም ማለት ትርጓሜው ብዙ ነው። ጥቅም ከዚህ አለሁ ሥልጣኔ ከዚያ እገኛለሁ ከሚልበት ይልቁንም ዋናው መዲናው የገንዘብ ሥር ካለበት፤ አብሮ መገኘት ስለሆነ፤ የቁጠባን አያያዝ በማወቅ የሚደረገው ብልህነት። በኑሮ ረገድ ይጠቅማል። ቁጠባን ማወቅ ይጠቅማል ሲባልም ንፉግ ሁኑ ማለት አይደለም።

የኢኮኖሚው ሕግ የሚለው ቆጥብ ነው። ቆጥብ ሲል ግን ንፈግ ያለ ይመስላል። ነገር ግን ቆጣቢ ለጋስ ነው እንጂ ንፉግ አይደለም። አንድ ኢኮኖሚ ዐዋቂ የሆነ ሰው ገንዘብ ካጠራቀመ በኋላ ተጠራቅሞ የኖረውን የወገኑን ችግር በገንዘቡ ሳያስወግድለት አለመቅረቱ የታወቀ ነው። ባሥር ደሆች መካከል አንድ ሀብታም ከተገኘ አሥሩም ደሆች ሀብታሞች ናቸው ለማለት ይቻላል።

አንድ ደሀ፤ ለንግድም ሆነ ለእርሻ ግብርና ማስፋፊያ ወርቅና ብር የሚያበድረው ካገኘ፤ ሆኖ ሊቀር አይችልም። ይህም ሊስፋፋ የሚቻለው አበዳሪና ተበዳሪ ሲተማመኑና ኪዳናቸውን ሲጠብቁ ነው።

ጊዜ ይህን የመሰለውን ዘዴ የተከተለ ስለሆነ በፊት ትምህርት ቀጥሎ ገንዘብ ከዚህም በኋላ መተማመን ይኖረን ዘንድ ከአዲሱ ዘመን አደራ ተብለናል። መተማመን ከሌለ አንድም የሚኖር ነገር የለም።

ካላመነኝ ገንዘብ አያበድረኝም። እኔም ካላመንሁት አላበድረውም። ወይም የመረዳዳት ሥራ ሊኖረን አይችልም። በዚሁ መሠረት መተማመን ከሌለ፤ ደሀ በሀብታም ቤት ተቀጥሮ፤ ሀብታምም በደሀ ጉልበት ተረድቶ ከፍጹም ሀብት ሊደርስ አለመቻሉ የታወቀ ነው።

ያ አምስት ዓመት ምንም ሆድ ለጥድ የሚያሸካክርና በእምነት መካከል ጥርጥር የሚያሳድር ምክንያት ቢፈጥርም ያንን ወደ አገሩ ከተሰናበተው ጠላት ጋር አብሮ ማሰናበት ለማኅበራዊ ጥቅማችን አስፈላጊያችን ነው።

ታላቁ አሳቢያችንና ብርሃናዊው መሪያችን ላገለገለ ቸርነት ሲያደርጉ፤ ለበደለም ምሕረት ማድረጋቸው ኢትዮጵያ የሆነ ሁሉ ባዲሲቱ ኢትዮጵያ ዙሪያ አዲስ ሕዝብ ሁኖ በኅብረታዊ አገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆን መልካም ፈቃዳቸው ስለሆነ ነው።

Join us on Telegram @amharicbookss

በዚህም ረገድ ዓለም የኢኮኖሚንና የአስተያየትን ዘዴ ያውቅ ዘንድ ግዴታ ስለ አለበት ዛሬ ወጣቱ የኢትዮጵያ አስተዳደርና ተዳዳሪ ከመቸውም ይልቅ ትዳር ዐዋቂና ኑሮ አሻሻይ ለመሆን ጊዜው እንደሚያስገድደው ያውቅ ዘንድ ያስፈልገዋል፤ ሳያውቀውም አይቀርም።

ከላይ እንደ አልነው ይህን የመሰለ የጀግንነት ሙያና ምግባር ያለው ኢትዮጵያዊ የአስተዳደርና የአንዋንዋር የቈጣቢነትና የቻይነት፤ ይህን በመሰለው ነገር፤ ይህን የመሰለውን ዘዴኛ መሆን አስፈላጊ ነው። ዱሮ ሰው እንደ ቤቱ እንጂ እንደ ጐረቤቱ አያድርም ይባል ነበር።

ዛሬ ግን እንደ ጐረቤትም እንጂ እንደ ቤት ማደር ቀርቷል። ጐረቤት የተራመደውን ካልተራመዱና የሠራውን ካልሠሩ ጥቃት መከተሉ አይቀርም። ይህ ሲሆን ግን በጥበብና በዘዴ በፈሊጥና በልዩ አደራረግ ነው።

ይህ ዓለም የተፈጠረው የምኞት መፈጸሚያና ያሣር መጨረሻ ለመሆን ስለ ሆነ ሆነ እውነት ነው። ሁሉም ያምራል። ነገር ግን ወንዝን እንደ መልካው ይሻገራል ነገር ግን እንደ ጊዜው ይናገሯል፤ እንደሚባለው፤ ሁሉ አማረኝ ብሎ ይገኝ ዘንድ ወደማይቻለው፤ ማንጋጠጥና መሮጥ፤ ትርፉ ዘጥ ዘጥ ነው። ያ እንደ ቤቱ እንጂ እንደ ጐረቤቱ የሚባለው ተረት፤ ለዚህ ብቻ ይጠቅማል።

የውጭ አገር ጌጥና ዕቃ፤ ልብስና ይህን የመሳሰለው ሁሉ ከመጥፋቱ የተነሣ፤ በጣም ውድ ሆኗል። አንድም የረከሰ ነገር የለም። በተሠራበትና በሚሠራበት አገር ይህን ያህል

ውድ ሲሆን ባልተሠራበትና በማይሠራበት አገርማ ውድነቱ ምን ያህል ይሆን።

እንግዲህ በሚቻል ዋጋ የማይገኘውን በማይቻል ዋጋ አገኛለሁ ማለት መጠንን አለማወቅ ነው። ይህም ያዲሱን ዘመን ጉልማሳነት ያለ ዕድሜው ያስረጀዋል።

ከፍ ያለ ክብርና ውድነት ባላቸው በሌሎች ዕቃዎችና ልብሳልብሶች እንዲሁም ከፍ ያለ ወጭ ባላቸው በብዙ ጉዳዮች ሁሉ መስሎ ለመታየት መግደርደርና መሽቆንጠር ለሥልጣኔ ምኑም አይደል።

ለሥልጣኔስ የሚስማማው የጊዜን ሁናቴ በመመልከት የሚደረገው ቁጠባና በዚያው ጊዜው በፈቀደለት መጠን ያሉበትን ደረጃ ማሳመር ነው። ሁሉን ነገር አሳማሪና መልክ ሰጭ ወሃና ሳሙና ምላጭና መቀስ ልዩ ተግባረ ዕድ የሥራ መስፋት ስለሆነ ልብስንም ገላንም፤ ቤትንም፤ ፊትንም፤ ጠጉርንም፤

Join us on Telegram @amharicbookss

ጥርስንም፤ መንገድንም፤ ከተማንም፤ ሁሉ ማጥዳት አለባበስንና አካሔድን፤ አሠራርና አስተዳደርን፤ አነጋገርንና አጻጻፍን፤ ሌሎችንም የንጽሕና ተግባሮችና የእጅ ሥራዎች መንገዶችንም ሁሉ ለሕዝብ እንደሚጠቅሙ አድርጎ በሰፊው መዘርጋት፤ ያዲሱ ዘመን ሥራ ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በኤውሮፓ ይታያሉ። በመታየታቸውም ያስደንቃሉ በሥራቸውም ይጠቅማሉ ተብለው የተጠሩት ሥነ ጥበባትና ፍልስፍናዎች የተሠሩት በሰላማዊ ዘመን ነው። ለሞኝ ሰኔ በጋው የሚባለው ምሳሌ የሚያስተምረው ሰላም የጦርነት መደራጃ መሆኑን ነው።

እነሱስ በሰላምና በጦርነት ጊዜም ቢሆን ለመሥራት ችለዋል። ባጭሩ ለማስረዳት አሁን በቅርቡ ጃፓን ፈጽሞ የተሸነፈበትና እጁን የሰጠበት ምክንያት በጦርነት ሰዓት ተሠርቶ በወጣው በአቶሚክ ቦምብ ደምሳሽነት መሆኑን ማንም አይስተውም።

ስለዚህ ለእኛ የሚጠቅመን ያየነውን መሥራት ነው እንጂ ማውራት ብቻ አይደለም። ወሬ ያለፍሬ ያስቀራል። አፍ ቢሰፋ እጅ ሥራ ካልሠራ ቁም ነገር የለውም። ኤውሮፖች አያሌ ገሥግሠዋል። ይገሠግሣሉም። ሞቅ ብሎ የሚሰማው ወሬና የሚታየው ታምር እኛንም ገፍቶ ከደረጃው በላይ አውጥቶ ቁብ ያደረገን ዘንድ አሁን በያዝነው መንቀሳቀስ ላይ ፈጣን እርምጃና የቀለጠፈ ግሥጋሴ የቀጠልን እንደሆነ ታሪካችንም፤ ሀብታችንም የገነነ ይሆናል።

Join us on Telegram @amharicbookss